አጥፊና ጠፊ



የሊቀ መንበሩ ጉብኝት በጎንደር 7ኛ ክፍለ ጦር

---

*ጊዜ የሚያመጣው የረቀቀ ምስጢር፣ የረቀቀ ሁነት*
*ለሰዎች ሕሊና ስለማይከሰት*
*ሟች ከገዳዩ ጋራ፣ አጥፊም ጠፊን ይዞ*
*በአብሮነት ይጓዛል፣ የሕይወትን መንገድ፣ ያጭር ምዕራፍ ጉዞ ።*
*የዚህ ዓለም ታሪክ ይህን ይመስላል*
*በሚገርም ክስተት ሰው በሰው ይበላል።*

---





# ምዕራፍ ፳

## እንደ ጠማማ ቀስት የተገለበጠ ሁኔታ፣

በምዕራፍ ሁለት ውስጥ በገሀድ፣ ቀንና ቁጥር በጨበጠና በተፈረመበት፣ እንዲሁም ሕጋዊ ማኅተም ባረፈበት የምስጋና ደብዳቤ፣ ጄኔራል ረጋሣ ጂማ በቅርብ አለቅነታቸው ባዩትና ባረጋገጡት የተግባር ውጤት ስለ ጄኔራል ታሪኩ ጀግንነት ግልጽ ምስክርነት ሰጥተዋል።

በማንኛውም የሥራ ዘርፍ የአለቃና የምንዝር ግንኙነት ሲፈተሽ በተለያየ ደረጃና ምክንያት በጎ የነበረው ሻካራ፣ መደማመጥና እውቀት ባለበት ሁኔታ ሲያዝ ደግሞ ሻካራው ግንኙነት ሰላማዊ ፈር መያዝ እንደሚችል ይታወቃል።

ይሁንና፣ መመሪያ ሲሰጡትና ሲያዙት የነበረ የበታች ሠራተኛና የሥራ ባልደረባ በሥራውና በውጤቱ እያደገ እኩያ በሚሆንበት ጊዜ፣ ወይም በግልጽና በድፍረት ስለ እውነት የሚሟገት ከሆነ፣ አንዳንድ ደካማ አስተሳሰብ ባላቸው ሰዎች ሕሊና ውስጥ ከድብቁ ሰብዕናቸው የሚመነጭ ከባድ ቅናትና ምቀኝነት ነፍስ በመዝራት ግለሰቡን ወደ መሠሪነትና ወደ አጥፊነት እንደሚገፋፉት የሥነ አዕምሮ ምሁራን ይናገራሉ።

ይህንን ዕኩይ ሰብአዊ የባህርይ ለውጥ በጄኔራል ታሪኩ የግዳጅ እንቅስቃሴና ሕይወት ላይ አሉታዊ ውጤት ያስከተለውን የጄኔራል ረጋሣ ጂማ ሁኔታና ድርጊት፣ በታሪክ ፀሐፊዎች ትዝብትና በሰጡት ምስክርነት እንደሚከተለው ማየት ይቻላል።

## አጥፊና ጠፊ



የሊቀ መንበሩ ጉብኝት በጎንደር 7ኛ ክፍለ ጦር

ጊዜ የሚያመጣው የረቀቀ ምስጢር፣ የረቀቀ ሁነት
ለሰዎች ሕሊና ስለማይከሰት
ሟች ከገዳዩ ጋራ፣ አጥፊም ጠፊን ይዞ
በአብሮነት ይጓዛል፣ የሕይወትን መንገድ፣ ያጭር ምዕራፍ ጉዞ ።
የዚህ ዓለም ታሪክ ይህን ይመስላል
በሚገርም ክስተት ሰው በሰው ይበላል።





# ምዕራፍ ፫

## እንደ ጠማማ ቀስት የተገለበጠ ሁኔታ፣

በምዕራፍ ሁለት ውስጥ በገሀድ፣ ቀንና ቁጥር በጨበጠና በተፈረመበት፣ እንዲሁም ሕጋዊ ማንተም ባረፈበት የምስጋና ደብዳቤ፣ ጄኔራል ረጋሣ ጂማ በቅርብ አለቅነታቸው ባዩትና ባረጋገጡት የተግባር ውጤት ስለ ጄኔራል ታሪኩ ጀግንነት ግልጽ ምስክርነት ሰጥተዋል።

በማንኛውም የሥራ ዘርፍ የአለቃና የምንዝር ግንኙነት ሲፈተሽ በተለያየ ደረጃና ምክንያት በጎ የነበረው ሻካራ፣ መደማመጥና እውቀት ባለበት ሁኔታ ሲያዝ ደግሞ ሻካራው ግንኙነት ሰላማዊ ፈር መያዝ እንደሚችል ይታወቃል።

ይሁንና፣ መመሪያ ሲሰጡትና ሲያዙት የነበረ የበታች ሠራተኛና የሥራ ባልደረባ በሥራውና በውጤቱ እያደገ እኩያ በሚሆንበት ጊዜ፣ ወይም በግልጽና በድፍረት ስለ እውነት የሚሟገት ከሆነ፣ አንዳንድ ደካማ አስተሳሰብ ባላቸው ሰዎች ሕሊና ውስጥ ከድብቁ ሰብዕናቸው የሚመነጭ ከባድ ቅናትና ምቀኝነት ነፍስ በመዝራት ግለሰቡን ወደ መሠሪነትና ወደ አጥፊነት እንደሚገፋፉት የሥነ አዕምሮ ምሁራን ይናገራሉ።

ይህንን ዕኩይ ስብእዊ የባህርይ ለውጥ በጄኔራል ታሪኩ የግዳጅ እንቅስቃሴና ሕይወት ላይ አሉታዊ ውጤት ያስከተለውን የጄኔራል ረጋሣ ጂማ ሁኔታና ድርጊት፣ በታሪክ ፀሐፊዎች ትዝብትና በሰጡት ምስክርነት እንደሚከተለው ማየት ይቻላል።

ሻምበል ኢዮብ አባተ እንዳለ፣ጄኔራሎቹ በሚል ርዕስ መስከረም 2002 ዓ.ም ለንባብ ባበቁት መጽሐፍ *(ገጽ 66፣67 እና ገጽ 68)* ላይ፣ ስለ ብ/ጄ ታሪኩ ተፈጥሮአዊ ባህርይ፣ ችሎታና የአመራር ብቃት እንደሚከተለው ጽፈዋል።

‹‹በተፈጥሮአቸው ፍርሃት የሚባል ነገር ያልፈጠረባቸውና በወታደራዊ አመራር ብቃታቸው ከፍተኛ ችሎታ እንደነበራቸው በጓደኞቻቸው የተመሰከረላቸው ብ/ጄ ታሪኩ ዓይኔ፣ የናደው ዕዝ አዛዥ ከመሆናቸው በፊት የትግራይ ዕዝ አዛዥ፣ ከዚያም በፊት የ7ኛ ክፍለ ጦር አዛዥ ነበሩ።›› በማለት ጄኔራሉ ተሠማርተውበት የነበረውን የግዳጅ ሥፍራና የኃላፊነት ደረጃ ጭምር ገልጸዋል።

ሻምበል ኢዮብ በመቀጠል ጄ/ታሪኩ ከጄ/ ረጋሣ ጅማ ጋር ከጎንደር ጀምሮ ፀብና መቃቃር እንደነበራቸው ለማሳየት፣

‹‹.....,ጄኔራሉ በጎንደር የ7ኛ ክፍለ ጦር አዛዥ በነበሩበት ጊዜ 35ኛ ሻለቃ ከድቶ ወደ ኢዲዩ እንዲገባ አድርገዋል በማለት መንግሥት ቀጥቷቸው ነበር።›› ሲሉ ጽፈዋል። በመቀጠልም፣

‹‹.......ጄ/ታሪኩ ጎንደር ሳሉ የበላይ አለቃቸው ከነበሩት ጄ/ረጋሣ ጂማ ጋር ከፍተኛ አለመግባባትና ቅራኔ እንደነበራቸው ፕሬዚደንቱ ሳይቀሩ በቅርብ የሚያውቁት ጉዳይ ነው......›› በማለት አክለው ገልጸዋል።

ይህ ከላይ የተሰጠው መግለጫ ጄ/ረጋሣ ጂማ የ501ኛ ግብረ ኃይል አዛዥ በነበሩበት ጊዜ ጎንደር ለነበሩት የ7ኛ ክፍለ ጦር አዛዥ ለጄ/ታሪኩ ዓይኔ ከጻፉላቸው የምስጋናና የምስክርነት ደብዳቤና ቃል መሠረት ፍፁም የሚቃረንና ስህተት ሆኖ ይታያል።





ከላይ በሻምበል ኢዮብ የተጠቀሰው የክስ ጭብጥ የተዛባ መሆኑን ለማረጋገጥ በራሳቸው በጄ/ረጋሣ ምስክርነት ኢዲዩንና ኢህአፓን ከጎንደር አካባቢ በማስወገድ ጄ/ ታሪኩ ባሳዩት አኩሪ ውጤት ይልቁንም ምስጋናና አድናቆት እንደቸሩዋቸው ቀደም ሲል በቀረቡት የቅጂ ደብዳቤዎች መረዳት ይቻላል። በርግጥ ቅራኔና ክስ በመካከላቸው ሙሉ በሙሉ አልነበረም ማለት አይደለም። ቅራኔው የተጀመረው ጄኔራል ታሪኩ የትግራይ ዕዝ አዛዥ በነበሩበት የአገልገሎት ዘመን እንደነበረ የምስጋና ደብዳቤዎቹ እንደሚጠቁሙ መረዳት ይቻላል።

ስለ መቀሌው ወህኒ ቤት በወያኔ መደፈርና ስለ እስረኞች መለቀቅ በተመለከተም፣ ‹‹.....ጄ/ታሪኩ ትግራይ በነበሩበት ወቅት፣ ሕውሃት የመቀሌን ወህኒ ቤት አጥቅቶ እስረኞችን ሲያስለቅቅ፣ የፖሊስ አዛዡ፣ ዕዙ እርዳታ እንዲያደርጉላቸው ጄ/ታሪኩን በስልክ ሲጠይቁ፣ ‹እኔ የወህኒ ቤት ዘበኛ አይደለሁም፣....› በማለት በሰጡት መልስና በደረሰው ጉዳት ተከሰው ከመንግሥት ጋር ከፍተኛ ቅራኔ ውስጥ ገብተዋል።››

ካሉ በኋላ ሻምበል ኢዮብ መነሻ መሠረት የሆናቸውን ጭብጥ ሳይጠቁሙ ግላዊ ትችታቸውንና ፍርዳቸውን እንደሚከተለው ሰጥተዋል። ‹‹......ጄኔራሉ በወቅቱ የፈፀሙት ስህተትና ያሳዩት ግዴለሽነት ብዙዎችን አስገርሟል። ወዲያው መንግሥት ጄኔራሉን ለመቅጣት ይመስላል፣ ከትግራይ ዕዝ አንስቶ የናደው ዕዝ አዛዥ አደረጋቸው። በማለት አስፍተው ጽፈዋል።

በመሠረቱ፣ ጄ/ታሪኩ የትግራይ ዕዝ አዛዥ በነበሩበት ወቅት፣ የትግራይ አማጺያን ተማርከውና በመቀሌ ወህኒ ቤት እንዲታሰሩ በተደረገበት ጊዜ፣ የአካባቢውን ነባራዊ ሁኔታ አበጥረው ያውቁ

ስለነበረ ወንበዴዎቹ ከመቀሌ ይልቅ አዲስ አበባ ተወስደው ቢታሠሩ በአስተማማኝ ሁኔታ በቁጥጥር ሥር እንደሚቆዩ ለመንግሥት ገልጸው ነበር። ይሁን እንጂ የሳቸው ሀሳብ ውድቅ ተደርጎ አማጽያኑ በዚያው ከተማ እንዲቆዩ ተደረገ።

ጄኔራል ታሪኩ ይህን ያሉበት መሠረታዊ ምክንያት ነበራቸው። በወቅቱ በትግራይ ውስጥ፣ ከምክትል አስተዳዳሪው እስከ የክፍለ ሀገሩ አውራጃ አስተዳዳሪዎችና የአውራጃ ኢሠፓ ተጠሪዎች ጭምር፣ ላይ ላዩን የመንግሥት ሠራተኞችና ደጋፊዎች መስለው በዓላማ ግን የአማጽያኑ ደጋፊዎች እንደነበሩና ድርብ ሚና እንደሚጫወቱ ይደርሳቸው በነበረ ወታደራዊ መረጃ ያውቁ ስለነበረ ነው።

የአብዮታዊነት ጭምብል አጥልቀው ነገር ግን ለህወሃት ታጥቀው ብዙዎች በሚንቀሳቀሱበት በዚያ ክፍለ ሀገር የወያኔዎቹ በመቀሌ መታሰር ትርጉም አልባ እንደሆነና ወህኒ ቤቱም አንድ ቀን ተሰብሮ ምርኮኞቹ እንዲያመልጡ እንደሚደረግ ጥሩ ግምት ነበራቸው።

ውሎ አድሮ ጄኔራሉ እንደገመቱት፣ በተቀነባበረ ሴራ እስር ቤቱ ተሰብሮ እስረኞች እንዲያመልጡ ተደርጓል። ከዚህ በኋላ በፖሊስ አዛዡ የተጠየቀውን እርዳታ ሲሰጡ አልፈቀዱም በሚል በተጋነነ ሂስና ክስ በብዙዎች ተተችተዋል ተወንጅለዋልም። ይህም በሻምበል ኢዮብ እንዳለ መጽሐፍ እንደታየው ሁሉ በሌሎችም መጻሕፍት ላይ ተገልጧል።

የእስረኞቹ ማምለጥ ጠንካራ ሴራ የነበረው የአማጽያኑ ደጋፊዎች እንቅስቃሴ እንደመሆኑ ሁሉ፣ የጀ/ ታሪኩ ሀሳብ ውድቅ





መደረግም ለምርኮኞቹ ማምለጥ ምክንያት የሆነ መሠረታዊ ሁኔታ ነበር።

እነዚያ፣ ድርብ ሚና የነበራቸው የደርግ የፖለቲካና የሲቪል ባለሥልጣናት ከአማጺው ቡድን ጋር የነበራቸው የግንኙነት መረብ በእርግጥም ሰፊና ጥብቅ እንደነበረ ውሎ አድሮ በሂደትና በድርጊት ታይቷል።

ይህንን ሁኔታም ዛሬ በሕይወት ያሉት የ‹‹እናብስት ምድርና ዋ.....ምዕዋ›› ደራሲ የመቶ አለቃ ታደሰ ቴሌ ሰልባኖ በምስክርነት ቃላቸው እንደሚከተለው አብራርተው ገልፀውታል።

‹‹ጀ/ታሪኩ ትግራይ ዕዝ አዛዥ በነበሩበት ጊዜ የሲቪሉ ኅብረተሰብ፣ አብዛኛው ባለሥልጣናት፣ ከነበረው የትግል ወይም የሕወሃት እንቅስቃሴ ጋር ተዳብለው ስለነበሩ፣ ታሪኩንም ለመመልመልና በኋላም አቋማቸውን ማስቀየር ሲያቅታቸው ለማስገደል ብዙ ጥረት አድርገው ነበር።

‹‹ታሪኩም ሁኔታውን በማጋለጣቸውና ዝርዝር መረጃውን ለማዕከላዊ መንግሥት በማቅረባቸው ከብዙዎች ጥርስ ውስጥ ገቡ። በዚሁ መሠረት፣ አቶ ጎሩይ የተባለ የትግራይ ክልል ምክትል አስተዳዳሪ ንቁ የሕወሃት አባልና የውስጥ አርበኛ መሆኑ ተረጋግጦ፣ መንግሥት ሲይዘው ሲሞክር፣እጁን እንዲሰጥ ሲጠየቅ፣ ሥራውን ያውቅ ስለነበረ በሩን ዘግቶ በገዛ እጁ ሕይወቱን አጥፍቶአል።

‹‹ሌሎችም አስራ አንድ የአውራጃ የኢሠፓ ተጠሪዎች፣ የትግራይ የሠላሳ አንዱ አውራጃ አስተዳዳሪዎች ሕወሃት ሆነው ስለተገኙ ሁሉም በቦታው ላይ ታስረው ለምርመራ በቀረቡበት ወቅት፣ ታሪኩ በመመስገን ለአገራቸው፣ለሙያቸውና ለወገናቸው

ሀቀኛ እንደነበሩ አስመስክረዋል። በሕዝቡም ሆነ በትግራይ አንዳንድ የአብዮቱ እውነተኛ አራማጆች፣ እንዲሁም የትግራይ ተወላጅ የሆኑ የሠራዊቱ አባሎችና በአካባቢው ነዋሪዎች ይደነቁ የነበሩ ሰውና በሠራዊቱ ይወደዱ የነበሩ ሰው ናቸው።›› በማለት ያ የመቀሌ የወህኒ ቤት ትርኢት ሹፈት እንደነበረና በጄኔራሉም የተሰጠው መልስ ትክክል እንደነበረ የሚያስገነዝብ ቃላቸውን ሰጥተዋል፡

የጄኔራል ታሪኩና የጄኔራል ረጋሣ ጂማ ቅራኔ መሠረት ሊሆን እንደሚችልና በመጨረሻም ለአብዮታዊው ሠራዊት የመጨረሻ ሽንፈት ምክንያት ነው ተብሎ የታመነባቸውን ነጥቦች መቶ አለቃ ታደሰ«የአናብስት ምድር» መጽሐፋቸው፣ ገጽ 436 ላይ እንደሚከተለው አስቀምጠውታል።

እንደ መቶ አለቃ ታደሰ መግለጫ፣ ለታላቁ የኢትዮጵያ ሠራዊት ሽንፈት

‹‹1. የሠራዊቱ አመራሮች መከፋፈል ዋነኛው ነው። በደርግ ዘመን የነበሩ ጄኔራል መኰንኖች፣ በክቡር ዘበኛና፣በጦር ሠራዊት፣ምሩቅነት፣ በወንዝ ልጅነት፣ በኮርስ ጓድነት ወዘተ.....የተከፋፈሉ፣

በሥልጣንና በጥቅማ ጥቅም የተሳሰሩ፣ ................የእርስ በርስ ስለላ፣ ስም ማጥፋት፣ የሥልጣን ሽኩቻ በመካከላቸው በመስፈኑ ምክንያት...... በዘመድ አዝማድ፣ ........ ተሳስረው በንግድ ላይ የተሰማሩ መኰንኖች ጥቂት አልነበሩም።

2 አብዛኛዎቹ አመራሮች ከጦር ግንባር ይልቅ፣ መሀል ከተማና መሀል አገር፣ ከውጊያ ይልቅ የቢሮ ውስጥ





ኃላፊነት መሸከም፣ ከዛም አልፎ ከቤተሰቦቻቸው ጋር ሰላማዊ ኑሮ መኖር የሚፈልጉ.....ወዘተርፈ እና ጦርነቱን እንደ ጦርነት ሳይሆን እንደ ከፍተኛ የገቢ ምንጭ፣ ካምፓኒ የቆጠሩ መኰንኖች ነበሩ።›› ሲሉ፣

የሚያውቁትን የመከፋፈልና የቡድን ገመና ገላልጠው በማስነበብ በአመራር ላይ የነበሩት አዛዦች ከኮርስ ጓደኞቻቸው ጋር አንድ የነበሩበትንና የተጠቃቀሙበትን፣ እንዲሁም ከሚጠሏቸው ጋር የተለዩበትንና ፀብና ቅራኔ የፈጠሩበትን መሠረታዊ ነጥቦች ጠቁመዋል።

ጄኔራል ታሪኩና ጄኔራል ረጋሣ ጂማ ደግሞ ከተለያዩ የሠራዊት ክፍሎች የመጡ ነበሩ። ጄኔራል ታሪኩ ከጦር ሠራዊት፣ ጄኔራል ረጋሣ ከክብር ዘበኛ ሠራዊት የተገኙ ነበሩ።

እነዚህ ታላላቅ ወታደራዊ ክፍሎች ከአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ጀምሮ በመናናቅና በመጠላላት አንዱ ከሌላው እሻላለሁ በሚል ስሜት ያደርጉት የነበረው መጠላለፍና ሽኩቻ፣ አልፎ ተርፎ በሠራዊቱ ውድ ሕይወትና በአገሪቱ ሕልውናና ንብረት ላይ አሉታዊ ጫና እንዳሳደረ ወታደራዊ ታሪክ ፀሐፍት ገልጸውታል።

ይህ ሥሩ የራቀና የደነደነ የቡድን ዕብሪት ስሜት የሥልጣንና የጥቅምን ቅርምት መሠረት አድርጎ ጄ/ረጋሣ በጄ/ታሪኩ ላይ ከመሰሎቻቸው ጋር በመሆን ጠልፈው እንዲጥሏቸው ሊያደርግ እንደሚችል መገመት ይቻላል።

ሻምበል ተስፋዬ ርስቴም ይህንኑ ሀሳብ በመጋራት፣ ‹‹ምስክርነት በባለሥልጣናቱ እንደበት›› መጽሐፋቸው ገጽ 280 ላይ፣

‹‹........ጄኔራል ኃይለጊዮርጊስ ሀብተ ማርያም፣ መርዕድ ንጉሤ፣ደምሴ ቡልቶ፣ ሙላቱ ነጋሽ፣ ረጋሣ ጂማ፣ አሥራት ብሩ፣ ከንፈ ገብርኤል ድንቁ፣ ብርሃኑ ደምሴ፣ ዘውዴ ገብረየስ እና ሌሎች ከፍተኛ ጄኔራሎች እናት ክፍላቸው ክብር ዘበኛ ነበር።

‹‹እነዚህ መኰንኖች በአብዮቱ ዓመታት ወቅት በምድር ጦር ሠራዊት በልዩ ልዩ ቁልፍ የኃላፊነት ቦታዎች በመመደብ መርተዋል። ጄኔራል ሀብተጊዮርጊስ የመከላከያ ሚኒስትር ሲሆኑ ጠቅላላውን የመከላከያ ሠራዊት መሪነት ክብር ዘበኞች ተቆጣጠሩት።

‹‹ከሆለታ ገነት የጦር ትምህርት ቤት የተመረቁት የጦር ሠራዊት መኰንኖች ደግሞ የክብር ዘበኞችን መሪነት አምርረው ይቃወሙ፣ ይታገሉም ነበር።›› በማለት ከሁለቱ የውትድርና ዘርፎች የመጡት መኰንኖች ምን ያህል የጠዘ የሥልጣን ሽኩቻ እንደነበራቸው ገልጸዋል።

በተጨማሪም፣ በጄኔራል ታሪኩና በጄኔራል ረጋሣ ጂማ መካከል ስለነበረው ፀብና ክስ በማውሳት፣ ሻምበል ተስፋዬ ርስቴ እንደጻፉት

‹‹.....ታሪኩ ዓይኔ ከጄ/ል ረጋሣ ጅማ ጋር ጉንደር ውስጥ ተጣልተው ጦር ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ ተደርገው ነበር። ረጋሣ ጅማን በመናቅ፣ በማዋረድና በመጋፋት ነበር የተወነጀሉት።›› ሲሉ ጥቅል የሆነ ሀሳብ አስቀምጠዋል።

ከላይ ለተጠቀሰው ፀብና ክስ እንዲሁም የመጨረሻ ውጤት መሠረታዊ መነሻው የሚከተለው ጉዳይ እንደነበር ከጄኔራል ታሪኩ የግል ማኅደር የተገኘው ሰነድ ያስረዳል። ጉዳዩ እንዲህ ነበር።





ብ/ጄ ታሪኩ በ1974 ዓ.ም በኰሎኔልነት ማዕረግ የሰሜን ዕዝ የ501ኛ ግብረ ኃይል የዘመቻ አስተባባሪ መኰንን ሆነው በሠሩበት ወቅት፣ ጥቅምት 18 1974 ዓ.ም በተጻፈ የክስ ማመልከቻ፣ በዐቃቤ ሕግ በኩል ክስ ተመሥርቶባቸው፣ ማመልከቻውም ለጦሩ ፍርድ ቤት ጥቅምት 26 ቀን 74 ዓ.ም ቀረበ። በጄኔራሉ ላይ የተመሠረቱባቸው የክስ ጭብጦች የሚከተሉት ነበሩ።

1 የግብረ ኃይሉን የማዘዣ ቦታ ከአክሱም ወደ ሺሬ እንዳሥላሴ አዛውረው እንዲያቋቁሙ ከሰሜን ዕዝ አዛዥ ብ/ጄኔራል አስራት ብሩ ተደጋግሞ የተሰጣቸውን ትእዛዝ አልፈፀሙም፣

2 የካቲት 19 ቀን 73 ዓ.ም በሌ/ኰሎኔል መርዳሳ ሌሊሳ አዛዥነት ተዋጊ ግብረ ኃይል ሺራሮን ለማስስ እንዲዘምት ተወስኖ እንቅስቃሴ በተደረገበት ጊዜ፣ አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲሰጥ፣ (ቁስለኞችን ለማንሳት) አንድ ሄሊኮፕተርና አንድ ሲሲና አውሮፕላኖች አክሱም ላይ ሆነው እንዲጠባበቁ የተደረጉትን ለሌላ ተግባር በማስማራት ለአንገብጋቢ ድጋፍ እንዳይገኝ በማድረግ በፈፀሙት ጥፋት ተከሰዋል።›› የሚሉ ነበር።

እንደ ሰነዱ አገላለጽ፣ጄኔራል ታሪኩ፣በወቅቱ በማያውቁት ምክንያትና ባልተረዱት ሁኔታ፣ ከ501ኛ ግብረ ኃይል የዘመቻ አስተባባሪነት ተነስተው ወደ 7ኛ ክፍለ ጦር አዛዥነታቸው ከየካቲት 18 ቀን 1973 ዓ.ም ጀምሮ እንዲመለሱ፣ በቁጥር 3/ሰዕ/ ም/4/1466 በተጻፈ ቴሌግራም ታዘው ነበር። ይህንን የሥፍራ ማለዋወጥ ሂደት የወሰኑት አዛዦችም፣

1ኛ የሰሜን ዕዝ አዛዥ ብ/ጄኔራል አስራት ብሩ
2ኛ የሰሜን ዕዝ ጥብቅ አዛዥ ብ/ጄኔራል ረጋሣ ጂማ
3ኛ ሌ/ኮሎኔል ታደሰ ተሰማ፣ የሰሜን ዕዝ የዘመቻ መኮንን ነበሩ።

የ18ኛ ክፍለ ጦር አዛዥ የነበሩትና በጄኔራል ታሪኩ ሥፍራ የተተኩት ሌ/ኮሎኔል መርዳሳ ሌሊሳም ከሰሜን ዕዝ መምሪያ ጋር ባልተቋረጠ ሁኔታ እየተገናኙ፣ የሽራሮን አካባቢ አሰሳን በሚሰጣቸው ትእዛዝ መሠረት እንዲጀምሩ፣ አድራሻው ለ7ኛ ክፍለ ጦር አዛዥ በሆነ፣ ከሰሜን ዕዝ አዛዥ በቁጥር 3/ሠዕ/ም/4/1466 የካቲት 18 ቀን 1973 ዓ.ም በተጻፈ ቴሌግራም ትእዛዝ ደርሷቸዋል። በዚህ መሠረት ጄኔራል ታሪኩ በታዘዙት መሠረት ወደ 7ኛ ክፍለ ጦር ተመልሰው ሄደዋል።

ኮሎኔል መርዳሳም በታውንና ሥራውን ተረክበው አሰሳውን የካቲት 19 ቀን ጀምረው ሽራሮ አካባቢ ሲደርሱ ያላሰቡትና ያልገመቱት የጠላት ምከታና አደጋ ያጋጥማቸዋል።

‹‹በዚያ ውጊያ ወቅት በርካታ የወገን ሕይወትና የአገር ንብረት በከንቱ ወደመ። ይህ ጥናት ያልተደረገበትና ጊዜ ተሰጥቶት በዕቅድ ያልተመራ፣ የችኮላ የውጊያ ዘመቻ ያስከተለው ክስረት ከላይ በስም የተጠቀሱትን የዕዝ አዛዦች ባለሥልጣናትና ኮሎኔል መርዳሳን በኃላፊነት የሚያስጠይቃቸው መሆኑ ግልጽና ትክክለኛ ጭብጥ ሆኖ ሳለ የተከሰሱት ጄኔራል ታሪኩ መሆናቸው የሚገርም ሆኖ ተገልጿል። እንደ ሰነዱ አገላለጽ፣

‹‹ይህንን የተረዱት ባለሥልጣናትም ከተጠያቂነት ለመዳን እንደገና ሌላ ተንኮልና ሴራ ጉንጉኑ። በነሱ ትእዛዝና መመሪያ





ከ501ኛ ግብረ ኃይል ተነስተው ወደ 7ኛ ክፍለ ጦር እንዲመለሱ የታዘዙትና በትእዛዙ መሠረት ወደ 7ኛ ክፍለ ጦር የሄዱት ጄኔራል ታሪኩ ለደረሰው ጥፋት ሁሉ ተጠያቂ ሆነው እንዲቀርቡ ክስ ተመሠረተባቸው።

በዚህ ጊዜ የጄኔራል ታሪኩ ጠበቃ ሆነው የቆሙትና ጉዳዩ ለትክክለኛ ፍትህ እንዲበቃ በፍርድ ፊት ሲከራከሩላቸው የነበሩት የሕግ ባለሙያው ኮሎኔል ታምራት ጎበዜ ነበሩ።

ዐቃቤ ሕጉም በሀገር መከላከያ ሚኒስትር ትዕዛዝ ለተቋቋመው ጠቅላይ የጦር ፍርድ ቤት ክሱን መሥርቶ ካቀረባቸው ሰባት የሰው ምስክሮች ውስጥ ሦስቱ፣

1ኛ የሰሜን ዕዝ አዛዥ ብ/ጄኔራል አስራት ብሩ
2ኛ የሰሜን ዕዝ ጥብቅ አዛዥ ብ/ጄኔራል ረጋሳ ጂማ
3ኛ ሌ/ኮሎኔል ታደሰ ተሰማ ይገኙበት ነበር።

በተራ ቁጥር አንድ ላይ የተጠቀሱት ምስክር፣ የሰሜን ዕዝ አዛዥ ብ/ጄኔራል አስራት ብሩ ከጦር ፍርድ ቤቱ ቀርበው የሰጡት የምስክርነት ቃላቸው፣

‹‹ተከሳሹ መኮንን የሽራሮን አሰሳ ዕቅድ ሽሬ ላይ ሆነው እንዲሰጡ እኔው ራሴ በቃል አዝዣቸዋለሁ።›› የሚል ነበር።

በመሠረቱ፣ የሰለጠነና የታላቅ አገር የጦር ኃይል አዛዥ ሥርዓትና ደንብ በሌለው የግንኙነት ሂደት፣ በቃል ንግግር፣ ትእዛዝ ያስተላልፋል ማለት አይታሰብም። ከተደረገም ስህተት መሆኑ ገሀድ ነው። አሠራሩም የተለመደ ከነበረ፣ የአመራሩን ገመና ለትዝብት

የሚያጋልጥ ነው። ትእዛዝና መመሪያ፣ በጽሑፍና በወጪ ቁጥር፣ ፊርማና ማኅተም በያዘ ሕጋዊነት ሥርዓት መንቀሳቀስ አለበት በማለት ተከላካይ ጠበቃው የተሰጠው የምስክርነት ቃል ተአማኒነት እንደሌለው አስረድተዋል። ከዚህም ጋር ቀደም ሲል በቁጥር 3/ሠዕ/ም/4/1466 የካቲት 18 ቀን 1973 ዓ.ም በተጻፈ ቴሌግራም ጄኔራል ታሪኩ ወደ 7ኛ ክፍለ ጦር እንዲመለሱ ያስተላለፉትን የቴሌግራም ትእዛዝ ሆን ብለው መርሳታቸውን በመግለጽ ተቃውሞአቸውን አሰሙ።

ከጦር ፍርድ ቤቱ ቀርበው ቃላቸውን የሰጡት ሁለተኛው ምስክር ደግሞ፣ ቀደም ሲል ባሸበረቁ ቃላትና በደብዳቤዎች ጀ/ታሪኩን ሲያሞግሷቸው የነበሩት ብ/ጄኔራል ረጋሳ ጂማም፣

‹‹ከኮሎኔል ታሪኩ ዓይኔ የሚተላለፍልኝ ሪፖርት ሁሉ ከሽሬ እንዳሥላሴ የማዘዣ ቦታቸው ሆነው እንደሚያስተላልፉልኝ አድርጌ ነበር የምገምተው። በኋላ ግን ግዳጅ ሲፈነዳ የማዘዣ ቦታቸው ከአክሱም ሆኖ ነው ያገኘሁት።››

በማለት በእሳቸውና በሰሜን ዕዝ አዛዥ ውሳኔ፣ ቁጥርና ቀን በተሰጠው የቴሌግራም ትእዛዝ ጄኔራል ታሪኩ ወደ 7ኛ ክፍለ ጦር መመለሳቸውን እንደማያውቁ ካዱ።

በኮሎኔል መርዳሳ ሌሊሳ አመራርና ባልተጠና አካሄድ የተደረገው የሽራሮ አሰሳ ከባድ ጉዳት ባደረሰበት በዚያ ወቅት፣ ቁስለኞችን ለማንሳት መገኘት የነበረባት ሲሲና ሄሊኮፕተር ባለመገኘቷ በሕክምና ድጋፍ መትረፍ የሚችሉ ጀግኖች ሞተዋል። በዚህም ጄኔራል ታሪኩ ተጠያቂ በመሆናቸው እንዲፈረድባቸው የሚጠይቀው ሁለተኛ የክስ ጭብጥ ሆኖ የቀረበ ሌላው ክስ ነበር።





ይህን በተመለከተ 7ኛ የዐቃቤ ሕግ ምስክር ሆነው የቀረቡት የሄሊኮፕተሯ አብራሪ ሻምበል ግርማ ጫላ የሚከተለውን የምስክርነት ቃል ሰጥተዋል።

‹‹....የካቲት 18 ቀን 1973 ዓ.ም ወደ ሽራሮ ለጦሩ ቀለብ ሳመላልስ ውያለሁ። በዚህ ጊዜ የሄሊኮፕተሯ ጉልበት ደካማ መሆኑን ስለተገነዘብኩ በማግሥቱ የካቲት 19/73 ዓ.ም እስከ ጠዋቱ አራት ሰዓት ተኩል ድረስ ተሠርታ፣ የተፈለገውን ያህል ባትጠገንም የተቻላትን ያህል እንድትሠራ ለ501ኛ ግብረ ኃይል ዘመቻ መኰንን ሪፖርት አደረግሁ፣ ለእኔም ከኰሎኔል ታሪኩ ዓይኔ ጋር በአዲ ረመጽ በኩል አድርገን ወደ ጎንደር እንደምንሄድ ተነገረኝ። በዚሁ መሠረት ሽሬ አዲ ረመጽ የሚሄዱትን ወታደሮች አውርደን ከቀኑ 7 ሰዓት ከ20 ደቂቃ ላይ ጎንደር አዘዞ አየር ማረፊያ ደርሰን ለምሳ ተሠማራን።

‹‹ከቀኑ አስር ሰዓት ላይ ‹‹ኰሎኔል ታሪኩ ይፈልጉአችኋል...›› የሚል አስቸኳይ መልዕክት ደርሶን ቀረብን። እሳቸውም ‹‹አሁኑኑ ሽሬ እንድንሄድ ትእዛዝ መጥቷልና እንሂድ›› አሉን። እኔም የቀኑን የአየር ሁኔታ እንደማያመችና የሽሬ ተራራም በዝናብ የተሸፈነ መሆኑን በማታም ወደዚያ መብረር አደጋ እንደሚያደርስ በመጥቀስ ጥንቃቄ እንዲደረግ ሀሳቤን አቀረብኩ። ከዚያም በተጨማሪ ገና ነዳጅ ተሞልቶ እስክንነሳ ሰዓቱ እያለቀ እንደሚሄድ ለማስገንዘብ ሞከርኩ።

‹‹እሳቸው ግን እንሞክር ብለው ስላስገደዱኝ ወደ አዘዞ አየር ማረፊያ በፍጥነት ተጓዝን። ነዳጁ ቀጂው ተፈልጎ እስኪገኝና እስክንቀዳ ድረስ ሰዓቱ ከ11 አሩብ ጉዳይ ሆነ። እኔም ከ11 ሰዓት ተኩል በኋላ ማብረር እንደማንችል ከመ/ቤታችን የወጣ ቋሚ

መመሪያ መኖሩን በመግለጽ ከዚያ ሰዓት በኋላ እንደማላበር ነገርኳቸው። ኮሎኔል ታሪኩም በአጋጣሚው አዝነው፣ የጦሩን ሁኔታ በስልክ ለማጣራት የስልክ ፍሪኩዌንሲ ለማግኘት ትግል አደረጉ። ያም ሳይሳካላቸው ቀረ።

‹‹በማግስቱ ጠዋት የካቲት 20 ቀን 73 ዓ.ም ነዳጅ ስንሞላና ሞተር ስናሞቅ ቆይተን በ0800 ሰዓት መሬት ለቅቀን ወደ ሺሬ በረርን....›› በማለት የነበረውን ሁኔታ ሻምበል ግርማ ገለጡ።

በተጨማሪም፣ ‹‹ኮሎኔል ታሪኩ ሄሊኮፕተሯንና ሲሲና አውሮፕላኗን /ቁስለኞች ለማንሳት/ ከግዳጅ ላይ እንዳይውሉ ማድረጋቸውን ያውቃሉ?›› ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ የሰጡትም መልስ የሚከተለው ነበር።

‹‹አላውቅም። በ19/6/73 የአሰሳ ግዳጅ እንደነበረም ፍጹም የማውቀው ነገር የለም። በኮሎኔል ታሪኩ ሥር የሚታዘዙ ሁለት አውሮፕላኖች ነበሩ። አንዱዋ የ50 ሰዓት ፍተሻ ጊዜ ስለደረሰባት በ17/6/73 ዓ.ም ወደ አሥመራ ተመልሳለች። ሁለተኛዋ ግን እኔ የያዝኳት ሄሊኮፕተር ነች...... ከ11 ሰዓት ተኩል በኋላ እንዳንበር በጽሑፍ የታዘዘ ትዕዛዝ አለን። ይህም ትዕዛዝ እኔ ማብረር ከጀመርኩበት ጊዜ ጀምሮ ያለ ነው።›› በማለት አብራሪው ምስክርነታቸውን ሰጡ።

ይህ የምስክርነት ቃል፣ ሄሊኮፕተሯና ሲሲናዋ የካቲት 19 ቀን 73 ዓ.ም ግዳጅ ላይ እንዳይውሉ ኮሎኔል ታሪኩ አግደዋል ተብሎ የቀረበውን ክስ ውድቅ በማድረግ፣ እነ ጀኔራል ረጋሣ ለጥፋታቸው ግርዶሽ ያዘጋጁት ተራ ምክንያት መሆኑን በማጋለጥ ተከሳሹ ጀኔራል ታሪኩ በነፃ እንዲለቀቁ በቂ ጭብጥ ሆኗል።





በዚህና በሌሎች ምስክሮችም ቃል እንዲሁም የሂደቱን ምስጢራዊ ተልዕኮና ምክንያት፣ ወታደራዊ በሆነ መስፈርትና ምዘና ፍርድ ቤቱ እንዲያጤነው የጠየቁት የሕግ ሰው ኮሎኔል ታምራት ጉበዜ የሚከተለውን ማጠቃለያና አቤቱታ በጽሑፍ አቅርበው ነበር።

‹‹......ስለዚህ የሽራሮ አሰሳ በሕሊናዬ ሳየውና ሳስበው፣ ውጤቱ እንዲሰምር ያልተፈለገበት ስውር የሆነ ደባ እንደነበረበት ነው እንጂ፣ እንዲሁ ተከሣሹን ለመጉዳት ብቻ ሆን ብሎ የተፈጠረ ደባ ብቻ አይደለም። ይሁንና ክቡር ፍርድ ቤቱን የማሳስበው በእውነቱ ከሆነ ለሽራሮ አሰሳ ጥፋት የሄሊኮፕተሯ አለመገኘት ነው ወይስ የኦፕሬሺኑ በትክክል አለመመራት? ይህንን ሚዛናዊ ምርመራ ለፍርድ ቤቱ እተዋለሁ።

‹‹...............ያም ሆነ ይህ፣ በተከሣሹ ላይ እንደ ክሱ አቀራረብ ያልተመሰከረባቸው ስለሆነ፣ በወ.መ.ሥ.ሥ. ቁጥር 141 መሠረት በነፃ እንዲለቀቁ በትህትና አመለክታለሁ።›› በማለት ታህሣሥ 16 ቀን 1974 ዓ.ም በተጻፈ የመቃወሚያ ደብዳቤ ኮሎኔል ታምራት ጎበዜ፣ የጦር ፍርድ ቤቱ ጀኔራል ታሪኩን በነፃ እንዲያሰናብታቸው ጠይቀዋል። በዚሁ መሠረት የወረዳው የጦር ፍርድ ቤት ጉዳዩን በጥልቀት መርምሮ ጀኔራሉን ከወንጀሉ ነፃ በማድረግ አሰናብቶአቸዋል።

ጥቂት የማይባሉ ሰዎች መከሰሳቸውን እንጂ የክሱን ጭብጥና ምክንያት እንዲሁም የፍርዱን ውሳኔ ያላገናዘበ ታሪክ፣ ‹ለግል ጉዳያቸው ሄሊኮፕተር ተጠቅመዋል፣.....› ብለው ጽፈዋል። ይህም የተዛባ መረጃ እንደሚያስተላልፍና የጀኔራሉንም ድካም፣ ክብርና ሰብዕና የሚያጉድፍ እንደሚሆን መገመት አያስቸግርም። ከዚህም ጋር አንዳንድ ፀሐፊዎች በድፍኑ፣ ጀ/ል ታሪኩ ከአመራር

አባላት ጋር አለመግባባት ይፈጥራሉ፣ለሥነ ሥርዓት የማይገዙና አለቆቻቸውን የሚንቁ ናቸው፣.......ወዘተ፣ በማለት ጽፈዋል።


ጄኔራል ታሪኩ ተከሰውበት ስለነበረው ስለ ሄሊኮፕተር ጉዳይ በተመለከተ በአሁኑ ወቅት በሕይወት ያሉትና ያለፈውን የእርስ በርስ ጦርነት ታሪክ «ዕጣ ፈንታ እና መስዋዕትነት» በሚል ርዕስ በመጽሐፍ አዘጋጅተው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያስነበቡት ብ/ጄኔራል ዋስ ይሁን ንጋቱ፣ ከገጽ 112 ጀምሮ ባሰፈሩት ታሪክ፣

«የታሰርኩት ኰሎኔል ታሪኩ ዓይኔ በወቅቱ ታስረው ይገኙበት በነበረው አንድ ክፍል ውስጥ ነበር። ኰሎኔል ታሪኩ በ1973 ዓ.ም በትግራይ ክ/ሀገር በሽሬ ኦፕሬሽን ዘመቻ ለቁስለኛ ማንሺያ ሄሊኮፕተር ባለመላካቸው ሊድኑ ይችሉ የነበሩ ቁስለኛ ወታደሮች ሞተዋል በሚል ሰበብ ተወንጅለው ነበር የታሰሩት። ኰሎኔሉ እንደነገሩኝ ከሆነ ግን፣ የሽሬን ግንባር በወቅቱ ለሌ/ኰሎኔል መርዳሳ ሌሊሳ ካስረከቡና ወደ ጎንደር ከተመለሱ በኋላ፣ ሌ/ኰሎኔል መርዳሳ በዕለቱ በሕወሃት ላይ ጥቃት ይሰነዝራሉ።በውጊያው በርካታ ወታደሮች ሲሞቱ ብዙዎችም ቆስለው ነበር።»

«ይሄን ጊዜ ነው ሌ/ኰሎኔል መርዳሳ ከጎንደር ሄሊኮፕተር እንዲላክላቸው የጠየቁት። ኰሎኔል ታሪኩም ፓይለቶች እንዲሄዱ ትዕዛዝ ይሰጣሉ። ፓይለቶች ግን በበረራ መመሪያችን መሠረት ከ11 ሰዓት በኋላ መብረር አንችልም ይሉና ሳይበሩ ይቀራሉ። እናም መቀሌና ጎንደር ተወስደው መታከም ይችሉ የነበሩ ወታደሮች በሄሊኮፕተር እጦት ይሞታሉ። በዚህ ምክንያትና የቆየ ቁርሾ ታክሎበት ኰሎኔል ታሪኩ ዓይኔ ለመታሰር በቁ።»







«ኰሎኔሉ በመጨረሻ ጉዳያቸው በወረዳ የጦር ምርመራ (Court of Inquiry) ታይቶ፣ከወንጀሉ ነፃ ሆነው ከተፈቱ በኋላ በአዋሳ የደቡብ ዕዝ ምክትል አዛዥ ተደርገው ተመድበው ነበር። የማታ ማታ ግን፣ በዘመናዊ ወታደራዊ ሳይንስ የተካኑትና የኤርትራና የኦጋዴን ጀግና የነበሩት፣ "ጀግናው ብ/ጄኔራል ታሪኩ ዓይኔ በአምባገነኑ የደርግ "መንግሥት" ግብታዊ ትዕዛዝ፣ በአሥመራ ከተማ በአሳዛኝ ሁኔታ በጦሩ ፊት ተረሸኑ፣ ያለፍርድ።»

አባላት ጋር አለመግባባት ይፈጥራሉ፣ለሥነ ሥርዓት የማይገዙና አለቆቻቸውን የሚንቁ ናቸው፣.......ወዘተ፣ በማለት ጽፈዋል።


ጄኔራል ታሪኩ ተከሰውበት ስለነበረው ስለ ሄሊኮፕተር ጉዳይ በተመለከተ በአሁኑ ወቅት በሕይወት ያሉትና ያለፈውን የእርስ በርስ ጦርነት ታሪክ ‹‹ዕጣ ፈንታ እና መስዋዕትነት›› በሚል ርዕስ በመጽሐፍ አዘጋጅተው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያስነበቡት ብ/ጄኔራል ዋስ ይሁን ንጋቱ፣ ከገጽ 112 ጀምሮ ባሰፈሩት ታሪክ፣

‹‹የታሰርኩት ኮሎኔል ታሪኩ ዓይኔ በወቅቱ ታስረው ይገኙበት በነበረው አንድ ክፍል ውስጥ ነበር። ኮሎኔል ታሪኩ በ1973 ዓ.ም በትግራይ ክ/ሀገር በሽሬ ኦፕሬሽን ዘመቻ ለቁስለኛ ማንሺያ ሄሊኮፕተር ባለመላካቸው ሊድኑ ይችሉ የነበሩ ቁስለኛ ወታደሮች ሞተዋል በሚል ሰበብ ተወንጅለው ነበር የታሰሩት። ኮሎኔሉ እንደነገሩኝ ከሆነ ግን፣ የሽሬን ግንባር በወቅቱ ለሌ/ኮሎኔል መርዳሳ ሌሊሳ ካስረከቡና ወደ ጎንደር ከተመለሱ በኋላ፣ ሌ/ኮሎኔል መርዳሳ በዕለቱ በሕወሃት ላይ ጥቃት ይሰነዝራሉ።በውጊያው በርካታ ወታደሮች ሲሞቱ ብዙዎችም ቆስለው ነበር።››

‹‹ይሄን ጊዜ ነው ሌ/ኮሎኔል መርዳሳ ከጎንደር ሄሊኮፕተር እንዲላክላቸው የጠየቁት። ኮሎኔል ታሪኩም ፓይለቶች እንዲሄዱ ትዕዛዝ ይሰጣሉ። ፓይለቶች ግን በበረራ መመሪያችን መሠረት ከ11 ሰዓት በኋላ መብረር አንችልም ይሉና ሳይበሩ ይቀራሉ። እናም መቀሌና ጎንደር ተወስደው መታከም ይችሉ የነበሩ ወታደሮች በሄሊኮፕተር እጦት ይሞታሉ። በዚህ ምክንያትና የቆየ ቁርሾ ታክሎበት ኮሎኔል ታሪኩ ዓይኔ ለመታሰር በቁ።››






ከተከበሸ ተከሳከይ የቀረቡት ምስክሮች በሰጡት ቃል ማንኛውም በራሺት በመግባባትና በጓደኝነት ላይ የተመሰረተ እንደሆነ ገልጸውታል ::

"ስለዚህ የሺራር አበባ በሕሊናዬ ባየሁና በሰበው ውጤት እንኳሆር ያልተወሰገበት ስውር የሆነ ደባ እንደነበረበት ነው ለኔ እንዲሁ ተከሣሹን ብቻ ለመጉዳት ሆነ ብሎ የተፈጠረ ደባ አይደለም":: ይሁንና ከጦር ፍ/ቤቱን የማበሰበው በእውነቱ ከሆነ ለሺራር አበባ ጥፋት "የሄሊኮብተሩ አለመገኘት ነው ወይስ አተረሸኑ በትክክል አለመራት" ይህንን ለፍርድ ቤቱ አተዋለሁ ::

የሰሜን እዝ የዘመቻ መኮንን ሌ/ኮሎኔል ታደሰ ተሰማ የሺራር አበባ ዘመቻ ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ አራበቸውም ሆነ አረዳታቸው በተከሳሹ ማዘዣ በታ አከሎም እየተገኙ የተደረጉትን ሆነ ወደፊት ሊፈጸሙ የሚገባቸውን እቅዶች እየተመለከቱ ወቅታዊ ዘገባውን ለእዙ ጥበቅ አዛዥ ለማበየት ይዘው እየሄዱ በበረበት የቆዩትን የ19—6—73 ዓ.ም ውጊያ ከተፈጠረ በኋላ በተከሳሹ የወጣውን አቻሁና የማዘዣውን በታ አከሎም መሆኑን የማያውቁ ሆነው መታየታቸው በጣም የሚያስገርም ነው :: ልገረምም የቻሉት ከዓቃቢ ሕግ ምስክሮችና ከመከላከያ ማስፈቻዎች በወሰጹሩት ዘገባ ሲሆን ሌሎ ታደሰ ተሰማ የተከሳሹ የማዘዣ በታ አከሎም መሆኑንና እቅዱንም ደህና አድርገው የሚያውቁት መሆናቸውን በመስከሩ በማዩቴ ነው ::

በሌላው በኩል ደግሞ የኔ የተከሳኪ መኮንን ቅሬታ በመከላከያነት የተቀጠሩት የተከሣሹ መኮንኑ የዘመቻ መኮንንና የመረጃው መኮንን እንዲሁም የ1ኛ መምሪያና በ4ኛ መምሪያነት በታ የሚቢሩት የመ.አ ኃይሉ ንጉ የወ.ሥ.ሥ ቁ 142 በሚያዘው መሠረት አጠር ፍ/ቡቱ ላይ ቀርበው ምስክርነቷ ቃላቸውን ቢሰጡላቸው ኖሮ ለፍ/ቤቱ የበለጠ መንደርደሪያና የፍርዱ ሐሳብ ማግኛ ለተከሳሹም ከተመሰረተባቸው የወንጀል ክስ መዳኛ ይሆን ነበር:: የ40 ቀን ጊዜ ቢሰጥ ኖሮ 3ቱም የመከላከያ ምስክሮች አዲስ አበባ ተገኝተው የሚፈለገባቸውን የመከላከያ ምስክርነት ለመስጠት ቢችሉ 40 ቀን ዱረስ ልንቆይ ስለማንችል በተሰማው ማስረጃ ብቻ ውሳኔ እንሰጣለን በማለቱ ነው:: ያም ሆነ ይህ በተከሳሹ ላይ እንደ ክሱ አቀራረብ ያልተመሰከረባቸው ስለሆነ በወ.መ.ሥ.ሥ ቁ 141 መሠረት በነጻ እንዲለቀቁ በትህትና አመለከታለሁ:: ===============================

" የኢ.ሰ.ፓ.አ.ኮ ተልዕኮ ይሳካል "
" በመራራው ትግላችን እናሸንፋለን "

የተከበሸተከሳከይ መኮንን

ኮሎኔል
ታምራት ገበዜ

‹‹ኮሎኔሉ በመጨረሻ ጉዳያቸው በወረዳ የጦር ምርመራ (Court of Inquiry) ታይቶ፣ከወንጀሉ ነፃ ሆነው ከተፈቱ በኋላ በአዋሳ የደቡብ ዕዝ ምክትል አዛዥ ተደርገው ተመድበው ነበር። የማታ ማታ ግን፣ በዘመናዊ ወታደራዊ ሳይንስ የተካኑትና የኤርትራና የኦጋዴን ጀግና የነበሩት፣ ጀግናው ብ/ጄኔራል ታሪኩ ዓይኔ በአምባገነኑ የደርግ መንግሥት ግብታዊ ትዕዛዝ፣ በአሥመራ ከተማ በአሳዛኝ ሁኔታ በጦሩ ፊት ተረሸኑ፣ ያለፍርድ።››

‹‹የደርግ መንግሥት እዚች አገር ላይ ጥሎት ካለፈው እጅግ በጣም አሳዛኝና አሳፋሪ ድርጊቶች አንዱ፣ አገራቸውን በቅንነትና በታማኝነት ያገለገሉ፣ እንደ ብ/ጀኔራል ታሪኩ ዓይኔና ኰሎኔል ውብሸት ማሞ የመሳሰሉ ጀግኖችን ያለ በቂ ምክንያት መግደሉ ነው፡፡

‹‹...........ለአመኑበት ዓላማ ፈጽሞ ወደ ኋላ ከማይሉት፣ አገርና ወገን ወዳድ ከሆኑት ልበ ሙሉ ጀግናው ጀኔራል ታሪኩ ዓይኔ ጋር በምድር ጦር ወታደራዊ እስር ቤት በአንድ ክፍል ውስጥ ሁለታችን ለሦስት ወራት አብረን ታስረን፣ በብስጭት የተነሣ ምግብ ይመገቡ የነበረው በቀን አንድ ጊዜ ብቻ፣ በዘጠኝ ሰዓት ነበር፡፡ ኰሎኔል ታሪኩ ያለ ጥፋታቸወ በእስር እየማቀቁ በነበረበት ጊዜ፣ ለአገራቱና ለሠራዊቱ መልካም ጊዜ እንዲመጣ ይመኙ እንደነበር አስታውሳለሁ፡፡›› በማለት ሕያው ምስክርነታቸውን ለታሪክ አስቀምጠዋል፡፡

*(ገጽ 112 እስከ 113)*

በሌላም በኩል፣ በጀኔራል ታሪኩና በጀኔራል ረጋሣ መካከል ስለነበረው ቅራኔ በተመለከተ በደኅንነት ሥራቸው ፀባይ የነበረውን ሻካራ ግንኙነት በሚገባ የሚያውቁትና ሕያው ምስክር ሆነው ቃላቸውን የሰጡት መቶ አለቃ ታደሰ ቴሌ፣ የብ/ጀኔራል ረጋሣ ጂማ ጥላቻና የበቀል እርምጃ የጠነከረበትን ምክንያት ለመጠቆም በሰጡት ቃለ ምልልስ ላይ ያስገነዘቡት ምክንያት የሚከተለው ነበር፡፡

‹‹.......... በኤርትራ ሣህል አውራጃ ወታደራዊ ችግሮች ስለነበሩ መንግሥቱ ‹ማነው ጥራት ያለው ጀኔራል.... ይህን መምራት የሚችል› ብለው ለማጣራትና ለመመደብ ኰ/መንግሥቱ አዛዦችን ሰብስበው ባነጋገሩበት ስብሰባ ላይ የተጠቆሙት አንዱ፣ ረጋሣ ጂማ ነበሩ፡፡





‹‹በዚህ ጊዜ መንግሥቱ፣..... ረጋሣ ጂማ ሙስናና ሴት ወዳድ ናቸው አይሾሙም በማለት ጥቆማውን ውድቅ አደረጉት፡፡

ቀጥሎም፣ጀኔራል ውበቱ ፀጋዬ ተጠቆሙ፣እሳቸ ውንም፣‹‹...... የባሰ ውድቀት ያመጣል እንጂ ወታደራዊ ብስለት የለውም፣ ብለው መንግሥቱ ውድቅ አደረጉ፡፡ ከዚያም ጀኔራል ተመስገን ገመቹ ይሁኑ የሚል ሀሳብ ቀረበ፡፡ እሳቸውንም በአየር ወለድ ብቃታቸው ከዚህ በፊት ባሳዩት ልምድ አየር ወለዱን ቢመሩልኝ ይሻላል በማለት መንግሥቱ ሳይቀበሉ ቀሩ፡፡

‹‹በመጨረሻም እናንተ ማቅረብ ካልቻላችሁ እኔ ላቅርብ በማለት ጀኔራል ታሪኩን ለናደው ዕዝ አዛዥነት የመለመሉት ኰሎኔል መንግሥቱ ኃ/ማርያም ናቸው፡፡ በወቅቱ የኢፌዲሪ ኘሬዚዳንት ነበሩ፡፡

ታሪኩ ወደ ናደው ዕዝ በሄዱበት ወቅት እንዲህ ዓይነቱ እሳት ውስጥ ነበር የገቡት፡፡›› ሲሉ ያንን የሥልጣን ሽኩቻ ዘመን አሳይተዋል፡፡ ቀጥለውም፣

‹‹ጀኔራል ታሪኩ የናደው ዕዝ አዛዥ ሆነው ተሾመው እንደተመደቡና ሥራ እንደጀመሩ ሦስት ችግሮች በአንድ ጊዜ ተፈጠሩ፡፡

1ኛ/ በክቡር ዘበኛና በጦር ሠራዊት መኰንኖች መካከል የመናናቅ የጨለ ፍጥጫ ተጀመረ፡፡

2ኛ/ የኤርትራ ወታደራዊ ጉዳይ ከነበረበት ተንጠራርቶ ከፍተኛ ደረጃ ደርሶ ነበር፣'

3ኛ/ ሲቪልና ወታደራዊ ባለሥልጣኖች የሥልጣን ሽኩቻ፣ የኢሠፖና የካድሬዎች መዝረክረክ፣ እርስ በርስ የሥልጣን ሽሚያ ትልቅ አደጋ እያስከተለ ነበር።›› በማለት የነበረውን የጊዜውን ሁኔታ ገልጸዋል።

ለብ/ጄኔራል ታሪኩ መገፋትና ለግፍ ፍፃሜ መዳረግ ምክንያት ሆነው ከታዩት በርካታ የተጠራቀሙ ሁኔታዎች መካከል ላቅ ብሎ የሚታየው ጥርጣሬና ሥጋት የቋጠረው የወታደራዊው መሪ የኰሎኔል መንግሥቱ ጥላቻና ቂም እንደነበረ የታሪክ ፀሐፍት አስረድተዋል። ይህንን በተመለከተ ኰሎኔል አምሳሉ ገብረዝጊ እንደ ማስረጃ ያቀረቡት ጭብጥ የሚከተለው ነው።

‹‹ብ/ጄኔራል ታሪኩ ዓይኔና ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃ/ማርያም በሚገባ የሚተዋወቁ ሰዎች ናቸው። መንግሥቱ የደርግ ሊቀ መንበር ከመሆናቸው በፊት በምሥራቅ ኦጋዴን፣ በ3ኛ ክ/ጦር ውስጥ አብረው ሠርተዋል። የትምህርት ደረጃ ልዩነትም ነበራቸው።

ብ/ጄኔራል ታሪኩ ዓይኔ መሥመራዊ መኰንንም ሆነው በኃይለኛነታቸው እንጂ በሰካራምነትም ሆነ በሌላ መጥፎ ባህርይ አይታወቁም።›› በማለት ከገለጹ በኋላ ሁለቱ መኰንኖች በነበሩበት ምሥራቅ ኦጋዴን የጄኔራል ታሪኩ 2ኛ ሚስት ይዞታ በነበረው ቡና ቤት በርካታ ምሽቶችን አብረው አሳልፈዋል። መኰንኖቹ በኑሮ ደረጃ፣ በባህሪም ልዩነት ነበራቸው። በሚገባ ቢተዋወቁም የቀረበ ጓዳዊ ግንኙነት አልነበራቸውም።

በመጨረሻም በአብዮቱ ዘመን በተፈጠረው አዲስ የታሪክ ሂደት መንግሥቱ አዛዥ ታሪኩ ታዛዥ ሆነው ወታደራዊ ጉዞአቸውን





ቀጠሉ በማለት ስለትውውቃቸው መሠረታዊ ነጥቦችን አሳይተዋል። ኰሎኔል አምሳሉ በመቀጠልም፣

‹‹በ1973 ዓ.ም ቤተ መንግሥት ውስጥ ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃ/ማርያም የመሩት አንድ ወታደራዊ ስብሰባ ነበር።......የስብሰባው ዓላማ የኤርትራን ጉዳይ ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እልባት ለማበጀት አንድ ሁለገብ ዘመቻ እንደሚያስፈልግና መዋቅር ተዘርግቶ ቅድመ ዝግጅት ለማድረግ ነበር።..አብዛኛዎቹ ጄኔራሎች ሊ/መ መንግሥቱን በመደገፍ ዘመቻው ኤርትራ ላይ እንዲያተኩር ስምምነት ላይ እየደረሱ ነበር።››

‹‹በዚህ መካከል ብ/ጄኔራል ታሪኩ ዓይኔ ‹‹ሀሣብ አለኝ›› በማለታቸው እንዲናገሩ ከሰብሳቢው ተፈቀደላቸው። ‹‹ዘመቻው ከኤርትራ ይልቅ የላቀ ውጤት የሚኖረው በቅድሚያ በትግራይ ተጀምሮ ሕውሃትን ሙሉ ለሙሉ የደመሰሰ እንደሆነ ነው።›› በማለት አቋም ይዘው፣ አስረግጠው በመናገርና ምክንያቶቻቸውን በማስረዳት ላይ ሳሉ ሰብሳቢው ጣልቃ ገቡ። ‹‹ታሪኩ ዝም በል፣ የማታውቀውን ነገር ነው የምትናገረው፣ ሕውሃት የትም የሚደርስ ድርጅት አይደለም። ዋነኛ ጠላታችን ሻዕቢያ ነው፣ በቅድሚያ መደምሰስ ያለበትም ሻዕቢያ ነው።›› አሉ።

ብ/ጄ ታሪኩም ነገሩን እርግፍ አድርገው ተውት።እንግዲህ በወቅቱ ተሰብስበው የነበሩት መኰንኖች ሁሉ የሊቀ መንበሩን ሀሳብና እቅድ በሙሉ ይሁንታ በተቀበሉበት ሁኔታ ውስጥ የጄኔራል ታሪኩ የተለየ ሀሳብና መሠረታዊ እውነት የጨበጠ አስተያየት መሰንዘር ለኰሎኔል መንግሥቱ ንቀት መስሎ ታይቷቸዋል። ይህ አጋጣሚ፣ አንድ ቂም የሚያስይዝ ኒጥብ ተደርጎ በመንግሥቱ አዕምሮ ተመዝግቧል። በዚህም ምክንያት በብዙ አውደ ውጊያዎች አኩሪ

ውጤት ያስመዘገቡት ብ/ጀኔራል ታሪኩ ዓይኔ በቀይ ኮከብ ዘመቻ እንዳይሣተፉና በደቡብ ዕዝ ም/አዛዥነት እንዲቆዩ ተደርጓል።›› በማለት ኰሎኔል አምሳሉ በሕያው እማኝነት ያዩትንና የሰሙትን የሊቀ መንበሩን የጥላቻና የቂም መሠረት የሆነውን ጉዳይ ጽፈዋል።

በጦር ሜዳ ግዳጅ ላይ በተለያየ የጦር ግንባር በአዛዥነት ተሰልፈው ይሠሩ የነበሩትን መኰንኖች የደርግ መንግሥት ሆን ብሎ እርስ በእርስ እንዳይስማሙ በማናከስ አለያይቶአቸው እንደነበረ የታሪኩ ባለቤቶችና የፍልሚያው ተሳታፊ ፀሐፊዎች ጽፈዋል።

ይህ የመከፋፈልና የማናከስ ሁኔታ ደግሞ ከፍርሃትና ከሥጋት የመነጨ የኰ/ መንግሥቱ ኃ/ማርያም ጭንቀት ነበር። መኰንኖቹ ከተስማሙና በመካከላቸው ሰላም ከነገሰ ሕገ ወጡን መንግሥት ለመንቀል እንደማይሳናቸው ስለሚታወቅ ከሥልጣን ሳለመውረድና ሳለመፈንቀል የተደረገ መሠሪ ስልት እንደነበር መገመት አያስቸግርም።

በዚሁ መሠረት፣ ሜ/ጀኔራል ረጋሣ ጂማ ጀ/ታሪኩን ባሞገሱበት አፋቸው እንደገና ወንጅለው ካሳሰሩአቸውና ክሳቸው ውድቅ ሆኖ ጀ/ታሪኩ ነፃ ወጥተው ደባውን የሠሩት ከፍተኛ መኰንኖች ትዝብት ላይ ከወደቁ በኋላ ከባድ መቃቃር ተፈጥሯል። ይህ ከሆነ በኋላ፣ ጀኔራል ታሪኩን በጀኔራል ረጋሣ አዛዥነት በነበረ ግብረ ኃይል ሥር እንዲያገለግሉ መመደቡ ይበልጥ በደል እንዲደርስባቸውና ፀቡና ቅራኔው እንዲፋፋም ታቅዶ የተደረገ እንደነበር ለማንም ግልጽ ይመስላል።

ጀኔራል ታሪኩ በነበራቸው የሠራዊት አመራር ኃላፊነት ውስጥ ሌሎች ተቃራኒና ተቃዋሚ ክፍሎች እንደነበሩባቸው የገለጹት





ኰሎኔል አምሳሉ፣ ጀኔራል ታሪኩ ሁሉንም እንደ ሥራውና እንደውጤቱ በአግባቡ ከመቀበል ባሻገር አድር ባይነትና የመለማመጥ ባህርይ እንዳልነበራቸው፣ እንዲሁም የወታደራዊ ሙያ እውቀትና ብቃት ሳልነበራቸው ለደርግ የፖለቲካ ሹመኞች በፍርሃት ባለመታዘዛቸውና የተለየ የመሽቆጥቆጥ አቀራረብ ባለማድረጋቸው፣ በዚህም በሻለቃ መላኩ ተፈራና በካሣዬ አራጋው የጥላቻ ጥርሶች በቂም ተወግተውበታል። ይህንን በተመለከተ በመጽሐፋቸው ገጽ 155 ላይ፣

‹‹.......ብ/ጀኔራል ታሪኩ ዓይኔ አጠገባቸው የነበሩትን የፖለቲካና የወታደራዊ ደኅንነት ኃላፊዎች እንደሌሎች አዛዦች የተለየ እንክብካቤ አያደርጉላቸውም ነበር። ሁሉም በመስመሩና በሥርዓቱ እንዲካሄድ አመራር ይሰጡ ነበር። በዚህም አጠገባቸው ያሉት ሰዎች ወደ ላይ ሪፖርት ያደርጉ ነበር። አሥመራ የሚገኙት የነዚህ አለቆችም ይኼንን በማስተጋባት የአምባገነንነት ስም ለጠፉባቸው።›› በማለት ኰሎኔል አምሳሉ ገልፀዋል።

በዘመነ ደርግ የፖለቲካ ባለሥልጣናት ወታደራዊ ተቋማትን ጭምር ለማዘዝና ቢቻላቸው አመራር ለመስጠት ይጥሩ እንደነበረ ብዙዎች የታሪክ ፀሐፊዎች ገልጠዋል። ይህንን ሁኔታ በተመለከተ በጎንደር የ7ኛ ክፍለ ጦር ዋና አዛዥ በነበሩት በጀኔራል ታሪኩና በጎንደር ኢሠፓ ዋና ፀሐፊ ሻለቃ መላኩ ተፈራ መካከል የነበረውን ፍጥጫና የከረረ ቅራኔ ሻለቃ ንጋቱ ቦጋለ በ‹‹ትውልድ ያናወጠ ጦርነት›› መጽሐፋቸው ገጽ 82 ላይ እንደሚከተለው ገልፀውታል።

‹‹ጀ/ታሪኩ የኢሠፓ አባል ቢሆኑም እንደ ኢሠፓ የሚጠሉት ፓርቲ ግን አልነበረም። አብዛኞቹን የፖርቲ መሪዎች

ጠንቅቀው የሚያውቋቸው በመሆኑ በእነርሱ አመራር መልካም ነገር ይኖራል ብለው አይጠብቁም።

‹‹.......በ1979 ዓ.ም ሕዝባዊ ሸንጎ ምርጫ ሲካሄድ፣ አጋሜ አውራጃን ወክለው እንዲወዳደሩ ተብሎ ስለተነገራቸው፣ ምርጫው ከመካሄዱ በፊት ቢያንስ ሁለት ቀናት ቀደም ብለው በሥፍራው በመገኘት ለሕዝቡ ንግግር ማድረግ ነበረባቸው። በወቅቱ አዲስ አበባ ስለነበሩ ይኸው ተነግሮአቸው በሥፍራው እንደገኙ ቢጠየቁ፣ ‹የአዲግራት ሕዝብ እኔን የት ያውቀኛል፣ እንዲህ ያለ ቀልድ ውስጥ ለመገኘት ፈቃደኛ አይደለሁም...› በማለት ሳይገኙ የቀሩ ሲሆን፣ በሌሉበት ተመርጠው የሕዝብ ሸንጎ አባል ተደርገዋል።››

‹‹........ በየክፍለ ሀገራቱ ፖርቲ ኮሚቴዎች ስብሰባ ለምን መሣተፍ እንደማይፈልጉ በዕዙ ፖለቲካ መምሪያ ተጠይቀው፣ ‹ጦሩ ውስጥ የፖርቲ ኮሚቴ ስላለ ሲቪሉ ውስጥ ልሣተፍ ፍቃደኛ አይደለሁም። ከሁሉም በላይ የፖርቲ ፀሐፊዎች ጦሩን ለማዘዝ ስለሚፈልጉ፣ ከእነርሱ የሚያገናኘኝ የዕዝ ሠንሰለት ስለሌለኝ፣ ልታዘዛቸው ፈቃደኛ አይደለሁም።› የሚል መልስ ሰጥተውን ነበር።››

‹‹የጎንደር ክፍለ ሀገር ፖርቲ ኮሚቴ ፀሐፊ የነበሩት መላኩ ተፈራም በክልላቸው የነበረውን 7ኛ ክፍለ ጦር ለማዘዝ ስለሚፈልጉ ጄኔራል ታሪኩ ፈቃደኛ አልነበሩም።..........መላኩ ተፈራም በዚህ በጄኔራሉ እምቢተኝነት በመበሳጨት በየወቅቱ አሉታዊ አስተያየታ ቸውን ለበላይ ሪፖርት በማቅረብ ሲወነጅሏቸው ቆይተዋል።›





ከጎንደር ክፍለ ሀገር ፖርቲ ኮሚቴ ጋር የነበረውን የከረረ ቅራኔ ለማስረዳት በአንድ ወቅት የተከሰተውን ሁኔታ ሻለቃ ንጋቱ በጋለ እንደ ማስረጃ ያቀረቡት እንደሚከተለው ነበር።

‹‹ ጥቂት መኰንኖች ከአዘዞ የጦር ካምፕ ወጥተው ለመዝናናት ጎንደር ከተማ ይገባሉ። ሲዝናኑ ያመሹት መኰንኖች በመጠጥ ኃይል ተገፋፍተው በመዝናኛ ሥፍራ ላይ ረብሻ ይፈጠራል። ፖሊስ ደርሶ በቁጥጥር ሥር ሊያደርጋቸው ቢሞክር መሣሪያ በመማዘዛቸው ማንነታቸው ብቻ ከተመዘገበ በኋላ ፖሊስ ሁኔታውን ለበላይ ያሳውቃል።

‹‹በተከታዮቹ ቀናት፣ ረብሻ ፈጥረዋል፣ ንብረት ላይ ጉዳት አድርሰዋል የተባሉት መኰንኖች ወደ ሕግ ፊት እንዲቀርቡ ክፍለ ጦሩ አሳልፎ እንዲሰጣቸው መጻጻፍ ቢደረግም ምላሽ ባለመገኘቱ፣ ሁኔታው ለክልሉ ፖርቲ ፀሐፊ ለጓድ መላኩ ተፈራ ይነገራል። እሳቸውም፣ለክፍለ ጦሩ አዛዥ ስልክ በመደወል፣አጃቢዎቻቸውን ስለሚልኩ ረብሻ አነሳሾቹ መኰንኖች እንዲሳኩላቸው ያዛሉ።

‹‹የክፍለ ጦሩ አዛዥም ሁኔታውን ለዕዙ ዋና አዛዥ ለጀ/ታሪኩ ሪፖርት ባደረጉበት ወቅት አንድም መኰንን ወይም ወታደር ተላልፎ እንዳይሰጥና አጃቢዎች የተባሉትም ጦር ካምፕ ግቢ እንዳይደርሱ ጥብቅ ትእዛዝ ይሰጣቸዋል። የክፍለ ጦሩ አዛዥም ይህንኑ ውሳኔ ለሻለቃ መላኩ በመግለጽ ለመላክ ፈቃደኛ አለመሆናቸውን ያሳውቃሉ።

‹‹ትእዛዜ ተጣሰ፣ ክብሬ ተደፈረ፣ ፖርቲው ተናቀ፣ ብለው የተናደዱት መላኩ መኪናቸውን አስነስተው፣ አጃቢ አስከትለው ወደ ክፍለ ጦሩ መምሪያ ይከንፋሉ። ጓድ መላኩን የማያውቅ ወታደር

አልነበረምና፣ ለወትሮው ሲመጡ፣ የብረት ሰላምታ ሰጥተው፣ በር የሚከፍቱላቸው ወታደሮች በተለመደው ሁኔታ ሳይቀበሏቸው ቀሩ።

በሩ እንዲከፈትላቸው ቢጠይቁና አጃቢዎቻቸውም ወርደው ቢንገራደዱ ምላሹ ያልተለመደ ሆነባቸው። ማንንም እንዳናስገባ መመሪያ ተሰጥቶናል ጌታዬ ይመለሱ፣ የሚል ነበር።

‹‹በተሰጣቸው መልስ እጅግ የተናደዱት ጓድ መላኩ ትእዛዙን የሰጠው ማነው ብለው አፈጠጡ። የክፍለ ጦሩ አዛዥ በተዋረድና የዕዙ አዛዥ ጄኔራል ታሪኩ መሆናቸው ተነገራቸው። ከመመለስ ውጭ ምርጫ ያልነበራቸው ሻለቃ መላኩ ሁኔታውን ለበላይ ሪፖርት በማቅረብ፣ ፓርቲው በጀ/ታሪኩ መደፈሩንና የዲሲፕሊን እርምጃ ካልተወሰደ በስተቀር አዝማማያው አደገኛ ሊሆን እንደሚችል በሪፖርታቸው ገልጸዋል።›› በማለት የሥልጣን ሽኩቻውን ክረት አሳይተዋል።

ከላይ የተጠቀሰውን ፍጥጫና ሂደት በተመለከተ ሻለቃ ንጋቱ ቦጋለ ሚዛናዊ አስተያየታቸውን ባሰፈሩበት ጽሑፍ፣

‹‹ጄኔራል ታሪኩ ዓይኔ ከፓርቲ ባለሥልጣኖች ጋር የተቃረኑትን ያህል በተቃራኒው በሁለቱም ክፍለ ሀገራት፣ ከጎንደርና ከትግራይ ከነበሩት የመንግሥት ተቋማት መሪዎችና ከሕዝቡ ጋር መልካም ግንኙነት ነበራቸው።

‹‹በመተባበር እንሥራ ለሚል ወገን ፈቃደኛ ከመሆናቸውም ሌላ፣ ሠራዊቱ ራሱን የቻለ አቋምና የእዝ ሰንሰለት ያለው፣ የተደራጀ ኃይል በመሆኑ፣ በወታደራዊ ግዳጅ ምክንያት በሚንቀሳቀስበት ክፍለ ሀገር ሁሉ የፓርቲ ባለሥልጣናት ልዘዙው ማለት አይችሉም የሚል





አቋም ስለነበራቸው፣ ከፖርቲ ባለሥልጣናት ጋር አሳትና ጭድ ለመሆን በቅተዋል።›› በማለት ለሠራዊቱ ክብርና መብት በግልጽና በድፍረት ይፋለሙ እንደነበር አስረድተዋል።

ይህንኑ ከኢሠፖ ባለሥልጣናት ጋር የነበራቸውን ቅራኔ የሚገልጽ ተጨማሪ ምስክርነት የሰጡት መቶ አለቃ ታደሰ ቴሌም፣

‹‹.......... ይህም የሆነበት ምክንያት ደግሞ የኤርትራ ክፍለ ሀገር ኢሠፖ ዋና ፀሐፊ ካሣዬ አራጋውና ረጋሣ ጂማ ግንባር ፈጥረው በሙስና፣ በሠራዊቱ ስም ስኳር በመነገድ የሠራዊቱን ገንዘብ ይዘርፉ ስለነበረና፣የሠራዊቱን መኪና በማከራየት ከፍተኛ ሚሊዮን ገንዘብ በመመዝበር ላይ ስለነበሩ፣ ታሪኩ ይህንን ለመንግሥቱ ነግሯል ወይም ይነግራል በሚል ጥርጣሬ እሳቸው እንዲመቱ ታላቅ ጥረት አድርገዋል።››

በማለት የኤርትራ የኢሠፖ ዋና ፀሐፊ የነበሩት ካሣዬ አራጋው ለምን ጠላት ሆነው ጄኔራል ታሪኩን እስከ ሕልፈተ ሕይወት እንዳሳደዷቸው ገልጠዋል።



ጀኔራል ታሪኩ የተገኙበት ስብሰባ በጎንደር

*እንደ ራሔል ዋይታ፣ በመከራ ኤሎሄ፣ እንባቸውን በረጨትና ስለ ልጆቻቸው በጅምላ መጨፍጨፍ ሀዘናቸው መራራ በነበረው የጎንደር እናቶች፣*

*‹‹መሳኩ ተፈራ የሞት ታናሽ ወንድም*
*የዛሬን ማርልኝ ከእንግዲህ አልወልድም፡፡››*

*የተባለላቸው፣ የጎንደርን ወጣቶች እጅ ከወርች እያሳሰሩ በገልባጭ መኪና በሲማሊሞ ገደል ያስወረወሩና ያስጨፈጨፉት፣ ሻለቃ መሳኩ ተፈራ፣ የጎንደር ኢሠፖ ጽ/ቤት ተጠሪ፡፡*







**ብርጋዲየር ጀኔራል ታሪኩ ዓይኔ**
**1931 ዓ.ም — 1980 ዓ.ም**



ጀኔራል ታሪኩ የተገኙበት ስብሰባ በጎንደር

እንደ ራሔል ዋይታ፣ በመከራ ኤሎሄ፣ እንባቸውን በረጩትና ስለ ልጆቻቸው በጅምላ መጨፍጨፍ ሀዘናቸው መራራ በነበረው የጎንደር እናቶች፣

‹‹መላኩ ተፈራ የሞት ታናሽ ወንድም
የዛሬን ማርልኝ ከእንግዲህ አልወልድም፡፡››

የተባለላቸው፣ የጎንደርን ወጣቶች እጅ ከወርች እያሳሰሩ በገልባጭ መኪና በሲማሊሞ ገደል ያስወረወሩና ያስጨፈጨፉት፣ ሻለቃ መላኩ ተፈራ፣ የጎንደር ኢሠፓ ጽ/ቤት ተጠሪ፡፡







**ብርጋዲየር ጀኔራል ታሪኩ ዓይኔ**
1931 ዓ.ም — 1980 ዓ.ም

# ምዕራፍ ፮

## የብ/ጄኔራል ታሪኩ የናደው ዕዝ አዛዥነት ሹመትና አንድምታው፣

‹‹በ1979 ዓ.ም መጨረሻ አካባቢ የ2ኛው አብዮታዊ ሠራዊት አዛዥ ሜ/ጄኔራል መርዕድ ንጉሤ ታመው ወደ አዲስ አበባ ለሕክምና ሄደው ነበር። በዚህም ምክንያት መንግሥት በወቅቱ በአዛዦች መካከል አጠቃላይ ዝውውር አወጣ።›› በማለት በኤርትራ መዘዝ መጽሐፋቸው ገጽ 151 ላይ መግለጫቸውን የጀመሩት ሻምበል አምሳሉ፣ ጄኔራል ታሪኩና ሌሎች ከፍተኛ መኰንኖች በዝውውር በአዳዲስ ሥፍራዎች ተመድበው ግዳጃቸውን እንዲወጡ ተደርጎ እንደነበር አብራርተዋል።

ያ በ ‹ሁአሠ› ውስጥ የተደረገ የአመራር ለውጥና ዝውውር ብዙዎችን እንዳላስደሰተ የገለጹት ሻምበል አምሳሉ፣ ምክንያቱም ብለው የሰጡት ጭብጥ፣ የከፍተኛ መኰንኖቹ በፍፁም አለመግባባት እንደነበረ ይገልጣል።

ይህ በመኰንኖች መካከል መግባባትና አንድነት ብሎም መከባበር አለመኖር መንግሥት ሆን ብሎ የፈጠረውና ሲጠቀምበት የነበረ ስልት ሲሆን፣ ከአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ጀምሮ እስከ ወታደራዊው መንግሥት የቀጠለው መሠሪ የሥልጣን መጠበቂያ ብልሃት እንደነበረም አክለው ጠቁመዋል።

በመቀጠልም፣ ‹‹ብ፣ጄኔራል ታሪኩ ወደ ሁአሠ ሲመደቡ ከአዛዡ ከሜ/ጄኔራል ረጋሣ ጂማ ጋር ተግባብተው መሥራት





እንደማይችሉ ገልፀው ነበር። እነ ሜ/ጄ ኃይለጊዮርጊስ ይህ ችግር እንደማይፈጠር በመቁጠርና ጉዳዩን አቃለው በማየት ጄ/ታሪኩን ወደ ኤርትራ ላኳቸው።›› ብለዋል።

የጄኔራል ታሪኩን ሹመትና ዝውውር በተመለከተ ምክንያታዊ ትንተና የሰጡት ሻለቃ ቦጋለ ንጋቱ፣ እንደሚከተለው ሀሳባቸውን በመጽሐፋቸው ላይ ገልፀዋል።

‹‹.......,ጄ/ታሪኩ ዓይኔ ወደ ኤርትራ ክፍለ ሀገር ናደው ዕዝ ግንባር በተዛወሩበት ወቅት አዲስ ሹመት ሳይሆን፣ ለበቀል የሚመች ሁኔታ ለመፍጠር እንደነበረ መገመት አስቸጋሪ አልነበረም። ››

‹‹ጄ/ታሪኩ ዓይኔ ወደ አፋቤት ግንባር በተዛወሩበት ወቅት እርሳቸውን ለመሸኘትና በምትካቸው የመጡትን ብ/ጄኔራል አዲስ አግላቸው ን ለመቀበል በተዘጋጀው ግብዣ ላይ ንግግር አድርገው ነበር። ንግግራቸውም፣

‹‹ካሁን ወዲያ የምንገናኘው ምናልባት ወደ ናደው ዕዝ ስትመጡ ነው። ያም ቢሆን በሕይወት ካለን ነው። የእኔን መዛወር በብዙዎቻችሁ ግምት ከፍተኛ ሹመት አድርጋችሁ እንደምትጠብቁ አውቃለሁ።

በግንባሩ ከተሰለፈው ሠራዊት ብዛትና አካባቢው ካለው ወታደራዊ ሁኔታ፣ እንዲሁም በአጠቃላይ አገራችን ባለችበት ጦርነት ውስጥ ግንባሩ ካለው ወታደራዊ ጠቀሜታ አንፃር፣ ምደባው ትልቅ ሹመት ይመስላል። ነገር ግን የተደገሰልኝን እኔ ስለማውቅ ሁላችንም መልካም ዕድል ይግጠመን።›› በማለት ተሰናብተዋል፣ ሲሉ በወቅቱ

በሥፍራው ተገኝተው የሰሙትን ንግግርና ሁኔታ ሻለቃ ቦጋለ ዘግበዋል፡፡ (ትውልድ ያናወጠ ጦርነት፣ *ከገጽ 79 እስከ 86)*

ብ/ጄኔራል ታሪኩ አፍአበት ተመድበው የናደው ዕዝ ዋና አዛዥ በሆኑበት ዘመን ለሥራ ጉዳይ ወደ ሥፍራው በመሄድ ያዩትንና የተገነዘቡትን ሁኔታ በተመለከተ፣ ኮሎኔል አምሳሉ ባሰፈሩት ታሪክ ላይ፣

‹‹ብ/ጄኔራል ታሪኩ የናደው ዕዝ አዛዥ ሆነው አፍአበት እንዳሉ ለሥራ ሄጄ ተገናኝተናል፡፡ ለሠራዊቱ ያላቸው ፍቅር፣ በውጊያ ጊዜ የሚያሳዩት ድፍረት፣ የበታች አዛዦችን የማስተማርና ለውጊያ የማዘጋጀት ችሎታቸው ከፍተኛ ነበር፡፡ ግርማ ሞገስ የተላበሱ፣ የአዛዥነት ብቃታቸው ከፊታቸው ላይ የሚነበብ፣ አመራራቸው ቆራጥ፣ የማያወላውል ውሣኔ የሚሰጡ፣ጠንካራ ጄኔራል መኰንን መሆናቸውን አይቻለሁ፣ ይህም በሁሉም ዘንድ የታወቀ ነው፡፡›› ሲሉ የታዘቡትንና የተገነዘቡትን የጄኔራሉን ብቃትና ክህሎት መስክረዋል፡፡

በዚያን ወቅት እንደተለመደው በአጠገባቸው የነበሩትን የፖለቲካና ወታደራዊ ደኅንነት ኃላፊዎች፣ ከሳቸው በፊት እንደነበሩት እንደሌሎች አዛዦች የተለየ እንክብካቤ እንደማያደርጉላቸውና፣ ሁሉም በመስመሩና በሥርዓቱ እንዲካሄድ አመራር ይሰጡ እንደነበርም ገልጸዋል፡፡

በዚህም ምክንያት አጠገባቸው የነበሩት የፖለቲካና የደኅንነት ባለሥልጣናቱ ወደ ላይ አለቆች ወደነ ካሣዬ አራጋውና ወታደራዊ አዛዦች አሉታዊ ሀሳባቸውን ሪፖርት ማድረግ





መቀጠላቸውንና አለቆቹም ውንጀላውን በማስተጋባት የአምባገነንነት ስም እንደ ለጠፉባቸው ኮ/ል አምሳሉ አስረድተዋል፡፡

እንደ ኮሎኔል አምሳሉ መግለጫ፣ በዚህ መካከል ብ/ጄኔራል ታሪኩ ኃይለኛ የኩላሊት በሽታ ይዟቸው፣ ደም እየሸኑ አመራር ይሰጡ እንደነበርና ለሕክምና አሥመራ ሲሄዱም መታመማቸው ተረጋግጦ ሕክምና ይደረግላቸው እንደነበር በሕክምና መዝገባቸው ላይ ተጽፏል፡፡ ይሁን እንጂ በሁአሠ አዛዥ በጄኔራል ረጋሣ ጂማ የጀ/ ታሪኩ መታመም ሹፈትና ከግንባር ለመሸሽ የተደረገ ስልት ሆኖ ተተረጐመ፡፡

ቀደም ሲል የሄሊኮፕተርን አጠቃቀም ጉዳይ በተመለከተ የክብር ዘበኛው ሠራዊት ምሩቅ ጄኔራል ረጋሣ ከክቡር ዘበኛ ጓዶቻቸው ጋር ባቀረቡት የተቀነባበረ ክስ፣ ጄኔራል ታሪኩ በበቂ ማስረጃ እንደረቷቸውና በነፃ እንደተለቀቁ ይታወቃል፡፡

በዚህ ቁጭት ውስጥ የነበሩት ጄኔራል ረጋሣ የጄኔራል ታሪኩን ሕመም ማጣጣልና በዕኩይ ትርጓሜ መመንዘር በቀል ለመቅረፍ የተዘጋጁ መሆናቸወን በግልጽ እንደሚጠቁም ኮ/ል አምሳሉ አመላክተዋል፡፡

ይህ በእንዲህ እንደነበረ፣ ከመስከረም 1980 ጀምሮ ሻዕቢያና ወያኔ ከደፈጣ ተዋጊነት ደረጃ አልፈው የመንግሥት ቅርጽ ይዘው የታዩበት ወቅት እንደነበረ መቶ አለቃ ታደሰ ቴሌ ሰልባኖ፣ ‹‹የአናብስት ምድር›› በሚለው መጽሐፋቸው ገጽ 361 ላይ ገልፀዋል፡፡ መንግሥት ደግሞ ያለ ትጥቅ ትግል ምንም ዓይነት መፍትሔ የሌለ መሆኑን በመግለጽና ,በመወሰን ትግሉን ቀጣይና ተግባራዊ ለማድረግ አቅዶ ኘበር፡፡

በዚያ ወቅት፣ ሻዕቢያም ከውጭ የኢትዮጵያ ጠላቶች ባዘነቡለት የገንዘብና የመሣሪያ ድጋፍ፣ በአገር ውስጥም በመንግሥቱ የአመራርና ወታደራዊ መዋቅር ውስጥ የተሰገሰጉ ባንዶች ይፈጽሙለት በነበረው አሻጥር፣ የኢትዮጵያ ሠራዊት እየተመታ፣በማረከው መሣሪያ ደንድኖ አስቸጋሪ ሆኖ ቀጠለ።

በዚሁ መሠረት በኅዳርና በታህሣሥ ወር 1980 ዓ.ም በልዩ ልዩ ሥፍራዎች በሠራዊቱ ላይ ባደረሰው ተከታታይ ጥቃት ሻዕቢያ በለስ ቀናው። ሠራዊቱን ለማዝናናትና ወኔውን ለማደስ የሙዚቃ በረከቱን ይዞ የሄደው የምሥራቅ ዕዝ ኪነት ቡድን አባላት፣ ከነሙሉ መሣሪያቸው የፍልሚያው ሰለባ የሆኑት በዚያው ዘመን እንደሆነ ታሪክ ዘግቧል።

በዚህ 1980 ዓ.ም በኅዳርና በታህሣሥ ወራት ታላቁን የናደውን ዕዝ ለመበተንና ኃይሉን ለመደምሰስ ሻዕቢያ በሚጥርበት ወቅት፣ በታህሣሥ ወር 1980 ዓ.ም ከናደው ዕዝ አንድ ክፍለ ጦር ተከፍሎ ወደ ደጋ አውራጃዎች እንዲጓዝና አሰሳ እንዲያደርግ ከሁለተኛው አብዮታዊ ሠራዊት /ሁአሠ/ አዛዥ ከሜ/ጄኔራል ረጋሣ ጂማ ለብ/ጄኔራል ታሪኩ የትዕዛዝ ደብዳቤ ደረሳቸው።

ጄኔራል ታሪኩም፣ይህን ትዕዛዝና ነባራዊውን ሁኔታ ለመገምገም የክፍለ ጦር አዛዦችንና ፖለቲካዊ ኃላፊዎችን በመሰብሰብ ሰፊ ውይይት እንዲካሄድበት አደረጉ።

በዚህ መካከልም ጠላት አፍአበትን ለማጥቃት ዝግጅትና ጠንካራ እንቅስቃሴ ላይ መሆኑን የዕዙ መረጃ ክፍል ተከታትሎ የደረሰበትን የስለላና የጥናት ጭብጥ ለስብሰባው አቀረበ።





በደረሰው ትእዛዝና በቀረበው የስለላ መረጃ፣ በነዚህ በሁለቱ ወሳኝ ጭብጦች ላይ ሰፊ ውይይት ተካሄዶ በመጨረሻ በተሰብሳቢዎቹ ሙሉ አቋም ከውሣኔ ላይ ተደርሷል። ውሣኔውም፣ ከዕዙ ተከፍሎ ጦር መላክ የለበትም፣ የሚል ጠንካራ የአቋም መልስ ነበር።

የዚያም መልስ መሠረታዊ ምክንያቱ፣ ጠላት አፍአበትን ለማጥቃት ጠንካራ ዝግጅት ማድረጉ በመረጃ በተረጋገጠበት በዚያ ልዩ ወቅት፣ ጦር ክፍሎ ወደ ሌላ አቅጣጫ እንዲሠማራ ማዘዝ የናደው ዕዝን ኃይል ይበልጥ ማዳከምና ለጠላት አመቺ ሁኔታ መፍጠር እንደሚሆን የሚጠቁም ነበር።

በውይይቱ ሂደት ክፍለ ጦር እንዲቀነስና በተናጠል ለአሰሳ እንዲሠማራ የታዘዘው ትእዛዝ፣ ወቅታዊውንና አካባቢያዊውን ሁኔታ ካለማወቅ፣ አለበለዚያም ሌላ ስውር ዓላማ ያለው ረቂቅ ተልዕኮ ለማከናወን የተሴረ ሴራ እንደነበረ ጉባዔው በከባዱ ጠርጥሮ ነበር።

በመሆኑም በስብሰባው ውሳኔ መሠረት የተባለው ጦር እንደማይላክ የምላሽ ደብዳቤ ተጽፎ በዕዙ አዛዥ በጄኔራል ታሪኩና በወቅቱ የዕዙ የፖለቲካ ኃላፊ በነበሩት ሻለቃ ጀምበሬ ተሰማ ተፈርሞ ለነሜ/ጄኔራል ረጋሳ ጂማ ተላከ።

ይህ ደብዳቤ አዛዡን ሜ/ጄ ረጋሳ ጂማንና ምክትል አዛዡን ብ/ጄኔራል ውበቱ ፀጋዬን እጅግ አበሳጨ። ከዚህም በመነሳት ምክትል አዛዡ ጄኔራል ውበቱ ወደ አፍአበት እንዲሄዱና የሚመለከታቸውን የሠራዊት አባላት ሁሉ እንደገና ሰብስበው በማነጋገር ትእዛዙ ተግባራዊ እንዲሆን መመሪያ እንዲሰጡ በዋናው አዛዥ ትእዛዝ ተሰጣቸው።

በዚህም መሠረት ጄኔራል ውበቱ በሄሊኮፕተር ወደ አፍአበት ሄዱ። ጄ/ ውበቱ አፍአበት እንደደረሱ ያደረጉት የቅድሚያ ተግባር የናደው ዕዝን አመራር መከፋፈል ነበር። በዚህም መሠረት፣ የፖለቲካ ኃላፊ በነበሩት በሻለቃ ጀምበሬ ተሰማ ላይ ማስፈራራትና ቀለል ያሉ የቅጣት እርምጃዎች ወሰዱ።

በመቀጠልም ‹‹እንዴት ከአንድ ፊውዳል አዛዥ ጋር ተባብረህ የተላለፈውን ትእዛዝ አንፈጽምም ብለህ ፈርመህ ትልካለህ?››በሚል ወቀሳ፣ከባድ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያም እንዲደርሳቸው አደረጉ።

‹‹....ፊውዳል አዛዥ›› የሚለውን አባባል የተመለከተ፣ አዛዡ ሜ/ጄኔራል ረጋሣ ምክትላቸውም ብ/ጄኔራል ፀጋዬ፣ በጄኔራል ታሪኩ ላይ የነበራቸው ጥላቻና ቂም ምን ያህል የደደረ እንደነበረ በገሀድ ሊያይበት ይችላል።

ከዚህ በኋላ፣ብ/ጄኔራል ውበቱ የናደው ዕዝን የአመራር አባላት በመሰብሰብ አነጋገሩ። የተሰጠው መልስ ሕገወጥና ትክክል እንዳልነበረ በመግለጽ፣ቀደም ሲል በተጻፈው ትእዛዝ መሠረት አንድ ክፍለ ጦር ከዕዙ ተገንጥሎ ወጥቶ አሰሳውን እንዲአከናውን አጥብቀው ለስብሰባው አሳሰቡ።

የስብሰባው አባላትም በዕዙ የደኅንነት ክፍል የሻዕቢያ ጦር አፍአበትን ለማጥቃት ጠንካራ ዝግጅት ማድረጉን መረጃ ያገኘ በመሆኑ በዚያን ሰዓት ኃይሉን መቀነስና ማሠማራት አደጋ ያስከትላል በማለት ሀሳባቸውን በማሰማት ጠንክረው ከተከራከሩ በኋላ ጥሪውን ሳይቀበሉት ቀሩ።





ጄኔራል ውበቱም ተሰብሳቢዎቹ ትእዛዙን እንዲቀበሉና ውሳኔያቸውን ዳግም እንዲያጤኑ ሀሳባቸውን ደጋግመው አቀረቡ። ይሁንና የናደው ዕዝ አመራር አባላትም አጥጋቢ ወታደራዊ ምክንያቶች ስላልቀረቡላቸው ቀደም ሲል የተጻፈውን የተቃውሞ ሀሳብ በመድገም በአቋማቸው እንደፀኑ ስብሰባው ተጠናቀቀ።

ሻለቃ ጀምበሬም ጠንካራና የመርህ ሰው ስለነበሩ ልዩ ልዩ የማስፈራራትና የቅጣት ጫና ቢደርስባቸውም ከአቋማቸው ፍንክች ሳይሉ ቀሩ።

ስብሰባውን ማሳመንና በቂ ምክንያት ማቅረብ የተሳነው በምክትል አዛዡ በብ/ጄኔራል ውበቱ የተመራው አመራርም ወደ አሥመራ ተመልሶ ለበላይ አካል ሪፖርት አደረገ። ያቀረበው ሪፖርትም፣‹‹ የናደው ዕዝ አዛዥ በዕብሪት ትዕዛዝ አልቀበልም፣ ብለዋል።›› የሚል ተንኮልና ሸፍጥ ያሸመቀ ዘገባ ነበር።

‹‹ይህም የተንኮል ዘገባ ለመከላከያ ሚኒስትሩ ለሜ/ጄኔራል ኃ/ጊዮርጊስ ሀ/ማርያም ደረሰ። እሳቸውም ለሊቀ መንበሩ አሻግረው አስታወቁ። ቀድሞውንም በሀሰት ውንጀላ በርካታ ወሬ ደርሷቸው፣ ጄኔራል ታሪኩን እንደ ሥልጣን ተቀናቃኝ ሲጠረጥሩአቸውና ሲያብጠለጥሉአቸው የቆዩት ሊቀ መንበሩ በብስጭት አበጡ። የልባቸው ቂምና ጥላቻም ይበልጥ ደደረ።

በዚህ ሁኔታ ውስጥ አማጽያኑ ሻዕቢያና ወያኔ በረዥም ጦርነት በተሰላቸው የኢትዮጵያ ሠራዊት ላይ ጥቃት እያደረሱ ይዞታቸውን ማስፋትና ማጠናከር ቀጠሉ። በዚህም መሠረት ከህዳር ወር እስከ ታህሣሥ ወር ማብቂያ ድረስ በኢትዮጵያ ሠራዊት ላይ በተቀናጀ ኃይል ከባድ ጉዳት አደረሱ።

ይህ በእንዲህ በነበረበት ሰዓት ጄኔራል ታሪኩ በኩላሊትና በአንጀት አልሰር ሕመም ከባድ ሥቃይ ላይ ነበሩ፡፡ ይሁን እንጂ በሕመም እተሠቃዩና ኃላፊነታቸውን እየተወጡ አልፎ አልፎ ወደ አሥመራ በመሄድ የሕክምና እርዳታ ለማግኘት ጥረት ያደርጉ ነበር፡፡

አሥመራ የነበረው የገጀረት ሆስፒታልም ለነበረባቸው ጽኑ ሕመም በቂ ሕክምና እንዲያገኙ ወደ አዲስ አበባ ጦር ኃይሎች ሆስፒታል ሄደው እንዲታከሙ ጽፎላቸው ነበር፡፡ በዚህም መሠረት የመታከም ዕድል እንዲያገኙ፣ በሥፍራቸው ጊዜያዊ አዛዥ እንዲተካ ከአንዴም ሁለቴ ጄኔራል ታሪኩ ማመልከቻ አቅርበዋል፡፡ ይሁን እንጂ በአለቃቸው በጀ/ረጋሣ ዕኩይ ትርጉም እንጂ ቀና ምላሽ ሳይሰጣቸው ቀረ፡፡

ደንብና ሥርዓትን በተከተለ መንገድ፣ለሕልውናቸው አስጊ የነበረውን ሕመም መታከም እንዲችሉ ለአለቃቸው ለሜ/ጄኔራል ረጋሳ ጂማ ለሦስተኛ ጊዜ ማመልከቻ አቀረቡ፡፡

## የሦስተኛው የማመልከቻ ይዘት የሚከተለው ነበር፡፡

ማመልከቻው የተጻፈበት ዕለት ታህሣሥ 8 ቀን 1980 ዓ.ም. አፍአበት ሆኖ፣ አድራሻው ለሁለተኛው አብዮታዊ ሠራዊት አዛዥ ለሜ/ጄኔራል ረጋሣ ጂማ፣ አሥመራ ይላል፡፡ በቀጣዩ አንቀጽም፣ ሦስተኛ አቤቱታው መልካም ፍጻሜ እንደሚያገኝ በማመን ፍሬ ነገሩን ይቀጥላል፡፡





የናደው ዕዝ አዛዥ ሆነው ከተመደቡበት ጊዜ ጀምሮ በእሳቸው አመራር ተደራራቢ ግፍና በደል እንደደረሰባቸው በመግለጽ፣ ካንዴም ሁለቴ በማመልከቻቸው ላይ ደረሰባቸው በደል ማስማታቸውን ይጠቅሳል፡፡

የተሰጣቸውም መልስ ማስጠንቀቂያ ዛቻና ማስፈራሪያ ቢሆንም ለሦስተኛ ጊዜ ያንኑ ችግሩን በዚያ ማመልከቻ ለማቅረብ መገደዳቸውን በመጥቀስ ችግሮቹን በቁጥሮች ቅደም ተከተል መሠረት ገልጸዋል፡፡

ያቀረቧቸው አቤቱታዎች፣

1ኛ የገጀረት ሆስፒታል የሰጠውን የሕክምና ማስረጃ ቅጂ በማቅረብ ሕክምና ማግኘት እንዲችሉና በኃላፊነት በታቸውሌላ አዛዥ እንዲወከል እንደገና መጠየቃቸውን፣

2ኛ የሕክምና መብት ጥያቄ ማቅረባቸው እንደ ጥፋት ተቆጥሮ በዲሲፕሊን ኮሚቴ መታመማቸው እንዲጣራ መደረጉ አግባብ እንዳልሆነና ስለጤናቸው መታወክ የሐኪም ማስረጃ ሊያቀርቡ እንደሚችሉ፣

3ኛ የሠራዊቱን የመዝናኛ ክበብ ገንዘብ ለግላቸው እንደሚጠቀሙበትና እንደሚዝናኑበት የተወነጀሉበት ወሬ ሀሰት እንደሆነና፣ ክበቡ ይመራ የነበረው ራሱን በቻለ ኮሚቴ፣ በዕዙ ፖለቲካ መምሪያ፣ በባህልና ስፖርት ጉዳይ ኃላፊነት እንደሆነና ይህንን እንዲያጣራ በብ/ጄ ታደሰ መሪነት ከአሥመራ የተላከው ቡድን የመዝናኛ ክበቡን አመራርና አሠራር አጣርቶ ከተወነጀሉባቸው አሉባልታዎች ነፃ መሆናቸውን አረጋግጦ እንደተመለሰ የሚያስረዳ ሀሳብ፣

4ኛ ለግል ጉዳያቸው አሥመራ እንደሚመላለሱ ተደርጐ የተወራው ሀሰት እንደሆነና ይሄዱም የነበረው በሐኪም ቀጠሮ መሠረት የሕክምና እርዳታ ለማግኘት እንደነበረ፣ የገለጸ ሆኖ፣ በመጨረሻም በአጽንኦት ያቀረቡት ጥያቄ፣

" ጽኑ የጨጓራና የአንጀት መቁሰል ሕመም ስላደረባቸው በሐኪሞች በተነገረው መሠረት ወደ መሀል አገር ሄደው እንዲታከሙ እንዲፈቀድላቸው የሚጠይቅ ነበር።

ያቀረቡት አቤቱታ የማይፈፀም ከሆነ፣ ዕድሜያቸው ለጡረታ መድረሱን በማስታወስ በጡረታ የመሰናበት ዕድል እንዲሰጣቸው፣ ይህም ካልሆነ ያለ ጡረታ መብት ከሠራዊቱ በነፃ እንዲሰናበቱና በዘመዶቻቸው ድጋፍ እየተረዱ እንዲታከሙ ስንብት እንዲፈቀድላቸው ይጠይቃል።




ጄኔራል ታሪኩ በሕመም ላይ በነበሩበት ወቅት





በወቅቱ ጄኔራሉ የጻፉት 3ኛ ማመልከቻ ትክክለኛ ቅጂ፣ከዚህ በታች እንደሚታየው ነበር።



4ኛ ለግል ጉዳያቸው አሥመራ እንደሚመላለሱ ተደርጐ የተወራው ሀሰት እንደሆነና ይሄዱም የነበረው በሐኪም ቀጠሮ መሠረት የሕክምና እርዳታ ለማግኘት እንደነበረ፣ የገለጸ ሆኖ፣ በመጨረሻም በአጽንኦት ያቀረቡት ጥያቄ፣

" ጽኑ የጨጓራና የአንጀት መቁሰል ሕመም ስላደረባቸው በሐኪሞች በተነገረው መሠረት ወደ መሀል አገር ሄደው እንዲታከሙ እንዲፈቀድላቸው የሚጠይቅ ነበር።

ያቀረቡት አቤቱታ የማይፈፀም ከሆነ፣ ዕድሜያቸው ለጡረታ መድረሱን በማስታወስ በጡረታ የመሰናበት ዕድል እንዲሰጣቸው፣ ይህም ካልሆነ ያለ ጡረታ መብት ከሠራዊቱ በነፃ እንዲሰናበቱና በዘመዶቻቸው ድጋፍ እየተረዱ እንዲታከሙ ስንብት እንዲፈቀድላቸው ይጠይቃል።



ጄኔራል ታሪኩ በሕመም ላይ በነበሩበት ወቅት





በወቅቱ ጄኔራሉ የጻፉት 3ኛ ማመልከቻ ትክክለኛ ቅጂ፣ከዚህ በታች እንደሚታየው ነበር።

አፋቤት ታኅሣሥ 8 ቀን 1980 ዓ.ም

ለጓድ ሜ/ጄኔራል ረጋሣ ጂማ
የሁለተኛ አብዮታዊ ሠራዊት አዛዥ
አሥመራ

አመልካቹ የምለምንበት ፍሬ ነገር ተመልክተው ከመልካም ፍላጎት አንጻር እንድታዩልኝ በመማፀን ነው።


ፍሬ ነገሩ ከ1979 ዓ.ም እንጋሽ ድምር የናደው ዕዝ አዛዥ ሆኜ ከተመደብኩ በኋላ ጀምሮ በአርበኞ አመራር የሚደርስብኝ ጫና እና በደሎች ከልክ ያለፉ ስለሆኑ ከዚህ ቀደም ሁለት ጊዜ በጻፍኩት ማመልከቻዬ መግለጼ ይታወሳል።

ይሁን እንጂ ላቀረብኳቸው ጥያቄዎች የተሰጠኝ መልስ ዛቻ እና የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በመሆኑ ለ3ኛ ጊዜ እነሆ ለማመልከት ተገድጃለሁ።

1ኛ/ በደረሰብኝ ከፍተኛ የአንጀት መቁሰል ሕመም እንደምሰቃይ 'በሐኪሞች ተረጋግጦ የገደረኝ ሆስፒታል ወይ ጦር ኃይሎች ሆስፒታል' እንድታከም የሰጡኝ አስረጂ ፍቱን ለአርበኞ አቅርቤ በቦታዬ ላይ ሌላ አዛዥ ይመደብ ብዬ ያቀረብኩትን [illegible] በመዘግየቱ በአሁኑ ሰዓት ሕይወቴ በአስጊ ደረጃ ላይ ይገኛል።

2ኛ/ የሕክምና ዕረፍት ጥያቄ ባቀረብኩ እንደገና ተቀምጦ ለደሊ ኪን ኮሚቴ እንዲጣራ ተደርጎ ጉዳዩ በኮሚቴ ሲጣራ ከዚህም በተጨማሪ እኔ ለግል ፍላጎቴ ከአፋቤት አሥመራ እንደምመላለስ፣ የሠራዊቱን መዝናኛ ከበብ ገንዘብ እንደምጠቀም ለጭምራው ሠራዊት ደግፍ እንደሌለኝ በአርበኞ የተደረሰ ይህ ኪን ኮሚቴ ጉዳዩን አጣርቶ ተመልሶዋል።

3ኛ/ እኔ ላለፉት 32 ዓመታት በሠራዊቱ ቤት ሳገለግል የሕክምና ዕረፍት የሄድኩ ለክስ የሠራዊቱ አባል ካለ በበቂ አላየሁም። እኔ እንዳሻኝ የት ለፍላጎቴ አሥመራ ጋዎች አላጭቀም። የምልጠው ባለሆ ፍጥር ነው ይሁን ደግሞ አርበኞም አሳምር ያውቃሉ። የዕዙን መዝናኛ ገንዘብ ለግል ጥቅሙ አጭሎክዋል የተባለው ከእውነት የራቀ ሀሰት ነው። ምክንያቱም መዝናኛ ከበቡ የሚመራው ገዐዙ ፖለቲካ መምሪያ ባህሉና ስፖርት ጉዳይ ሀለፊ ሲሆን፣ የሚተዳደረው ደረሰኝ በቻለ ኮሚቴ በኩሁኑ 05 ሣንቲም እንደሚጠቅን ኮሚቴው በደረገው ማጣራት አረጋግጦ ተመልሶዋል። ለጭምራው ሠራዊት ደገፍ እንደሌለኝ



_2_

ላይ ጠላት ጉዳት አድርሰዋል የተባለው በሰዐቱ እና በገደረት ሆስፒታል ሕክም
ትዕዛዝ ለ5 ቀን በከገዱ መርፌ ታዘለኝ እየተከታተሉ በመታከም ላይ እያለሁ ጠላት
ባደረሰ ጉዳት እርስዎም በእኔ ቦታ ሆነው ቢያዩት የሕሊና ፍርድ መስጠት ይችላሉ::
በወቅቱ ያለጥገም ለማገኛው ሕክምና ቀን አጀር ወደ ግንባር ተመልሻለሁ::=

ጓድ ጄኔራል እኔ አሁን የምፈልገው፤

1ኛ የጤናዬ መቃወስ ሕክምና ፀገብ ብገ ቀን ከሌሊት በመሰናዶት ላይ በመሆኔ በዚህ ከቀጠለ ለሕይወቴ አደጋ መሆኑን በሐኪሞች ስለተነገረኝ ወደ መሐል ሀገር ሽኙ እንዲታከም ::

2ኛ/ ዐይኔ የ ለጡረታ በመቆየት ከሠራዊቱ በጡረታ ተሰናብቼ ከፍተኛ ሕክምና ተከታትዬ ሕይወቴን እንዳላትርፍ እንደደረገልኝ::

3ኛ/ 1ኛ2ኛ ጥያቄዬ ተቀባይነት ካጡ ገን አሁን በቁጥር የተደቆኣነኝ ከፍተኛ ጥቃት ለሕይወቴ ስለአሰጋኝ ያለጡረታ መብት ከሠራዊቱ በነጻ እንድሰናበት ኝ ደ ይህን ሰሰ የጉዱን በሚረሰበ አንደመሆኔ መጠን ወደ ተወለድኩ ቦታዬ ወበ እና ጉዱን ለወራዲ ጋር ወረፋ ሲኖ ዘመዶቼ በራሳቸው ወጭ አሳክመው እንደሚያድኑኝ ተስፋ ስላለኝ ነው::

ኢትዮጵያ ትቅደም

ብ/ጄኔራል
መ/1468 ታሪኩ ዓይኔ

ገለባጭ
ለጓድ ሌ/ጄኔራል ተስፋዬ ገ/ኪዳን
የኤርትራ ክፍለሐገር የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ
አስተዳደር የበላይ አስተዳዳሪ
ለጓድ ሜ/ጄ ኃ/ጊዮርጊስ ኃ/ማርያም
[illegible]
ለጓድ ሜ/ጄ መርዕድ ንጉሤ
የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም
ለጓድ ኃይሉ ወ/ሚካኤል
የምድር ጦር ዋና አዛዥ





ይህም ሦስተኛ የአቤቱታ ማመልከቻ ቀና ምላሽ ሳያገኝ ይልቁንም አሉታዊ ትርጉም ተሰጥቶት ከግዳጅ ሥፍራ በመሸሽና በአምቢተኝነት ተተርጉሞባቸዋል፡፡


ይህ በእንዲህ እንደነበረ የሻዕቢያ ሠራዊት በታህሣሥ ወር ላይ ከከረን ወደ አሥመራ፣ እንዲሁም ከምጽዋ ወደ አሥመራ፣ ከአዲ ቀይህ ወደ አሥመራ በመንገዝ ላይ በነበሩት ነዳጅና ልዩ ልዩ የድጋፍ ቁሳቁስ በጫኑ የመንግሥት ተሽከርካሪዎች ላይ አደጋና ዘረፋ አደረሰ፡፡

በተጨማሪም፣ ታህሣሥ 21 ቀን 80 ዓ.ም ከምሥራቅ የሄዱት የምሥራቅ ዕዝ ኪነት አባላት በጠላት ደፍጣ ጥቃት በማለቃቸውና ከዚህም በላይ፣ ስሜን ያለው ጦር በፕሬዚደንቱ ላይ ለማመጽ እየተነሣሣ ነው የሚል መረጃ የደረሳቸው መሪ ደጋፊዎቻቸውን አስከትለው በብስጭት እንደጦፉና በሥጋት እንደተወጠሩ አሥመራ ገቡ፡፡ እንደደረሱም ከየዕዙ የተውጣጣ ጦር በማሰባሰብ አነጋገሩ፡፡ ጦሩም ብሶቱን ተናገረ፣ እሳቸውም የማይጨበጥ ተስፋ ለወታደሩ ሰጡ፡፡

ከዚያም፣ ዋነኞቹ የሰሜን ዕዝ ዋና አዛዦች እነ ጄ/ረጋሣ ጂማም ስለተፈፀመው አደጋ ሁኔታና ምክንያት አፍአበት ላይ በተደረገው አስቸኳይ ስብሰባ ላይ ሪፖርት እንዲያቀርቡ ተጠየቁ፡፡

ዋና አዛዦቹም ቀደም ሲል በሀሳብ አለመግባባትና በሥራ ምክንያት በተፈጠረ ቅሬታ የጠሏቸውን በተዋረድ የነበሩ አዛዦችና መኰንኖችን ግንባር ቀደም ተጠያቂ በማድረግ ለሊቀ መንበሩ ዘገባቸውን አቀረቡ፡፡

ከተወነጀሉት አዛዦች መካከል ብ/ጄኔራል ታሪኩ አንዱ ነበሩ፡፡ ሊቀ መንበሩም የየዘርፉን የዕዝ አዛዦች በቀረበባቸው ክስ







ይህም ሦስተኛ የአቤቱታ ማመልከቻ ቀና ምላሽ ሳያገኝ ይልቁንም አሉታዊ ትርጉም ተሰጥቶት ከግዳጅ ሥፍራ በመሸሸና በእምቢተኝነት ተተርጉሞባቸዋል።

ይህ በእንዲህ እንደነበረ የሻዕቢያ ሠራዊት በታህሣሥ ወር ላይ ከከረን ወደ አሥመራ፣ እንዲሁም ከምጽዋ ወደ አሥመራ፣ ከአዲ ቀይህ ወደ አሥመራ በመጓዝ ላይ በነበሩት ነዳጅና ልዩ ልዩ የድጋፍ ቁሳቁስ በጫኑ የመንግሥት ተሽከርካሪዎች ላይ አደጋና ዘረፋ አደረሰ።

በተጨማሪም፣ ታህሣሥ 21 ቀን 80 ዓ.ም ከምሥራቅ የሄዱት የምሥራቅ ዕዝ ኪነት አባላት በጠላት ደፍጣ ጥቃት በማለቃቸውና ከዚህም በላይ፣ ሰሜን ያለው ጦር በፕሬዚደንቱ ላይ ለማመጽ እየተነሣሣ ነው የሚል መረጃ የደረሳቸው መሪ ደጋፊዎቻቸውን አስከትለው በብስጭት እንደጦፉና በሥጋት እንደተወጠሩ አሥመራ ገቡ። እንደደረሱም ከየዕዙ የተውጣጣ ጦር በማሰባሰብ አነጋገሩ። ጦሩም ብሶቱን ተናገረ፣ እሳቸውም የማይጨበጥ ተስፋ ለወታደሩ ሰጡ።

ከዚያም፣ ዋነኞቹ የሰሜን ዕዝ ዋና አዛዦች እነ ጀ/ረጋሣ ጂማም ስለተፈፀመው አደጋ ሁኔታና ምክንያት አፍአበት ላይ በተደረገው አስቸኳይ ስብሰባ ላይ ሪፖርት እንዲያቀርቡ ተጠየቁ።

ዋና አዛዦቹም ቀደም ሲል በሀሳብ አለመግባባትና በሥራ ምክንያት በተፈጠረ ቅሬታ የጠሏቸውን በተዋረድ የነበሩ አዛዦችና መኰንኖችን ግንባር ቀደም ተጠያቂ በማድረግ ለሊቀ መንበሩ ዘገባቸውን አቀረቡ።

ከተወነጀሉት አዛዦች መካከል• ብ/ጄኔራል ታሪኩ አንዱ ነበሩ። ሊቀ መንበሩም የየዘርፉን የዕዝ አዛዦች በቀረበባቸው ክስ

ባነጋገሩበት ወቅት ጄኔራል ታሪኩንም ለወጉ ያህል ሀሳባቸውን ጠይቀዋቸው እንዲናገሩም ዕድል ሰጥተዋቸው ነበር።

ጄኔራል ውበቱ አፍአበት ሄደው ሠራዊቱና አመራር አባላቱ በዚያ ቀውጢ ሰዓት ጦር ከናደው ዕዝ ተከፍሎ ወደሌላ ሥፍራ መሄድ የለበትም ያሉትን ውሳኔ፣ ጄ/ታሪኩን ለመጉዳትና ለመውጋት ባሴረ አባባል፣ ‹‹የናደው ዕዝ አዛዥ ትእዛዝ አልቀበልም›› ብለው ሪፖርት አቅርበው ነበርና፣ ይህን በተመለከተ ጦር ተከፍሎ ይውጣ የሚለውን ትእዛዝ የሳቸው አመራር ያልተቀበለበትን ምክንያት አሳማኝ በሆነ መረጃ ለማስረዳት ጄ/ታሪኩ ጥረት አድርገው ነበር።

ይሁን እንጂ አስቀድሞ በነገር ተሞልተው እና ወስነው የመጡ ስለነበረ ጄኔራል ታሪኩ ያቀረቡትን ሀሳብ ሁሉ በማጣጣል ኰሎኔል መንግሥቱ ሳይቀበሏቸው ቀሩ። በዚያ ስብሰባ ወቅት፣ ሊቀ መንበሩም ቀደም ሲል በተሞሉት ወሬ እየተገፉ ሆን ብለው ይጫኑዋቸው እንደነበረ በስብሰባ ተካፋይነት በሥፍራው የነበሩና የታዘቡ ጽፈውታል።

ቂምና ጥላቻ ቋጥረው፣ የበቀል ጊዜ በማስናዳት ላይ የነበሩት መሪም፣ በአስተውሎትና በተገቢ ሁኔታ እንዳላነጋገሯቸውና መከላከያ ጭብጣቸውን ሊቀበሉዋቸው ፈቃደኛ ባልነበሩበት ጊዜ፣ ጄኔራል ታሪኩ ስለያዟት እውነት ቢከራከሩም ሰሚ በማጣታቸው፣ አንዳንዶች እንደሚሉት የደርጉን መሪ ያበሳጨ ኃይለ ቃል ተናግረው እንደነበረ የስብሰባው ዕድምተኞች የነበሩት ዘግበዋል።

ከዚያ በኂላ ጄኔራል ታሪኩና ብ/ጄኔራል ከበደ ጋሼ ከስብሰባው ወጥተው እውጭ እንዲቆዩ ምክክሩ እንዲቀጥል ተደረገ።





ቀድሞውንም ጉድጓድ ሲምሱላቸው የነበሩት ጄኔራል መርዕድና ጄኔራል ረጋሳ ነገሮችን በማጋነን፣ ‹‹ .....ጓድ ኘሬዚዳንት ጄኔራል ታሪኩ የናቀው እኛን ብቻ አይደለም። እርስዎም ላይ ከፍተኛ ጥላቻና ንቀት አለው።....›› በማለት ከእሳት ላይ ቤንዚን እንደማርከፍከፍ ዓይነት ነገሩን አበላሽተውታል፣ በሚል ታዛቢዎች ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል።

ከዚህ በኂላ ጄኔራል ታሪኩና ብ/ጄኔራል ከበደ ጋሼ በሁለተኛው አብዮታዊ ሠራዊት ወታደራዊ እስር ቤት እንዲታሠሩ ተደረገ። በሌላ በኩል ደግሞ ሁኔታውን በአስቸኳይ አጣርተው እንዲያቀርቡ የሚከተሉት ታላላቅ ጄኔራሎች፣ትዕዛዝ ደረሳቸው።

1 ሌ/ጄኔራል ተስፋዬ ገ/ኪዳን የምድር ጦር ዋና አዛዥ፣
2 ሜ/ጄኔራል ኃይሉ ገ/ሚካኤል፣
3 ሪር አድሚራል ተስፋዬ ብርሃኑ፣
4 ሜ/ጄኔራል አምሃ ደስታ የአየር ኃይል አዛዥ፣

እነሱም የተሰጣቸውን ኃላፊነት በእውነት ለመወጣት የሰውና የሰነድ ማስረጃ አሰባስበው ስፊ ማጣራት አደረጉ።

ጄኔራል ታሪኩን በተመለከተ፣ የደረሱበት አንዱ መረጃ፣ በወቅቱ ከአንጀት መቁሰል በተጨማሪ በኩላሊት ሕመም የተነሳ በሕክምና ላይ እንደነበሩ የሚያረጋግጥ የሐኪም ሰነድ ነበር።

በመጨረሻም ከዚህ ውጭ በጄኔራል ታሪኩ ላይ ጥፋት ከተገኘ፣ ለሠላሳ ሁለት ዓመታት ያደረጉት የግዳጅ አገልግሎትና መስዋዕትነት ግምት ውስጥ ገብቶ የጡረታ መብታቸው ተከብሮ እንዲሰናበቱ የሚጠይቅ የውሳኔ ሀሳብ አቀረቡ።

ይህ የማጣራት ሂደትና የቀረበው ውሳኔ ያበሳጫቸው ሊቀ መንበሩ በኮሚቴው አባላት ሰብሳቢ በሌ/ጄኔራል ተስፋዬ ላይ ከሥርዓት ውጭ በሆነ ዕብሪት እንደጮሁባቸው በወቅቱ ለጉዳዩ ሂደት ቅርብ የነበሩ ፀሐፍት ለታሪክ አስፍረውታል።

ከላይ እንደተገለጸው በሰሜን ዕዝ ውስጥ በነበሩ ከፍተኛ አዛዦች መካከል የነበረውን ተንኰል፣ የሥልጣን ሽሚያና የመጠላለፍ ደባ እንዲሁም የቡድን ሥራ ኰሎኔል አምሳሉ በ «የኤርትራ መዘዝ» መጽሐፋቸው ውስጥ በስፋት አሳይተዋል።

ቀድሞውንም በሥጋት ላይ የነበሩትና በደረሳቸው፣«የታቀደ የመፈንቅለ መንግሥት እቅድ አለ…» በሚል እኩይ ዘገባ ደንግጠውና ተጨንቀው፣ ድብቅ የበቀል ሀሳባቸውን ቋጥረውና ተንደርድረው የደረሱት ሊቀ መንበር፣ በአምባገነንነት የራሳቸውን ውሳኔ በመስጠት ጄኔራል ታሪኩ እንዲገደሉ፣ ብ/ጄኔራል ከበደ ጋሼ ማዕረጋቸው እንዲገፈፍና ያለ ጡረታ መብት እንዲሰናበቱ አዘዙ።

ፍፁም ስሜታዊ የነበረው ውሣኔ የካቲት 6 ቀን 1980 ተጠናቆ የካቲት 7 ቀን ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት ላይ በሚከተሉት ሰዎች አስፈጻሚነት ውሳኔው ተተገበረ።

1ኛ ብ/ጄኔራል ውበቱ ፀጋዬ፣ የሁአሠ ም/አዛዥ፣
2ኛ ኰሎኔል መንግሥቱ ወልደ ጊዮርጊስ፣ የሁአሠ የሕግ አገልግሎት ኃላፊ፣
3ኛ ኰሎኔል አሥራት ታዬ፣ የሁአሠ አስተዳደር መምሪያ ኃላፊ

ያ የግፍ ድርጊት ከመፈፀሙ በፊት ደማቸውንና ጉልበታቸውን እንዲሁም እውቀታቸውንና ፍቅራቸውን ባፈሰሱላት፣ ለ32 ዓመታት በተንከራተቱላት አገራቸው ላይ፣ በንፁህ ፍቅርና ታማኝነት በአዛዥነት በአገለገሉት ሠራዊት ፊት እንደ አቡነ ጴጥሮስ





እጆቻቸው በሰንሰለት ታስረው፣ በገዛ ወገኖቻቸው ሊረሸኑ በቀረበበት ጊዜ፣ በጄኔራሉ ላይ የሚከተሉት የወንጀል ነጥቦች በንባብ ተሰሙ፣

ብ/ጄኔራል ታሪኩ ዓይኔ፣

" የበላይ አካልን መመሪያ አይቀበሉም፣
" ጦሩን አይጎበኙም፣
" የጦሩን ገንዘብ ለራሳቸው ጥቅም አውለዋል፣
" ከሻዕቢያና ወያኔ ጋር ልዩ ግንኙነት ፈጥረዋል፣
" ወገንን ለጠላት አጋልጦ የሚሰጥ ምስጢር ሳይመሰጠር እንዲተላለፍ አድርገዋል፣ የሚሉ ነበሩ።

ይህ እውነትነት የሌለው የቂም መቅረፊያ ውንጀላ ከተነበበ በኋላ በዘጠኝ ተኳሾች ተገደሉ። ንፁህ ደማቸውም ከአገራቸው ምድር ሠርጎ ገባ፣ ሆኖም ስለ እውተኛ ፍርድና ስለ ፍትሕ እስከዛሬ ወደ እግዚአብሔርም በመጮህ ላይ እንደሆነ አያጠራጥርም።

ጉባዔው ሲካሄድና በኋላም ግድያው ሲፈፀም በሥፍራው ነበርኩ በማለት ቃላቸውን የሰጡት መቶ አለቃ ታደሰ ቴሌ እንዲሚከተለው መስክረዋል፣

«ጄኔራል ታሪኩ ወደ ናደው ዕዝ በሄዱበት ወቅት እጅግ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ነበር የገቡት። ይሁንና ታሪኩ ሁኔታውን ለመቋቋም ሁለት ስልት ነበር የተጠቀሙት።

1ኛ ሠራዊቱን በሻለቃ ደረጃ፣በክፍለ ጦርና በብርጌድ ደረጃ አሰባስበው በማነጋገር የሠራዊቱን ስሜት አጠኑ፣

2ኛ ከስብሰባው የተገኘውን ሁኔታ መሠረት ያደረገ መፍትሔና ውሳኔ እንዲገኝ አደረጉ።

‹‹በዚሁ መሠረት ከሠራዊቱ ጋር ደረጃ በደረጃ ከተነጋገሩና የሠራዊቱን ችግርና ብሶት ከተረዱ በኋላ፣ ሀሳቡን ሰብስበው ለማዕከላዊ መንግሥት አቀረቡ፡፡

‹‹በዚህም፣

" የማዕረግ ዕድገት ለሠራዊቱ እንዲሰጥ፣

" ወደ አገር ቤት ለረዥም ጊዜ ፍቃድ ያጡ አባላት ወዳገር ቤት ሄደው እናት አባታቸውን ጠይቀው እንዲመጡ፣

" የቤተሰብ ችግር ያለባቸው ዝውውር እንዲፈቀድላቸው፣

" የሕክምና ችግር የነበረባቸው ሕክምና እንዲያገኙ፣ በአሥመራም ሆነ በተለያዩ ቀላል ቦታዎች ላይ እንዲሠሩ፣

" ዕድሜያቸው ገፍተር ያሉና በ45 ዓመት በላይ ወይም በ50ዎቹ አካባቢ የነበሩ አባላት ከሠራዊቱ በጡረታ ተሰናብተው ወይም በመሀል አገር በኮሚሳሪያት ተሠማርተው እንዲሠሩ በማድረግ ከአንድ ሺህ አምስት መቶ ሠራዊት በላይ እንዲቀነሱ ለማዕከላዊ መንግሥት አቅርበው አስፈጽመዋል፡፡

በነሱም ምትክ አዲስ ምልምል ሠራዊት በመውሰድ ክፍለ ጦሩንና ብርጌዶችን በማጠናከር ከፍተኛ አመራር ሲሰጡ አውቃለሁ፡፡ ይህን ማድረጋቸው በመንግሥት ፊት በወቅቱ ከፍተኛ ምስጋና ነበር ያስገኝላቸው፡፡

‹‹መጨረሻ ላይ ለጄኔራል ታሪኩ ሞት የመጀመሪያው ግንባር ቀደም ሰዎች

1ኛ ጄኔራል ረጋሣ ጂማ የሁለተኛ አብዮታዊ ሠራዊት አዛዥ፣

2ኛ ጄኔራል መርዕድ ንጉሤ የጦር ኃይሎች ኤታ ማዦር ሹም፣





3ኛ ጄኔራል ደምሴ ቡልቶ የመከላከያ ሚኒስቴር የዘመቻ መኰንን፣

4ኛ ጄኔራል አስራት ብሩ፣ የመከላከያ ኢንስፔክሽን መምሪያ ኃላፊ፣

5ኛ ካሣዬ አራጋው የኤርትራ ተጠሪና የብሔራዊ ጦር አባል፣ እነዚህ በመሆን ታሪኩን በምን መልኩ እናጥቃቸው፣ በምን መልኩ እናዛውራቸው በሚል መረብ ዘረጉባቸው፡፡

‹‹እነዚህ ጄኔራሎቹ በሙሉ የክቡር ዘበኛ አባላት ናቸው፡፡ ይህን የሚያደርጉት ደግሞ አስራት ብሩን የናደው ዕዝ አዛዥ አድርገው ሌ/ጄኔራል እንዲሆኑ፣ ለማድረግ አሰበለዚያም ውበቱ ፀጋዬን እዚያ ቦታ ላይ በማድረግ የሜጀር ጄኔራል ማዕረግ ለማሰጠት ነበር፡፡

‹‹ይህም የሆነበት ምክንያት መንግሥቱ ኃ/ማርያም የሜጀር ጄኔራልነት ማዕረግ ለታሪኩ ይገባዋል በማለት ለምልመላ ሲያቀርቡአቸው፣ ገና ይገምገም ብዙ ችግር አለበት በማለት ስሙን በማጥፋት ከማዕረግ አዘግይተዋቸው ነበር፡፡ በዚህም ሁኔታ ሌሎቹ ሜ/ጄኔራል ሲሆኑ ታሪኩ ሳይሆኑ ቀሩ፡፡ ይህም መረጃ ለታሪኩ በወቅቱ ደረሳቸው፡፡

‹‹ታሪኩም እኔ የምሠራው፣ የሠራሁትም ለሹመት አይደለም፡፡ ናቅፋን በመሰለ አስቸጋሪ አውደ ውጊያ ከፍተኛና ግዙፍ ሠራዊትን የመራሁ ነኝና፣ ከአገሪ በላይና ከሠራዊቱ በላይ ምንም ማዕረግ አልፈልግም፡፡ ማዕረጉም ይቅርብኝና እኔ በሰላም ለመኖር እፈልጋለሁ ወደሚል ስሜት ገቡ፡፡

‹‹በዚህም ታሪኩ ከፍተኛ ብስጭት ስላደረባቸው የክብደት መቀነስና ለረዥም ጊዜ የተውትን ሲጋራ ማጨስ እንዲጀምሩ ሆነ። የባህሪ ለውጥም ታየባቸው። ከላይ የተጠቀሱት የክቡር ዘበኛ ሠራዊት አባል የነበሩት መኰንኖች የጦር ሠራዊት አባል የነበሩትን ጄኔራል ታሪኩን ወደ ከፍተኛ አደጋ ገፍተዋቸዋል። ከዚያ በኋላ ታሪኩ ነጭናጫና ከበላይ አለቆቻቸው ጋር ያለመስማማት የሚፈጥሩ ሆኑ። ከሠራዊቱ ጋር ግን ቅቤና ፀጉር ነበሩ። ይወዳቸው የነበረው ሠራዊትም ሕክምና በመንግሥት ከተከለከሉ፣ገንዘብ አዋጥተን በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ እናሳክም እስከድደው ወደ አፋበት ይመልሷቸው ነበረ።

‹‹ታሪኩ ለሕክምና በሐኪም ሪፈር ወይም ቀጠሮ አሥመራ በሄዱበት ጊዜ ሁሉ፣‹..... ለምን መጣህ፣› በማለት፣ የዕዙ ሐኪም፣ ‹ሪፈር ወደ ገጀረት ሆስፒታል› ብሎ የጻፈላቸውን ወረቀት እየነጠቁ፣ አሥመራ ገብተው ገና አልጋ ከመያዛቸው በፊት በሚሊቴሪ ፖሊስ አስገድደው ወደ አፋበት ይመልሷቸው ነበረ።

‹‹መጨረሻ ላይ ጄኔራል ታሪኩ እንግዲህ ሕክምና በማጣቴ የተደቀነብኝ ሁኔታ ለሕይወቴ ስለሚያሰጋኝ፣ የተደቀነብኝ ጥላቻም አደገኛ ስለሆነ፣ ሠራዊቱ ውስጥም የሠላሳ ሁለት ዓመት አገልግሎት ስላለኝ በጡረታ አሰናብቱኝ፣ከኔ በስተቀር በሠራዊቱ ውስጥ የሕክምና መብት ያጣ የለም። ዕድሜዬ ለጡረታ ስለደረሰ አሰናብቱኝ፣ አናሳክምም ከላችሁም ወደ ዘመዶቼ፣ ወይም ወደ ትውልድ አገሬ ሄጄ በዕርዳታ በሕዝብ ገንዘብ ለመታከም እሞክራለሁና በነፃ አሰናብቱኝ የሚል አቤቱታ ለመንግሥት አቀረቡ።

‹‹ከዚያ በኋላ እነ ካሣዬ አራጋው እና እነ ረጋሣ ጂማ በዚህ ጉዳይ ላይ ተነጋግረው ሌላ ውንጀላና ማጥቂያ አዘጋጁ።





ያም የማጥቂያ ጭብጥ፣

" በሕመም ምክንያት ከወሳኝ ጦር ግንባር የመሸሽ ፍላጎት አሳይተዋል፣
" የሠራዊቱን የክበብ ገንዘብ በከፍተኛ ደረጃ አባክነዋል፣
" ሠራዊቱን ግንባር አስማርተው እሳቸው አሥመራ ለመዝናናት፣ አሥመራ ቪዲዮና ሴት እያሳደዱ ቲክሲ

አምባ በተባለው ግንባር ላይ ሻዕቢያ ድል አግኝቶ ሠራዊቱን ጨፍጭፏል፣ የአብዮታዊ ሠራዊት ውድቀት የታሪኩ ንዝህላልነት ነው፣ የሚሉትን የተለያዩ ዝባዝንኬዎችን በመጻፍ ከመንግሥቱ ጋር እንዲጣሉ በከፍተኛ ሸርና ግፍ ምኞታቸውን ፈጽመዋል።

‹‹ኮ/መንግሥቱ በአሥመራ ጉብኝት ባደረጉበት ወቅት በቅድሚያ በነዚህ መሠሪ ሰዎች ወሬ ተሞልተው፣ ቀጥለው ወደ አፋቤት ለጉብኝት ሄደው ነበር። በጉብኝቱ ወቅት ስለተነገሩባቸው ጥፋቶች ታሪኩንም ጠይቀው ነበር።

‹‹ታሪኩም የተባለው ውንጀላ ሁሉ በፍፁም ውሸትና አመራሩና ሠራዊቱ ብቃት እንዳለውና ከአዛዦቹ ከካድሬ ዎቹና ከደኅንነቶቹ ጋራ ምንም ዓይነት ስምምነት እንደሌላቸው ለመንግሥቱ በየዋኅነት ገለጹ።

‹‹መንግሥቱ ይህንን ችግርማ አሥመራ ላይ እፈታዋለሁ ብለው ወደ አሥመራ በመመለስ ሁሉንም የዕዝ አዛዦች አሥመራ ጠርተው አነጋግረዋል። ሌሎችን የአስራ ስድስት ክፍለ ጦር አዛዦች፣ የዕዙን ሰባት ጄኔራሎች ማለትም፣ የዘመቻ፣ የመረጃ፣ የዕዝ አዛዥ፣ የፖለቲካ የደኅንነት ኃላፊዎች ጠርተው አነጋግረዋል።

‹‹የሁአሠ አዛዥ ረጋሣ ጂማና የደኅንነት ኃላፊው ከዕዛችን ለሠራዊቱ ውድቀት ምክንያት የሆኑት ታሪኩ ዓይኔና ከበደ ጋሼ ናቸው ብለው ከሰሱ። የክብር ዘበኛ ሠራዊት አባል የነበሩት ረጋሣ፣ እነዚህ ሰዎች ጧር ሠራዊት ስለሆኑ ብቃት የላቸውም፣ በወታደራዊ ብስለታቸው ደካሞች ናቸው፣ ብለው

በመናገራቸው፣ ኰሎኔል መንግሥቱ፣ ‹ጦር ሠራዊት አይመራም ያለው ማነው..... እኔ ማነኝ?› እስከ ማለት ደርሰው ነበር።

‹‹ከዚያም ጄኔራል ረጋሣን ‹....ውጣልኝ፣› በማለት ከስብሰባው አስወጥተዋቸዋል። ሽዋረጋንም አንተ አየር ኃይል፣ ረጋሣ ክቡር ዘበኛ ስለሆናችሁ ተባብራችሁ ታሪኩን እየወነጀላችሁት ነው። እናንተም ኤርትራን አትመሩም ውጣ....› በማለት እንዳባረሯቸው አውቃለሁ።

‹‹በመጨረሻ ግን ጄኔራል ታሪኩ እንዲሙቱ ካደረጉት ከፍተኛ የፖለቲካ ሰዎች አንዱ ካሣዬ አራጋው ነው። ለመንግሥቱ ኃይለማርያም ያቀረበው ከፍተኛ ሪፖርትና ውንጀላ የግፍ እርምጃ እንዲወሰድባቸው አድርጓል።

‹‹ካቀረበው 27 ገጾች ሪፖርት ውስጥ ዘጠኙ ገጾች በተለይ በጄኔራል ታሪኩ እና በጄኔራል ከበደ ጋሼ ላይ ያነጣጠሩ ነበሩ።

‹‹ይህም የሆነበት ምክንያት ደግሞ ካሣዬ አራጋውና ረጋሣ ጂማ ግንባር ፈጥረው በሙስና፣ በሠራዊቱ ስም ስኳር በመነገድ የሠራዊቱን ገንዘብ ይዘርፉ ስለነበረና፣የሠራዊቱን መኪና በማከራየት ከፍተኛ ሚሊዮን ገንዘብ በመመዝበር ላይ ስለነበሩ፣ ታሪኩ ይህንን ለመንግሥቱ ነግሯል ወይም ይነግራል በሚል ጥርጣሬ እሳቸው እንዲሙቱ ያደረጉት ታላቅ ጥረት ነው።

‹‹ታሪኩ ካልተመታ ሠራዊቱ በትክክል አይመራም በሚለው አረመኔያዊ ውሳኔ ላይ እንዲደረስ ጠላቶቻቸው ከፍተኛ ሚና ከተጫወቱ በኋላ መጨረሻ ላይ፣ ታሪኩ ይሙቱ፣ ከበደ ጋሼ ማዕረጋቸውን ተገፈው ይባረሩ የሚል ውሳኔ ላይ ተደረሰ።





‹‹ውሳኔው ከተሰማ በኋላ፣ ‹እሺ ታሪኩ ይሙታ..... ከበደ ጋሼም ማዕረጉ ይገፈፍ..... ረጋሣ ጂማም ሁለተኛ አብዮታዊ ሠራዊትን አይመራም። ኰሎኔል ሽዋረጋም የፖለቲካ ኃላፊ አይሆንም...... በማለት በቦታቸው ላይ ሌሎች ተወካዮች በማድረግ እነሱንም ወደ አዲስ አበባ አባረሯቸው።

‹‹በወቅቱ ግን ይህንን ሁሉ የሚያቀርቡት ሌ/ጄኔራል ተስፋዬ ገ/ኪዳን ሁለተኛው ካሣዬ አራጋው ናቸው። ይህን ያደረጉትም ‹ታሪኩ ዓይኔ አፋቤት ካለ፣ ሻዕቢያ አፋቤትን መቆጣጠር አይችልም፣በሚል ታሪኩን ለማስመታት ከሻዕቢያ ጋር ግንባር በመፍጠር ነበር።

‹‹ሠራዊቱን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለማስመታት ከኰሎኔል ሽዋረጋ በቀር ጄኔራል ረጋሣም ካሣዬ አራጋውም፣ ተስፋዬ ገ/ኪዳንም ከሻዕቢያ ጋር ግንባር ፈጥረው ነበር።

‹‹ይህን ግንባር በመፍጠር በጄኔራል ታሪኩ ቦታ ላይ ጄኔራል ውበቱ ፀጋዬ ሄዶ ያስተባብር፣ውጊያ ሲነሳ በሄሊኮፕተር ይወጣል፣ በማለት የተንኰል መረብ በመዘርጋት ጄኔራል ታሪኩ የካቲት 7 ቀን 80 ዓ.ም እንዲገደሉ አደረጉ።›› በማለት ዝርዝር ሂደቱን ይፋ አድርገዋል።

በመቀጠልም፣ ‹‹ሻዕቢያ ወዲያውኑ በወሩ ወረራ አደረገ፣ አፋበትንና ናደው ዕዝን ሲይዝ ለናደው ዕዝ ተወክለው የሄዱት ጄ/ውበቱ ፀጋዬ በግመል ሸሽተው ነው ,ከአፋቤት ከረን የገቡት። እንግዲህ ይህ ከታሪኩ ሞት በኋላ የመጣ ወታደራዊ ውድቀት ወይም ፌስራቲ ነው።

ከዚያም ሻዕቢያ በራዲዮ ጣቢያዋ ስታስተላልፍ፣‹ናደው ዕዝ በመያዝ ላይ የነበረው ከሁለት ዓመት በፊት ነው፣ አሁን ግን ሙሉ በሙሉ ያዝነው፣ የያዝንበትም ምክንያት መንግሥቱ በግራ እጁ ቀኝ እጁን ስለቆረጠው ነው፡፡ ቀኝ እጁም ታሪኩ ዓይኔ ነበረ፡፡›› የሚል ከፍተኛ ፕሮፖጋንዳ አሠራጭታለች፡፡

የጀርመን ሬዲዮ ጣቢያም፣ ‹‹…መንግሥቱ ኃ/ማርያም የአዕምሮ በሽተኛ ካልሆኑ በስተቀር ታሪኩ ዓይኔን የሚያክል ግዙፍ ሰው መግደል አልነበረባቸውም፣….›› ብሏል፡፡

በዚያን ጊዜ ይህ ድርጊት የዓለም ትኩረት የሳበ የጠላትም የወዳጅም ከፍተኛ ወሬ ሲሆን ሌሎቹ ጄኔራሎች መንግሥቱ በሌሉበት ተሰብስበው፣ ነገ የኛስ ዕጣ ፋንታ ምንድነው፣…. ስለዚህ የፈለገው ውድቀት /ፌሌሪቲ/ ይምጣ እንጂ መንግሥቱን ከመገልበጥ ሌላ ምንም አማራጭ አይኖረንም በማለት፣ ከታሪኩ ሞት በኋላ ሌላ መረብ ዘረጉ፡፡›› በማለት የነበረውን የከረረ የሥልጣን ጥማትና ሽኩቻ ገልጸዋል፡፡

ጄኔራል ታሪኩ ስለ ተወነጀሉበት የሠራዊቱ ገንዘብ በተመለከተ መቶ አለቃ ታደሰ በተብራራ መልኩ እንዲያስረዱ በዚህ መጽሐፍ አዘጋጅ ተጠይቀው ሲያስረዱ፣

‹‹እኔ በወቅቱ አሥመራ የክፍለ ጦር ወታደራዊ የፖለቲካ መምሪያ ተወካይና የፖለቲካ ኃላፊ ነበርኩ፡፡ በአሥመራ ዕዝ ውስጥም ከፍተኛ ሚና የነበረኝ ሰው ነኝ፣ ከጄኔራሎቹም ጋር ቀረቤታም ነበረኝ፡፡





‹‹ጄኔራል ታሪኩ፣ በእውነት ነው የምለው እንኳን የሠራዊቱን ገንዘብ ሊጠቀሙ፣ከፍቅር ብዛት ገና ከአፍበት ተንቃንቀዋል ሲባል፣ አልጋ ይይዙላቸው የነበሩት የሠራዊቱ አባሎች ናቸው፡፡ ይጠጡት የነበረው ቢራ ነበር፣ ቀድመው ለሁለት ሦስት ካሳ ቢራ ከፍለው ይጠብቋቸው ነበር እንጂ ታሪኩ አሥመራ ገብተው ከኪሳቸው ገንዘብ አውጥተው ሲዝናኑ አይቼ አላውቅም እኔ፡፡

‹‹ጋባዥች ሲቪሎችም ጭምር ነበሩ፡፡ በበላይ አለቃነቻው ሳይሆን ከፍቅርና ከአብክሮት በመነጨ ስሜት ነበር፡፡ እሳቸውም ሠራዊቱን ‹ልጆቼ ናቸው…እኔ ልጆቼን ጥዬ አሥመራ አልውልም…አዲስ አበባ አልሄድም….› በሚል ስሜት ከሠራዊቱ ጋር የተቆራኘ ሕይወት ነበራቸው፡፡

‹‹የሠራዊቱን የክበብ ገንዘብ ተጠቅመዋል የሚሉት እውነት ከሆነ፣ በሀቅ ከሆነ፣እኔ ስለ ታሪኩ ከጄኔራል ረጋሣ ጂማ ከሌሎችናከመንግሥቱ ኃይለ ማርያም የተወሰነባቸውን ሰነዶችን አሰባስቤያለሁ፡፡

‹‹በተለይ ብ/ጄኔራል ታደሰ ተሰማ የተባሉት ጄ/ታሪኩ የሠራዊቱን የክበብ ገንዘብ ተጠቅመዋል ተብሎ በተወራባቸው ጉዳይ ላይ እንዲያጣሩ ታዘው አፍአበት ሄደው ከአጣሩ በኋላ ሲመለሱ፣ ለጄኔራል ረጋሣ ባቀረቡት ሪፖርት ዜሮ አምስት ሣንቲም ጭራሽ እንደሌለባቸው አረጋግጠዋል፡፡

‹‹ነገር ግን ለጦር ኃይሎች ስፖርት ፌስቲቫል፣ ለዋልያ ስፖርት ክለብ እሥመራ ለነበረው፣ ለናደው ዕዝ ስፖርት ክለብ ተብሎ እሥመራ የነበረው የስፖርት ኮሚቴና በመንግሥት መመሪያና በተላለፈው ውሳኔ መሠረት፣ ከናደው ዕዝ ክበብ ገንዘብ ላይ ሁለት ሚሊዮን ብር ከሌሎችም ብርጌዶች ክፍለ ጦሮች ሁሉ እንዲዋጣ በታዘዘው መሠረት ጄ/ታሪኩ ያንን የሁለት ሚሊዮን ብር ቼክ ፈርመው ለስፖርት እንቅስቃሴ እንዲከፈል አድርገዋል።

‹‹በተረፈ ታሪኩ ሣንቲም ከሠራዊቱ ገንዘብ እንዳልነኩ እመሰክራለሁ። ታሪኩም በዚህ እንደማይገለጹ እዚያ የነበረው የክበቡ ኮሚቴ አረጋግጦላቸዋል። ይህም ሰነድ በእጄ ላይ አለ። ከዚያም ጄ/ረጋሣ የጻፉበት ሪፖርትም በእጄ ላይ አለ።

‹‹ስለጄኔራል ታሪኩ ይጻፉ የነበሩ በርካታ ሰነዶች በእጄ ስለሚገኙ እውነቱን ማረጋገጥ ይቻላል። ስለዚህ ዜሮ አምስት ሣንቲም የሠራዊቱን ገንዘብ አልነኩም። እሳቸው ስለሞቱ እኔ ስላለሁ አይደለም፣ ሀቅ ነው። እንዲጣራ ያስደረገውም፣ ያጣራውም ጠላቶች ነበሩ። ለማስገደል ሄደው የነበሩት አጣሪ ጄኔራል፣ ሠራዊቱን ሰብስበው፣

‹ጄኔራል ታሪኩ የሠራዊቱን ገንዘብ በተመለከተ ምን እያደረጉ ነው? በማለት በጠየቁበት ጊዜ፣ ‹‹ታሪኩ አባታችን ነው…… እሱ ከመጣ ወዲህ ነው ለችግራችን መፍትሔ ያገኘነው… ሹመትም፣ የጡረታ መብትና የአስተዳደር መፍትሔም ያገኘነው በሱ ነው….›› በማለት ሠራዊቱ መስክሮላቸዋል።





‹‹ለታሪኩ ሞት ዋናዎቹ የፖለቲካ ኃላፊዎች፣ ደኅንነቶችና የካሣዬ አራጋው ፖርቲ እንዲሁም የክቡር ዘበኛ ጄኔራሎች ናቸው። እነዚህ ሰዎች ታሪኩ ካልተገደለ እንደልባችን አመራር ልንሰጥ አንችልም በሚል ጥላቻና ቂም ተሞልተው በቅድሚያ ተሰብስበው ሴራውን አደራጅተው መንግሥቱ ሲደርሱ የመንግሥቱን ጭንቅላት በሀሰት ውንጀላ ሰውጠው ወደ አሳዛኝና አሳፋሪ ውሳኔ እንዲገቡ አድርገዋል።

መንግሥቱም ጄኔራል ታሪኩን ካስገደሉ በኋላ ከፍተኛ ቁጭት ውስጥ ነው የገቡት። ከግድያው በኋላ ጄኔራሎቹን አዲስ አበባ ቤተ መንግሥት ውስጥ ሰብስበው በስም ጠርተው፣ መርዕድ…ሥዩም….ተስፋዬ ገብረኪዳን…እገሌ….
እገሌ…. ብለው ከጠሩ በኋላ ታሪኩን የገደለች ጥይት መጀመሪያ በእናንተ ውስጥ ማለፍ ነበረባት። ሥጋችንን በጥርሳችን እንድንበላ ያደረጋችሁ አረመኔዎች ናችሁ። ያሉበት ሰነድ አጀንዳው ራሱ አለ።

ይኼ ማለት መንግሥቱም በታሪኩ ሞት መቆጨታቸውን ያሳያል። ፖለቲካ ሆኖ ለመሸፋፈን ይሞክሩ እንጂ ታሪኩን ከምሥራቅ ጀምሮ ያውቁአቸዋል። ጄኔራል ታሪኩ ቅድም ያልገለጽኩት አንድ ባህሪ አላቸው። ዝርክርክ ሰው አይወዱም። በአለባበሱ፣ በአበላሉ በወታደራዊ አቋሙ ዝርክርክ ሰው አይወዱም። እንኳን መደበኛ ሠራዊት ሚሊሺያው ልብሱን ተኩሶ እንዲለብስ የሚያደርጉ ነበሩ። ኮስታራ ሆኖ እንዲታይ፣ ከተማ ገብቶ ሲወጣም ወታደራዊ ክብሩን እንዲጠብቅ የሠራዊቱን ሥነ ልቦና ንቃት ከፍ ያደረጉ ነበሩ።

‹‹እነ ጄኔራል ረጋሣ ጂማ ደግሞ በቀን በጠራራ ፀሐይ የልጅ ልጃቸው የሆኑትን ሴቶችን ወደ ቃኘው ግቢ በተለያየ

መኪና ሲያመላልሱና በክበብ ገንዘብ እንደፈለጉ ሲጠቀሙ ስለነበረ ታሪኩ ብቻ ሳይሆን መላ ሠራዊቱ ይቃወም ስለነበረና ታሪኩም ይህ አግባብ አይደለም ብለው በግልጽ በመናገራቸው ከጠላቶቻቸው ጥርስ ገብተዋል። በዚህም በሀሰት ውንጀላና የቡድን ሴራ በጥድፊያ እንዲገደሉ ተደርጓል።

ጀኔራልን የሚያህል ከፍተኛ የፖለቲካ ውሳኔ የሚያስፈልጋቸውን ሰው የክበብ ገንዘብ አጠፉ በማለትና ሌሎችም የሀሰት ውንጀላዎች በመደፍደፍ መግደል ታሪክ እና እውነት እያጠሩ የሚያሳዩት ሰይጣናዊ ሥራ ነው።

‹‹ከመንግሥት በጀት ላይ አጭበርብረው ቪላ ቤት የሠሩ፣ ልጅ ልጆቻቸውን ውጭ አገር ልከው የሚያስተምሩ እንደነበሩ ኮ/መንግሥቱ ያውቃሉ። በሞተ በከዳ የጦሩን ገንዘብ ሲዘርፉ ለምን መንግሥቱ አልገደሉዋቸውም? እንደዚህ ጥቅም የሚያስገድል ከሆነ፣ ታሪኩ ደግሞ የጠላት አጣሪ ቡድን ራሱ ነፃ ናቸው ብሎ የመሰከረላቸው ናቸው። ዋናው የግድያቸው ምክንያት የፖለቲከ ሽኩቻ፣ የሥልጣን ሽሚያና ጥላቻ መሆኑ የተረጋገጠ ነው።

‹‹እኔ ጀኔራል ታሪኩ ሲያዙም እዚያው ነበርኩ።ሲታሰሩም ነበርኩ። ሲገደሉም ነበርኩ። እንግዲህ ማን ያርዳ የቀበረ፣ ማን ይናገር የነበረ እንደተባለው ያየሁትን ነው እያስረዳሁ ያለሁት። በግምትና ሳይሆን አይቀርም በሚል ሳይሆን እውነቱንና በዓይኔ ያየሁትን ነው የምመሰክረው።

‹‹ጀኔራል ታሪኩ ወደ አዲስ አበባ የካቲት 7 ቀን ሊበሩ የካቲት 6/80 ዓ.ም የአውሮፕላን ቲኮ ት ተቆርጦላቸው ነበር። ‹ታሪኩ መሄድ የለበትም፣....› በሚል ውትወታ እዚያው





አሥመራ እንዲቀሩና እርምጃ እንዲወሰድባቸው እነ ካሣዬ አራጋውና የክቡር ዘበኛ ጀኔራሎች ከፍተኛ ሴራ በማድረጋቸው የካቲት 6 ቀን ማታ ተይዘው የካቲት 7 ቀን እርምጃ ተወሰደባቸው።

ለጀኔራል ታሪኩ በተቆረጠው ቲኬትም ጀኔራል ከበደ ጋሼ ወደ አዲስ አበባ መጥተውበታል። ማንም ቢጠይቅ እሳቸውም አይክዱም፣ ቲኬቱ ጄ/ታሪኩ ዓይኔ ይላል እንጂ ጄ/ ከበደ ጋሼ አይልም። ሌላው ደግሞ ሰው ከሞተ ተመልሶ አይጠይቀንም የሚሉ ሕሊናቸውን የሸጡ ሰዎች፣ ጊዜያዊ ጥቅም ለማግኘት የሚያስቡ ኃይሎች፣ የአንድን ሰው ታሪክና ማንነት ሳያውቁ የዘለለ ሀሳብ ሊያስቀምጡ ይችላሉ።

‹‹ነገር ግን የአናብስት ምድር በሚል መጽሐፌ ላይ እንደጻፍኩት የጀኔራል ታሪኩን ሞት በሰነድ ምንም በማያወላዳ ሁኔታ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም በፊርማ የግድያ ትእዛዝ የሰጡበትን ሳይቀር ዝርዝር ሰነድ አውጥቻለሁ። አሁን ባዘጋጀሁት መጽሐፍ ደግሞ ጀኔራል ታሪኩ ከመገደላቸው በፊት እጃቸውን ታስረው በተሰበሰበው ሠራዊት ፊት ቆመው እንደነበረና ከተገደሉም በኋላ የተነሱት ፎቶ ለመንግሥቱ ኃይለ ማርያም በመሸኛ ደብዳቤ የተላከ ሰነድ አለኝ።

ይህ እንግዲህ በቂ ማረጋገጫ የሆነ፣ በአይኔ ያየሁትና በሰነድም በእጄ ያለ ነው። ሰዎች ግን በወሬ የሰውን ታሪክ ሲያጉድፉ እያየሁ አዝናለሁ። እኔ ግን ይህን በማስረጃ የተረጋገጠና የሚረጋገጥ ምስክርነት ስሰጥ ታሪኩን ስለማውቃቸው ሳይሆን ስሀቅና ስለሀቅ ብዬ ነው።

‹‹እስቲ እንግዲህ ጀ/ታሪኩ ተንኰለኛ ሆነው ከተገደሉ፣ ታሪኩ የሠራዊቱን ክበብ ገንዘብ ተጠቅሟል ተብለው ከተገደሉ፣ ወደ ኋላ መለስ ብለን ነገሮችን እንመልከት፡፡ እሳቸው በኃላፊነታቸው በሚሊዮን የሚቆጠር የመንግሥት ገንዘብ ፈርመው ያንቀሳቅሱ ነበር፡፡ ለምን የመንግሥትን ገንዘብ ዘረፉ ብለው አይከሱዋቸውም ነበር፡፡ የመንግሥት ገንዘብ ኦዲተር አለውና አልተመቻቸውም፡፡ ክበብ ደግሞ የሠራዊቱ ነው፣ ሠራዊቱ ነው ገንዘቤ ተበላ ብሎ የሚነሳ ወይስ መንግሥት ነው የሠራዊቱ ገንዘብ ተበላ ብሎ የሚከሰው፣

‹‹ክበብ ደግሞ ኮሚቴ አለው፣ አመራር አለው፣ከታሪኩ ጋር ምን ያገናኘዋል፣ ታሪኩ የክበብ ሊቀ መንበር አልነበሩም፡፡ የሠራዊቱ ገንዘብ ኦዲት እየተደረገ በየሁለት ወሩ በየሦስት ወሩ ለሠራዊቱ ይገለጻል፡፡ የሚገርመው ጀ/ታሪኩን ዝቅ አድርገው ከአንድ የክበብ ገንዘብ ጉዳይ ጋር ማያያዛቸው ነው፡፡

በሰባት፣ በስምንት ሚሊዮን የሚቆጠር የሠራዊቱን ደሞዝ ይፈርሙ ነበር፡፡ወታደራዊ በጀት እስከ 150 ሚሊዮን ይፈርሙ ነበር፡፡ ልምዱና ፍላጎቱ ቢኖራቸው ኖሮ ከዚያ ላይ አይጠቀሙም ነበር ወይ?

‹‹የክበብ ገንዘብ በላ ብለው የወነጀሉአቸው ጠላቶች የገንዘብ እንቅስቃሴውን አጣርተው ውሸት መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡ ጀ/ታሪኩ በባህሪያቸው ዝርክርክ ሰው አይወዱም ብያለሁ፡፡ በመንግሥቱም ሆነ በጀኔራሎች እምነት አልነበራቸውም፡፡ እምነታቸው በሠራዊቱ ነበር፡፡ መንግሥቱ ጀ/ታሪኩን አፍአበት ተወስደው በሠራዊቱ ፊት ይገደሉ ብለው ነበር የወሰኑት፡፡





‹‹ጀኔራሎቹ ግን አፍአበት ቢሄዱ አንዳቸውም ስለማይተርፉ፣ ሠራዊቱ ይገለናል ብለው ስለፈሩ አሥመራ ዙሪያ የነበረውን ሠራዊት ሰብስበው ነው አዲጉአዲድ በተባለው ቦታ የገደሉዋቸው፡፡ አፍአበት ቢወሰዱ ኖሮ ለመረሸን የሄደ አንድም አይመለስም ነበር፡፡ ወይም ታሪኩ አይገደሉም ነበር፡፡ እርግጠኛ ስለነበርኩ ነው፡፡

‹‹እና ይሄን ያህል የፖለቲካ ሽኩቻ በነበረበት ሁኔታ ላይ ጀ/ታሪኩ በወዳጅ ጠላት ቢሞቱም ታሪካቸው ግን አይሞትም፡፡ ስማቸውም ታሪኩ ነው፣ ታሪካቸውም ትልቅ ነው፡፡ ነገ በልጆቻቸው ወይም በልጅ ልጆቻቸው ታሪካቸው ተጽፎ ወጥቶ እናነብ ይሆናል፣እኛም ደግሞ በዓይናችን ያየነውን እናስፍራለን፡፡ እውነተኛ ምንጮች በመጡ ቁጥርና ሀቁ እየጠራ ሲመጣ ከዚህ በፊት መሠረት የሌለው አሉባልታ የጻፉ ሰዎች ያፍሩበታል፡፡ ለካ የጻፍኩት በውሸት ላይ ተመርኩዤ ነው፣ ምንም መረጃ አልነበረኝም ብለው ይቅርታ እስከመጠየቅ ይደርሳሉ ብዬ አስባለሁ፡፡ ምናልባት ሀሰተኛውን ውንጀላ እንዳለ በመቀበል የጻፉት ከመረጃ እጥረት እንዳይሆን የሚል እምነት አለኝ፡፡

የጀኔራል ታሪኩ ታሪክ ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለመጪው ትውልድ በብቃት እንዲቆይና የሳቸው ጠላቶች ደግሞ ምን ያህል ተልካሻና ምን ያህል አሳሳች ሰዎች እንደሆኑ የዓለም ሕዝብ ጭምር የሚረዳበት ሥራ እንዲሠራ እመኛለሁ፡፡›› በማለት እውነትን ይዘው በግፍ ስለተገደሉት ጀኔራል ታሪኩ ያላቸውን ቁጭትና ልባዊ ሀዘን በሰፊው ገልጸዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ፣

የጀኔራል ታሪኩ የግፍ ፍፃሜ እንኳን በአማርኛ በእንግሊዝኛ ትርጉምም እንዲጻፍና እንዲሠራ፣ በቀጣይ በትያትርና በድራማም ተሠርቶ ትውልድና ዓለም እንዲማርበት፣

ታሪካቸውም እንድ እውነተኛ ጭብጥ እንዲያገኝ ቤተሰቡ ቢያደርግ እሳቸውም መረጃ በመስጠት፣ ወታደራዊ ጉዳዮችን በማሟላት፣ በገንዘብም ይሁን በአካል፣ በአዕምሮም ይሁን አቅማቸው የሚፈቅደውን ለማድረግ ወደኋላ እንደማይሉ፣ ለቤተሰባቸውም፣‹‹እኔ ከጐናችሁ ነኝ፣›› በማለት ቃል ገብተዋል።

በወቅቱ ያንን በጄኔራል ታሪኩ ላይ የተፈፀመውን የግፍ ውሣኔና ድርጊት የሰሙት የናደው ዕዝ ሠራዊትና ሌሎችም የጦር አባላት ከባድ ሀዘንና ቁጣ እንደተሰማቸው ተገልጧል። ያም እንስሳዊ ውሣኔና ድርጊት የታሪክን ሂደትና አቅጣጫ የለወጠ አሳዛኝና አሳፋሪ ክስተት ነበር።

በዚያ ታሪክ በአሳፋሪ ሁኔታ በተለወጠበት ወቅት፣ የእውነተኛውን ጀግና በግፍ መገደል በተመለከተ የሻዕቢያ ሬዲዮ ጣቢያ ‹‹....ደርግ እጁን በእጁ ቆረጠ..... የማዕዘን ድንጋይ የነበረው ሰው ተነቀለ።›› የሚል የደስታ ዜና አሰራጭቷል።

ያ የግፍ እርምጃ ከተወሰደ በኋላ እነ ጄኔራል ረጋሣ እንዳቀዱት በጄኔራል ታሪኩ ምትክ ብ/ጄኔራል ውበቱ ፀጋዬ ተሹመው አመራሩን ያዙ። እኒህ ጄኔራል ‹‹አይታዘዝም...... እምቢተኛ ነው.....›› የሚል ሪፖርት በጄኔራል ታሪኩ ላይ አቅርበው የወነጀሉና የግድያውን ሂደት ያከናወኑት ናቸው። ከጥቂት ጊዜ ቆይታ በኋላ የሻዕቢያም ግፊት እየጨመረና ፍጥጫው እየጠነከረ ሄደ። ብዙም ሳይቆይ ሌላ ወሳኝ የፍልሚያ ሁኔታ ተከሰተ።

መጋቢት 8 እና 9 ቀን 80 ዓ.ም የሞት የሽረት ትንንቅ ተደረገ። ሆኖም የናደው ዕዝ ተመታ። በመቶ አለቃ ታደሰ ቴሌ ስልባኖ መረጃ መሠረት፣ ጄኔራል ፀጋዬም ዕዙን በትነው በመሸሽ፣ በመንገድ ላይ ያገኙትን ዘላን ልብስ አስወልቀው በመልበስና ሻሽ በማሰር፣ሙስሊም በመምሰል፣ እንዲሁም ግመል በመቀማት፣ መጋቢት 10 ቀን 1980 ዓ.ም ከረን ገብተው ከወገን ጦር ተቀላቅለው ራሳቸውን ሲያተርፉ ሠራዊቱን ለዕልቂት አጋልጠውታል።

*(የአናብስት ምድር፣ ገጽ 368)*





የናደው ዕዝ ሠራዊትም በጄኔራል ታሪኩ የግፍ ሞት በማዘኑና ሞራሉ በመነካቱ በብ/ጄኔራል ውበቱ ሥር ተሰልፎ የአቅሙን ያህል ሲዋጋ እንዳልቻለና ለሽንፈት መዳረጉንና ከሞት የተረፈውም በየአቅጣጫው ዕዙን ለቆ እንደተበተነ ፀሐፍቱ ዘግበውታል።

የጄኔራል ታሪኩን የግፍ ሞት በተመለከተ በሥራ ምክንያት በቅርብ እንደሚያውቋቸው የገለጹት ብ/ጄኔራል ዋስይሁን ንጋቱ፣ የምስክርነት ቃላቸውን በዕጣ ፋንታ የታሪክ መጽሐፋቸው ላይ እንደሰጡት፣ ‹‹.....በወታደራዊ ሳይንስ የተካኑትና የኤርትራና የኦጋዴን ጀግና የነበሩት፣ ጀግናው ብ/ጄኔራል ታሪኩ ዓይኔ በአምባገነኑ የደርግ መንግሥት ግብታዊ ትዕዛዝ በአሥመራ ከተማ በአሳዛኝ ሁኔታ በጦሩ ፊት ያለፍርድ ተረሸኑ›› ብለዋል።

እንግዲህ የጉዳዩ ሥርና ሂደት ይህ ሆኖ ሳለ ለጄኔራል ታሪኩ ሞት ተጠያቂ የሆኑት፣ ከመሪው ጀምሮ በፖለቲካውና ወታደራዊ ዘረፍ የነበሩት ባለሥልጣናት ወንጀላቸውን ለመሸፈን የሀሰት ታሪክ ለማውራት ሲቅለበለቡ ታይተዋል። አንዳንድ ፀሐፍትም ባልነበሩበት ሥፍራና ጊዜ ለተከናወነው የግፍ ድርጊት ሽፋን የተሰጠውን ውንጀላ እንዳለ በመውሰድ፣ ጄኔራል ታሪኩን አብረው በመወንጀል ታሪክ ጽፈው አስነብበዋል።

‹‹አሉ›› በሚል መሠረተ ቢስ ወሬ የሰው ስም ጥላሸት መቀባትና የሰውን ድካም መቅበር ከገዳይነት የማይተናነስ ወንጀል ነው። ይሁንና እውነት ስለማትሞት ሀቁ በታወቀ ቁጥር ወሬኞች በትዝብት እየቀለሉ መሄዳቸው እየታየ ነው።

ጀግናው ጄኔራል ታሪኩ፣ ይወዱት በነበረው ወታደራዊ ሙያ ለእናት አገራቸው ሕልውናና ሰላም ለ32 ዓመታት ከአንዱ ወደ ሌላው አውደ ውጊያ ያለ ማሰልቸት እየተዘዋወሩ የዜግነት

አገልግሎታቸውን ቢያበረክቱም የኋላ ኋላ ወሮታቸው ሞትና ንፁሕ ደማቸውን በአረመኔዎች ማፍሰስ ነበር። ይህን ዓይነቱ ከሥልጣን ጥማት የመነጨ ግፍ፣ በአገራችን በዘመናት ውስጥ በሌሎችም ጀግኖች እንደተፈፀመ የቆራጡን የበላይ ዘለቀን ታሪክ ልብ ይሏል።

እንደተጻፉት ታሪኮች ጭብጥ፣ በአለባበስ ይሽቀረቀሩ፣ በሽቶ ይታጠቡ፣በከተማ ኑሮ በምቾት ይንደላቀቁ፣ ከሥልጣን ቁንጮ ላይ ይንፈላሰሱ የነበሩት ባለሥልጣናት የሠራዊቱንና የአዛዦቻቸውን ከባድ የትግል መስዋዕትነት የመረዳትና ችግራቸውን የማስተካከል ብቃት አልነበራቸውም። ሠራዊቱንም እንደ አጥር ጠባቂ ውሻ በርቀትና በንቀት ይመለከቷቸው ነበር።

ስለዚህም እንደ ሰፊው ሠራዊት ሁሉ ጄኔራል ታሪኩም ሰብአዊ መብታቸው ተረግጦ የሕክምና ዕድል እንኳን ተነፍጐአቸው፣ በመጨረሻም አረመኔያዊና እንስሳዊ ውሳኔ ተላልፎባቸዋል።

ኢትዮጵያችን ሆድዋ ዥንጉርጉር ስለሆነ፣ ቅንና መሠሪ፣ ጀግናና ፈሪ፣ ሀቀኛና ከሀዲ፣ ቁምነገራምና ቅሌታም፣ ታታሪና ሰነፍ፣ አስተዋይና ግልብ፣ሆዳምና ኩሩ፣ ጨካኝና ርኅሩኅ ....ወዘተ እየዘነቀች መውለዷ በሕይወት አውድና በታሪክ ምስክርነት ፊት በሥራቸው በሚጠቀሱ ሰዎች ተግባር ይታወቃል። በዚህም ምክንያት ምድሪቱ ግፍ ባፈሰሳቸው በበርካታ ክቡርና ንፁህ የልጆቿ ደም ረስርሳለች። ያም ደም ወደ ፈጣሪ መጮኹ አይጠረጠርም።

በተፈጥሮ ፀጋዋና ውበትዋ፣ በሌሎችም በቂ ምክንያቶች መነሻነት ቅኝ ገዥዎች የሚቋምጡላትና ነገር ግን ሊያገኙዋት ያልቻሉት አገራችን፣ ታሪኳ ከጦርነት ጋር የተቆራኘ ነው። ነፃነቷም ከዚሁ ጠንካራ ጦርነት እሳት ውስጥ የተፈለቀቀ ክብርና ሕልውና ነው።

በቅርቡ የአሳለፍነውን የደርግ መንግሥት ዘመን ገመና ስንመለከት የእርስ በርስ ደም ያጐረፈ፣ ውድ ሕይወት የረፈረፈ የጦርነት መቅሠፍት መድረክ እንደነበረ እናስታውሳለን። የዚያን ዘመን ኢትዮጵያዊም ከአያት ቅድመ አያቶቹ በወረሰው አደራና





ኃላፊነት መሠረት፣ የአገሩን አንድነትና ድንበር ለማስከበር በሚል አንጡራ ምክንያት፣ ከአገሩ በፊት ራሱን ለመሰዋት ቆርጦ የተሠማራ ነበር።

ለነገሩ፣ የኢትዮጵያ ሠራዊት በየትኛውም ዘመን የአገሩን አንድነት፣ የወገኑን ክብርና ታሪክ ለመጠበቅ ሲል እስከ መስዋዕትነት ሊፋለም ወደ ልዩ ልዩ የትንንቅ ጐራዎች ሲጓዝ በሚገርም ደስታና በልበ ሙሉነት እንደሆነ የጠላትም ስንክሳር የየዘመኑን የኢትዮጵያውያንን ትግልና ድል ሲያወሳ ይመሰክረዋል።

የጠንቁ ሥር እጅግ ረዥም የሆነ ውና የመሠሪዎቹ የቅኝ ገዥዎች ምኞት የተበተበው፣ በተለይም የእንግሊዝ ሴራ ሸርና ክፋት የቆላለፈው እየቆየ የሚፈነዳ የተንኮል ቦምብ አካላችን ኤርትራን የመቅሠፍትና የሞት ምድር እንድትሆን አድርጓት ኋላም ነጥሎአታል።

ሕሊናቸው በቅኝ ገዥዎች ስብከት የተሞላው የማንነትን ክብርና መሠረት የማያውቁ፣ ግላዊ አጀንዳቸውን በጥንቃቄ ቀምረው፣ ነገር ግን አገራዊ ጉዳይ አስመስለው የተነሱ የወገን ጠላቶችና ወንበዴዎች፣ ለሰላሳ ዓመታት ያህል ሲዋጉና ሲያዋጉ በርካታ ውድ ሕይወት በከንቱ እንዲከስም ምክንያት ሆነዋል። ይህ ጥፋትና ክስረት ሲደረግ የቆየው በዋናነት በወታደራዊው የዕዝ ሰንሰለት ውስጥ መረባቸውን ዘርግተው ወገናቸውንና የአገራቸውን አደራ ለጠላቶች ሲሸጡ በነበሩ የውስጥ ቦርቧሪ ባንዶች ምክንያት ነው።

በተለይም በደርግ የመጨረሻዎቹ ዘመን ግዙፍ የኢትዮጵያ ሠራዊት በኤርትራ ምድር ሰፍሮ የእጅ አዙር የቅኝ ገዥዎችን ፍልሚያና የወንበዴዎቹን ገሀድ ትንንቅ ሲያመክን ቆይቷል።

በ1980 ዎቹ መጀመሪያ ላይ በትጥቅ ትግል ከዳር መድረስ ያልቻለውን ትንንቅ በዘዴና በተንኮል ለማጠናቀቅ ያሰበው ጠላት፣ ሰብዕናቸው ልፍስፍስ የሆኑትንና ለጊዜያዊ ጥቅም የሚደለሉትን

የሠራዊት መሪዎች በሆዳቸውና ግላዊ ምቾታቸው በመደለል ሠራዊቱን መምታት ብቸኛ አማራጭ እንደሆነ በመረዳት ባደረጉት ድለላ ድልን ገዝተዋል።

በዚህም መሠረት እንደነ ብ/ጄኔራል ጥላሁን ክፍሌ፣ ብ/ጄኔራል ዓሊ ሐጂና ካፒቴን ፀጋዬ መኮንን ያሉ ከሀዲዎችና የታሪክ አተላዎች ሠራዊታቸውን ሸጡት።

በአንጻሩም የኢትዮጵያ ታሪክ ዕንቁ የሆኑት ጀኔራል ተሾመ ተሰማ፣ ሻለቃ ሮሪሣ ዳዲ፣ ሻምበል ሸዋን ታዬ፣ ሻምበል አዲሱ፣ ሻምበል ወንድወሰንና ሌሎችም አንበሶች በተንኮልና በክህደት ገመድ እየተጠለፉ ወደቁ። የማዕዘን ድንጋይ ይባል የነበረው በኃይል ድርጅት ግዙፍና በሙያ ሞገደኛ የነበረው ኃያሉ የናደው ዕዝም እንዲሽረሽርና እንዲበተን ተደረገ። ምድር በደም ጨቀየች ታሪክም ጉደፈ፣ አገር የሀዘንና የሀፍረት ከል አጠለቀች። ታሪኩም ታሪክ ሆነ።

አገርን ከገንጣይና ከአስገንጣይ ለማትረፍ በታቀደ የረዥም ጊዜ ጦርነት ውስጥ ሁለት ዓይነት አሰላለፍ እንደነበረ በማጠናቀቂያው ውጤት መሠረት ገሀድ ታይቷል። በእርግጠኛ የዜግነት ዓላማና ታማኝነት የተሰለፉና ከነዚህም አኳያ ስውር አጀንዳ በማንገብ በማስመሰል የተቀላቀሉ እንደነበሩበት ታሪክ አረጋግጧል።

ሀቀኞችና ከሀዲዎች ተደባልቀው በተሰለፉበት በዚያ የሰሜን የጦርነት ፍልሚያ የተመዘገበው ውጤት ዘግናኝና የታሪክ ጠባሳ ያተረፈ፣ አገርና ዜጎች የሞቱበት የ30 ዓመት ዘመቻ ‹ዘመቻ ከንቱ› ሆኗል። የሠራዊቱን አቅምና የእንቅስቃሴ ሁኔታ ይዘውት በነበረው የአመራር ቦታ ጠንቅቀው ያውቁ የነበሩት ከሀዲ መኮንኖች ለፀረ ኢትዮጵያ ወገኖች ምስጢር በማቀበል ትግሉ እንዲኮላሽ ጠንካራ አስተዋጽኦ ሲያደርጉ ኖረዋል።





ኢትዮጵያን በቅኝ ሲገዙ ተመኝተው የቀሩ ጥንተ ጠላቶቻችንም ስውርና ረዥም ክንዳቸውን በከሀዲያን ዜጎች ትከሻ ላይ ዘርግተው እስከ ቅርብ ጊዜ ተዋግተዋል። ጥቁርን በነጭ ላይ የበላይ ያደረገው የአድዋ ድል ሲያንገበግባቸው ኖሯልና በልዩ ልዩ የጦር መሣሪያ ግብዐትና የኢኮኖሚ ድጋፍ የስውር ደጀንነታቸውን አሳይተዋል፣ ወደፊትም ያሳያሉ።

በኢትዮጵያ ሠራዊት ውስጥ ሠርገው የገቡ የተገንጣይ አስገንጣይ ተላላኪዎች በእውነተኛ ኢትዮጵያውያን መኮንኖች ላይ የፈጠሩ ወንጀል በማቀነባበር ደካማ አመለካከትና ግልብ አስተሳሰብ በነበራቸው የደርግ ቁንጮ መሪ በማስመታት ሀቀኞች በግፍ እንዲገደሉ በማድረግ ታላቅና ሸርና አሻጥር ሲሠሩ ቆይተዋል።

ለዚህ ሰይጣናዊ ድርጊት ዋነኛው ማስረጃ «ዋ ምዕዋ» ላይ በማስረጃ የተደገፈው የመቶ አለቃ ታደሰ ቴሌ ሰልባኖ ምስክርነትና የታሪክ ጽሑፍ ታላቅ ማስረጃ ነው።

ሀገራችን ኢትዮጵያ ቆራጥና እውነተኛ ተቆርቋሪ ሕዝቦችና መሪዎች የተዋደቁላትና ነፃነትዋን አስጠብቀው እንዳቆዩዋት ሁሉ፣ ታሪክ ከነእድፋቸው ዘግቦ በአውደ ዘመን መዝገቡ ውስጥ ያስቀመጣቸው አምባገነን መሪዎችና ጀሌዎቻቸው በቅለው እንደከሰሙባት በግልጽ ያስነብበናል።

በማጭበርበርና በኃይል፣ አምባገነኖች ሥልጣን ይዘው በታዩባቸው ዘመናት ሁሉ ኢትዮጵያ ለሕዝቦቿ የመከራ መድረክ ሆና እንባና ደም የጐረፈባት፣ ሕይወት የታጨደባት፣ ፍትህና ሕግ የተጓደሉባት ምድራዊ ሲኦል ሆና ኖራለች።

እናም ኢትዮጵያችን፣ በእልፍ አዕላፋት ንፁሀን ዜጎች ደም የረሰረሰች የደም ምድር ናት። ተደጋግሞ እንደተነገረው የኢትዮጵያውያንን ደም በዕብሪት ያፈሰሱት ወራሪ ጠላቶቿ ብቻ አልነበሩም። በየዘመኑ የተነሱ፣ በዕውቀት ድህነት አስተሳሰባቸው የጫጩ፣ ጠባቦችና ራስ ወዳዶች እንዲሁም በበታችነት ስሜት መንፈሳቸው የሚቃጠል ጨካኞችም ጭምር ናቸው።

ይህች በጦርነት ስትንገላታ የኖረች አገራችን ለጥቃት ሳትንበረከክ በሕልውና መገኘቷ ቢያኮራንም በጦርነት ጉዳት ምክንያት ኋላ ቀርነትዋ የኂለኞች እንድንሆን በማድረጉ ደግሞ ይቆረቁረናል።

ይሁን እንጂ በምድሯ ውስጥ ሠርጎ አንድነቷን ያፀናው የዜጎቿ ደም ያስረፀው የኢትዮጵያዊነት መንፈስ ታላቅ ኃይል አለው። አሁን አሁን ግን ይህ ኃይል እየተሰለበና እየተቦረቦረ በመሆኑ ወራሹ ትውልድ አገር አልባ፣ ታሪክ አልባ ስደተኛ/ዲያስፖራ ሆኖ እንዳይቀር አስረካቢው ትውልድ ልጁን፣ ወገኑን የማስተማርና የማሳወቅ የዜግነት ግዴታውን መወጣት ያለበት ጊዜ ከምንጊዜውም አሁን እንደሆነ በግልጽ የሚታይ ነው።

---





# ምዕራፍ ፯

## ስለ ጀኔራል ታሪኩ ማንነት የተጻፉ <u>የተዛቡ አስተያየቶች፣</u>

1. የመጽሐፍ ርዕስ፣ ምስክርነት በባለሥልጣናቱ አንደበት

   ታሪክ ፀሐፊ ሻምበል ተስፋዬ ርስቴ

   የታተመበት ዘመን ግንቦት 2001 ዓ.ም

ሻምበል ተስፋዬ ርስቴ በደረሱትና ግንቦት 2001 ባሳተሙት ‹‹ምስክርነት በባለሥልጣናቱ አንደበት›› በሚለው መጽሐፋቸው ውስጥ ልዩ ልዩ ባለሥልጣናትን በመጠየቅ ስለ ጀኔራል ታሪኩ ዓይኔ ማንነትና ተግባር ጽፈዋል።

በጽሑፋቸው ውስጥ ከጀኔራል ረጋሣ ጋር የነበራቸውን ቅራኔ አጉልተው በማሳየት ክስ ደረጃ እንደደረሱ ቢገልጹም የክሱ መጨረሻ ምን እንደነበረ አልጠቀሱም። ይህም ያልተሟላ ዘገባ ጀኔራል ታሪኩን ጥፋተኛ ብሎ ከመፈረጅ የሚቆጠር ሆኖ የሚታይ አቀራረብ ነው። ይህም ሁኔታ በሚከተለው ጽሑፋቸው በግልጽ ተቀምጧል።

‹‹ታሪኩ ዓይኔ ከጀኔራል ረጋሣ ጂማ ጋር ጉንደር ውስጥ ተጣልተው ጦር ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ ተደርገው ነበር። ረጋሣ ጂማን በመናቅ፣ በማዋረድና በመጋፋት ነበር የተወነጀሉት።

‹‹ታሪኩ፣ መቀሌ ከተማ ውስጥም ከጀኔራል ከፈለኝ ይብዛ ጋርም ተጣልተው ነበር። ታሪኩ፣ ትዕቢተኛና ጥጋበኛ፣ መኰንን ነበሩ ይባላሉ። ነገር ግን ከሰዎች ጋር የሚጣሉት በአብዛኛው በግል

ሳይሆን፣ «ለጦር አዛዥነት ብቃት የላችሁም፣» በማለት እንደነበረ የሚያውቋቸው ይናገራሉ።»

ታሪኩ፣ ትዕቢተኛና ጥጋበኛ፣ መኮንን ነበሩ ይባላሉ። በሚል ሚዛኑን ባልጠበቀ የ‹አሉ› ወሬ ላይ በተመሠረተ ሁኔታ ታሪክ የጻፉት ሻምበል ተስፋዬ፣ አሉባልታውን እንደ እውነት በመቀበል፣

«...........ሰውን ያለ አግባብ ማዋረድና መዝለፉ ተገቢ ባይሆንም፣ አንዳንዶቹን መኮንኖች በአካል ቀርቦ የሚያውቅ ሰው፣ ለታሪኩ ዓይኔ አባባል እጅግ ከፍተኛ ግምት መስጠቱ አይቀርም።» ሲሉ የጄኔራሉን ተሳዳቢነት ያመኑበት መሆኑን በሚገልጽ ስሜት በመተቸት፣እንደገና የጄኔራሉ ዘለፋ ለተዘለፉት ሰዎች የሚገባቸው ነበር በማለት እርስ በርሱ የሚቃረን ሀሳብ አስፍረዋል።

«ጄኔራል ታሪኩ ዓይኔ ዘራፊ፣ትዕቢተኛና ሴሰኛ እየተባሉ ቢወነጀሉም፣ ያነጋገርኳቸው ከፍተኛ መኮንኖች፣ ታሪኩ ሙያውን የሚያውቅ፣ ተዋጊና አዋጊ ጄኔራል እንደነበሩ ይመሰክራሉ።» ብለዋል።

በዚህ ዘገባቸው ደግሞ ከላይ በጠቀሷቸው ወንጀሎች ሁሉ ጄኔራሉ ስማቸው መነሣቱን ጠቅሰው፣ ነገር ግን ይህ ስም የተሰጣቸው የትና እንዴት፣ እንዲሁም መቼ፣ በትክክል በፈፀሙት ድርጊት እንደሆነ መረጃ አላቀረቡም። ይህን ዓይነቱ በ ‹አሉ› ላይ የተመሠረተ አጻጻፍ መሠረት የሌለው ውንጀላ ከመሆኑም በላይ የአንባቢን መንፈስ የሚያጉድፍ መግለጫ ነው።

በዚሁ መጽሐፋቸው ላይ በሻምበል ተስፋዬ ተጠይቀው ስለ ጄኔራል ታሪኩ ማንነትና ተግባር ምስክርነታቸውን የሰጡት ብ/ጄኔራል ከበደ አርምዴ፣ ደግሞ፣





‹ታሪኩ ዓይኔ በሠራዊቱ በጣም ተወዳጅ የጦር መኮንን ነበር። ከፍተኛ የአመራር ብቃት የነበረው፣ ከተራ ወታደር እስከ ከፍተኛ መኮንኖች ጋር ተቀራርቦ መሥራት የሚችል፣ ነገር ግን ደካማ የሆኑ አዛዦችን ደግሞ በጣም የሚንቅ ሰው ነበር።» በማለት ብዙዎች የሚስማሙበትን እውነታ ተናግረዋል።
በማከልም።

«ጄኔራል ታሪኩ በሰሜን ግንባር፣ለረዥም ጊዜ በመሪነት በመሥራቱ የመልክአ ምድሩንና የአካባቢውን የውጊያ ስልት ያውቀው ነበር።የተዋጊውንም ጦር ችግርና ብሶትም ይረዳው ነበር።በሚመራው ጦርም ተቀባይነት ነበረው።......ከዚህም በላይ በታሪኩ ያለ ሕግ መገደልና በሌሎችም ምክንያቶች ያኮረፉ የኮሩ አባላት ድንገት ወደ ወንበዴው ከዱ። በዚህ የተነሣ፣ የአፋበት ግንባር ከታሪኩ ዓይኔ በኋላ ለአጭር ጊዜ እንኳን መቀጠል አልቻለም። ፈረሰ። ለውድቀታችን የመጨረሻው መጀመሪያ የአፋበት ውድቀት ሆነ።» በማለት ብዙዎች የመሰከሩትን እውነታ እሳቸውም አዳብረውታል።

*ምስክርነት በባለሥልጣናቱ አንደበት ከገጽ 280 እስከ 283*

በዚሁ መጽሐፍ ከገጽ 303 ጀምሮ የጄኔራል ታሪኩ ዓይኔን ቀደምት የአመራርና የውጊያ ተግባሮች በማንሳት፣ የሚከተለው ታሪክ ተጽፎ ይገኛል።

«የ501ኛ ግብረ ኃይል በጄ/ ታሪኩ እየተመራ ከጎንደር ተነስቶ ኢድህንና ኢህአፖን ድል እያደረገ ሁመራ ደረሰ። ከሁመራ በኋላ፣ከገንጣዮች ጋር እየተዋደቀ በጀብሀ ተሰብሮ በነበረው የመረብ ወንዝ ላይ ተገጣጣሚ ድልድይ በመሥራት እየተፋለመ በመግፋት የተሰነይ መስመርን ተከትሎ በመገስገስ•በድል አድራጊነትአቀርዳት ከተማ ገባ።» ካሉ በኋላ

‹‹ጄ/ታሪኩን የ503ኛ ‹ለ› ንዑስ ግብረ ኃይልን በተጨማሪ በመምራት በሴሮ በኩል ጠላቱን እየደመሰሰና መስዋዕትነት እየከፈለ መንዙንና ጻረና መግባቱን አብራርተዋል፡፡ ከዚያም በቁርጠኛ የጀኔራል ታሪኩ አመራርና በሠራዊቱ ጀግንነት በየምዕራፉ ከፍተኛ ውጊያ እየተካሄደ አዲ ቀይህና ደቀ መሀሪ ነጻ መውጣታቸውን ዘግበዋል፡፡

ሻምበል ተስፋዬ በጻፉት ታሪክ ውስጥ በጣም የሚገርምና በተለያዩ ምክንያቶች ሊተረጐም የሚችል ክስተት ተጠቅሷል፡፡ ያም ክስተት 503ኛ ‹ለ‹ ግብረ ኃይል ጦር በድል አድራጊነት ደቀ መሐሪ ሲገባ፣ የዘመቻ መምሪያ መኰንኑ ገብረክርስቶስ ቡሊ ደቀ መሐሪ በመሄድ ከጀኔራል ታሪኩ ጋር ፀብ መፍጠራቸው ነው፡፡

የፀቡ ምክንያት የጀኔራል ታሪኩ ጦር በፍልሚያና በግስጋሴ ላይ በነበረበት ወቅት የስልክ ግንኙነት አለማድረጉና የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴውን ለዘመቻ መምሪያው አለማሳወቁ ነበር፡፡ ጀኔራል ታሪኩ ከነበራቸው ልምድና ተሞክሮ በስልክ የሚደረጉ ሪፖርቶች በጠላት እየተጠለፉ ለጠላት ጥቅም መዋላቸውን ያውቁ ስለነበር እንዲደረግ አልፈቀዱም፡፡

ይህንን ውጤትና ድል ያስመዘገበውን የጀኔራል ታሪኩን ጥንቃቄ እንደ ጥፋት በመቁጠር ብ/ጀኔራል ገብረክርስቶስ ጀኔራል ታሪኩን ከኃላፊነት በታቸው አነሷቸው፡፡ ዘመቻውም በኰ/ል እስጢፋኖስ ቀጥሎም በኰ/ል ሰይፉ ወልዴ መሪነት ወደ ምፅዋ ቀጠለ፡፡

ሆኖም በጀኔራል ገብረ ክርስቶስ የተሳሳተ ውሳኔና ሹም ሽረት መንስኤ የተነሳ ጦሩ ድል ሆኖ ከባድ አደጋ ደረሰበት፡፡ በዚህ ጊዜ የዋናው ግብረ ኃይል አዛዥ ካሣ ገብረማረያም ተገደሉ፡፡





ከሳቸውም ጋር 26 ወጣት መኰንኖች በከንቱ የሕይወት መስዋዕትነት እንደከፈሉ ሻምበል ተስፋዬ በጽሑፋቸው አስፍረዋል፡፡

ያ ጥፋትና ታላቅ ክስረት የደረሰበት ሁኔታ የጄ/ ገብረክርስቶስን አመራርና አቋም ከጥርጣሬ ውስጥ የሚያስገባ ጭብጥ የማይሆንበት ምክንያት የለም፡፡

2. የመጽሐፍ ርዕስ፣ ነበር፣ ክፍል ሁለት
   ታሪክ ፀሐፊ ዘነበ ፈለቀ
   የታተመበት ዘመን 2001 ዓ.ም

<u>‹‹ የብ/ጀኔራል ታሪኩ ዓይኔ መገደልና የአፋበት ውድቀት››</u>

በሚል ርዕስ፣ ዘነበ ፈለቀ በ2001 ዓ.ም በነበር ክፍል ሁለት መጽሐፋቸው ላይ ታሪካዊ ዘገባ አስፍረዋል፡፡ በዚሁ መሠት፣

‹‹ሻዕቢያ፣ በሳህል አውራጃ ውስጥ በሚገኙ የናደው ዕዝ ክፍለ ጦሮች ላይ ከህዳር ወር 1980 መጨረሻ ጀምሮ ሰፊ የማጥቃት ዘመቻ ከፈተ፡፡ በተለይም ከህዳር 27 እስከ 30 ባሉት ሦስት ቀናት ውስጥ በ15ኛው ክፍለ ጦርና በ22ኛው ተራራ ክፍለ ጦር ላይ ጠንካራ በትር አሳረፈ፡፡ ይህ ከቀይ ኮከብ ዘመቻ በኋላ የመጀመሪያው ጠንካራ እርምጃው ነበር፡፡ በዚህ ወቅት የናደው ዕዝ አዛዥ ብ/ጀኔራል ታሪኩ ዓይኔ ለአለቆቻቸው ሳያሳውቁ የዕዝ መደባቸውን ትተው አሥመራ ነበሩ፡፡›› ብለዋል፡፡

ዘነበ ፈለቀ በዚህ መግለጫቸው ጀኔራሉ በዚያ ወሣኝ ወቅት አሥመራ መገኘታቸውን እንጂ የሄዱበትን ምክንያት አልገለጹም፡፡ ይህም ጥቅል አባባል ጀኔራሉን በግዴለሽነትና በመሳሰሉት አሉታዊ ግምቶች አንባቢዎች ጀኔራሉን እንዲፈርጁ የሚጋብዝና የሚያደናግር ነው፡፡

በመቀጠልም‹‹......በሁለቱ ክፍለ ጦሮች ላይ የደረሰው ውድቀት በ ‹‹ሆደ ሰፊነት›› እና በ‹‹ይቅርታ ታልፈው የነበሩትን የጄኔራሉን አሮጌ ጥፋቶች ሁሉ አዋራቸውን እየጠራረገ አደሳቸው፡፡›› ብለዋል፡፡

ዘነበ ፈለቀ ይህን እርግጠኛ የሚመስል ከባድ መግለጫ ሲጽፉ፣ የጄኔራሉ ቀደምት ጥፋቶች ያሏቸውን ጉዳዮች እንዳቸውንም ለማረጋገጫነት አልጠቀሱዋቸውም፡፡ ሆኖም ጄኔራሉ ጥፋተኛ እንደሆኑ ማመናቸውንና አንባቢም ይህንኑ እንዲቀበል የፈለጉ ይመስላል፡፡

በእርግጥ ጥፋተኛ ተብለው የተከሰሱበትና የታሰሩበትም ጊዜ ነበር፡፡ ይሁንና በጦር ፍርድ ቤት ተከራክረው በጨበጡት እውነት ነጻ ወጥተዋል፡፡ ለዚህም በርካታ መረጃዎች አሉ፡፡ መከሰሳቸውን እንጂ የክሱ ምክንያትና ውጤት ታክሎ አለመጻፉ ጽሑፉን ሚዛናዊነት የጐደለው አድርጐታል፡፡ ዘነበ ፈለቀ በመቀጠል፣

‹‹,..........ጄኔራሉ፣‹‹በኔ ላይ ጥላቻ አላቸው›› የሚሏቸው ሁሉ አጋጣሚውን ሰበብ አድርገውና የግል ባህሪያቸውን በልዩ ልዩ ትርጉም እየመነዘሩ ሊያጠቋቸው ተነሱ፡፡››

‹‹ብ/ጄኔራል ታሪኩ፣ በጦር አዛዥነት ብቃታቸው እምብዛም የኘሬዚደንት መንግሥቱን ዓይን የሳቡ አልነበሩም፡፡ ‹‹ከተመኛ ነው የሚል ግምት ስላላቸው ነው የሚል ግምት ስላላቸው ነው›› ይባላል፡፡

‹‹እንግዲህ እኝህ ሰው በብዙ ጥርሶች የተቀረፈጨጨ ሆነው እንደምን የአእምሮ እረፍትና የመንፈስ ሰላም ሊያገኙ ይቻላቸዋል? ስለዚህ በጽኑ መታመማቸውን ገልፀው ከኤርትራ ወደ መሀል አገር ዝውውር እንዲፈፀምላቸው ለሁለተኛ አብዮታዊ ሠራዊት አዛዥ





ለሜ/ጀኔራል ረጋሣ ጂማ በጻፉት ተደጋጋሚ ማመልከቻ ጠየቁ፡፡ ተገቢውን መልስ አላገኙም፡፡››

ያሉበት ይህ አንቀጽም፣ ጄኔራሉ ታመምኩ ማለታቸው ከነበራቸው የአለቆች ቅራኔ ለመራቅ ያቀረቡት እንደሆን እንጂ በእርግጥ መታመማቸውን የማይቀበል አንድምታ ሆኖ ተስሏል፡፡ ጽሑፋቸውን በመቀጠልም፣

‹‹የማመልከቻውን መልስ በመጠባበቅ ላይ እንዳሉ ኘሬዚደንት መንግሥቱ በናደውና በመክት ዕዝ ላይ የደረሰውን ውድቀት በአካል ተገኝተው ዘገባ ሊያደምጡና ቀውሱ የሚስተካከልበትን አመራር ሊሰጡ አሥመራ ገቡ፡፡

- ሌ/ጄኔራል ተስፋዬ ገብረኪዳን፣
- ሜ/ጄኔራል ኃይለ ጊዮርጊስ ሀብተ ማርያም፣
- ሜ/ጄኔራል መርዕድ ንጉሤ፣
- ሜ/ጄኔራል ረጋሣ ጂማ እና ሌሎችም የዕዝ አዛዦች፣

እንዲሁም ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሁሉ በተገኙበት በዕዞቹ ላይ የደረሰው ጥቃት መንስኤው ምን እንደሆነ ማድመጥና መመርመር ተጀመረ፡፡ የናደው ዕዝ አዛዥ ብ/ጄኔራል ታሪኩ ዓይኔና የመክት ዕዝ አዛዥ ብ/ጄኔራል ከበደ ጋሼ በስብሰባው ላይ ተገኝተው በዕዞቻቸው ላይ የደረሰውን ጥቃት መንስኤ ለማስረዳት ሞክረዋል፡፡

‹‹.....ይሁን እንጂ፣ ብ/ጄኔራል ታሪኩ መታመማቸውን በመጥቀስ የዝውውር ጥያቄ ማቅረባቸውንና በግል ጥላቻ የተነሣ አቤቱታቸው መልስ አለማግኘቱን፣ የውድቀቱም መንስኤ እርሳቸው

አለመሆናቸውን ለማስረዳት ሲጥሩ፣ ከታየባቸው ንዴትና ከሰነዘሩት ኃይለ ቃል በኂላ ነገሩ ሁሉ ተበላሸ።››

‹‹እርሳቸውና ብ/ጄኔራል ከበደ ጋሼ እውጭ እንዲቆዩ ተደርጎ ምክክሩ ሲቀጥል፣ ‹‹ጓድ ኘሬዚደንት፣ ጄ/ታሪኩ የናቀው እኛን ብቻ አይደለም፣ እርስዎም ላይ ከፍተኛ ጥላቻና ንቀት አለው....›› በማለት ጄ/መርዕድና ጄኔራል ረጋሣ በመቀባበል ነገሩን ሁሉ አወሳሰቡት።››

‹‹ከዚያ በኂላማ በኘሬዚደንቱ ዘንድ መልካም ነገሮች ሁሉ ጠፉ። ስለዚህ፣ በሠራዊቱ ደንብ መሠረት፣

- የጦር ፍርድ ቤት ሳይቋቋም፣
- ክስ ሳይቀርብባቸው፣
- እምነት ክህደት ሳይጠየቁ፣
- ማስረጃ ሳይመረመር፣
- ነቃሽ ሳይቆጠርና የግራ ቀኝ ክርክር ሳይካሄድ፣

ብ/ጄኔራል ታሪኩ ዓይኔ በሞት እንዲቀጡ፣ ብ/ጄኔራል ከበደ ጋሼ ማዕረጋቸው እንዲገፈፍ ተፈረደባቸው።›› በማለት ጄኔራል ታሪኩን በተመለከተ የጻፉትን ሀሳባቸውን አጠናቀዋል።

*(ከገጽ 141 እስከ 146)*





# ምዕራፍ ፳

## ስለ ብ/ጄኔራል ታሪኩ ማንነትና ተግባር የተጻፉ አዎንታዊ ተጨማሪ ምስክርነቶች፡

| | |
|---|---|
| የመጽሐፍ ርዕስ | የስደተኛው ማስታወሻ |
| ታሪክ ፀሐፊ | ተስፋዬ ገብረአብ |
| መጽሐፉ የታተመበት ዘመን | 2006 ዓ.ም |

በጄኔራል ታሪኩ ተግባርና ማንነት ብሎም ስለተፈፀመባቸው የግፍ ግድያ ሰፊ ትንተና በመስጠት የጻፈው፣ በኢትዮጵያ ጋዜጠኛ የነበረውና በስደት ላይ እንደሚገኝ የሚገልፀው ተስፋዬ ገብረአብ ነው። በ2006 ዓም በጻፈው ‹‹የስደተኛው ማስታወሻ›› መጽሐፉ ውስጥ በአብዛኛው ከብዙዎቹ ወታደራዊ ታሪክ ፀሐፍት ሀሳብ ጋር የሚስማማ ታሪክ ጽፏል።

ሰፊውንና ተራኪ እንዲሁም ስዕላዊ መግለጫውን ሙሉ በሙሉ በመውሰድ ለአንባቢ ተጨማሪ እይታ ይሰጣል በሚል እሳቤ እንደሚከተለው ቀርቧል።

ጥር 26፣ 1980 (ግ.አ.)

ከሰአት በሁዋላ፣ ኮሎኔል መንግስቱ ሃይለማርያም ከምፅዋ ወደ አሰብ በባህር ሃይል መርከብ በመጓዝ ላይነበር። በጉዞ መሃል የሬድዮ መልእክት መጣለት። አጭር ነበር መልእክቱ፣ "ውሳኔው ተግባራዊ ተደርጓል!" የሚል። ተግባራዊ የተደረገው ውሳኔ የጄኔራል ታሪኩ መገደል ነበር።

ኮሎኔል አምሳሉ፣ "የኤርትራ መዘዝ" በተባለ መፅሃፉ እንዳሰፈረው ከሆነ፤ ጄኔራል ታሪኩ መገደሉን ለፕሬዚዳንቱ ሪፖርት ያደረገው ብርጋድየር ጄኔራል ውበቱ ፀጋዬ ነበር። ይህ ጄኔራል በዚያኑ እለት የሁለተኛው አብዮታዊ ሰራዊት ተጠባባቂ አዛዥ ሆኖ ተሾሞአል።አዲስ የተሾመበትን ስራውን የጀመረው ጄኔራል ታሪኩን በመግደል ነበር።

ውበቱ ፀጋዬ እንደማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ፣ በጠዋት ወደ ቢሮው ገብቶ መደበኛ ስራውን ነበር የሰራው። አንድ መምህር ተማሪዎቹን በመርሃ ግብሩ መሰረት በቦታው ተገኝቶ ካላስተማረ ከስራ ይባረራል። ጄኔራል ውበቱ ያን ቀን ማለዳ የስራ ባልደረባውን መግደል የማለዳ ስራው ሆኖ ተገኘ። "በዚያን እለት እኔ በውበቱ ቦታ ብሆን ኖሮምን አደርግ ነበር?" ብዬ ራሴን ጠይቂያለሁ። "አላደርገውም!ሄሊኮፕተር አስነስቼ እኮበልል ነበር።"አልኩ። በርግጥ ቁጭ ብሎ ወሬ መቅደድ ቀላል ነው።

በዚያን እለት ውበቱ የታዘዘውን ባይፈፅም ኖሮ ከጄኔራል ታሪኩ ጋር ተደርቦ ይረሽን እንደነበር ግን ግልፅ ነው። በዚያም ተባለ በዚህ ጄኔራል ታሪኩ ከመረሸን የሚያመልጥበት እድል አልነበረም። ጄኔራል ውበቱ ሁዋላ በግንቦት ስምንቱ የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ተጠርጥሮ ታስሮ ነበር። ወያኔ አዲስ አበባን ለመያዝ አምስት ቀናት ሲቀረው ነፃ ወጥቶ ወደ አሜሪካ ሄደ።

የታሪኩን አገዳደል በተመለከተ ኮሎኔል አምሳሉ በመፅሃፉ በጨረፍታ ነካክቶታል። ከአስመራ ወጣ ብላ በምትገኘው አዲ ጓእዳድ ከተባለች ቀበሌ ወታደሮች እንዲሰበሰቡ ተደረገ። ለወታደሮቹ የተነገራቸው " ጓድ መንግስቱ ያነጋግሯችሁዋል።"የሚል ነበር።





ከስብሰባው ቦታ ሲደርሱ ግን "በቆራጡ መሪ" ፈንታ "ቆራጥ ያልሆኑ"ሁለት ጄኔራሎች እጆቻቸው የሁዋሊት ታስሮ ቀረቡ። ሁለተኛው ጄኔራል አልተረሸነም። ከበደ ጋሼ ይባል ነበር። ማእረጉ ተቆርጦ ብቻተባረረ። በዚህ የግድያና የማባረር ስነስርአት ላይ ኮ/ሌ አስራት የተባለ መኮንን ወረቀት አወጣና የጄኔራሎቹን ሃጢአት አነበበ።

ስለ ጄኔራል ታሪኩ የገለፀው እንዲህ የሚል ነበር፣

"የበላይ መመሪያ አይቀበልም። የክበብ ገንዘብ ለግል ጥቅሙ አውሏል።

ከሻእቢያና ከወያኔ ጋር ልዩ ግንኙነት ፈጥሯል..."
ከዚያም የእሩምታ ተኩስ ተሰማ።

ጋዜጠኛ ገነት አየለ ሃራሬ ሄዳ ስለዚሁ ጉዳይ መንግስቱን በጠየቀችው ጊዜ የብልግና ምላሽ ሰጠ፣

"...እንዴት እንዲገደል ነበር የተፈለገው? በጦር ሜዳ ላይ ጥፋት ያጠፋ ሰው የሚሞተው በጥይት ነው እንጂ በገመድ አይሰቀል? ሰራዊቱ ፊት ተረሸኑ የሚባለው...ትምህርት እንዲሆን ተብሎ ነው። አንዳንድ ደካማ ሰው በግፍ እንደተረሸኑ አድርጎ ያወራል። የሰው ዝቃጭ ሞተ ተብሎ ይታዘናል?"

መንግስቱ እንዲህ ያለ ንግግር መናገሩ አይደንቅም። ቃላቶቹ እንደ ጠባዩ ስድ ናቸው። መንግስቱ ወደ ስልጣን ከመምጣቱ በፊት በቡና ቤት አምባጓሮዎች እንደሚታወቅ የሚያውቁት ፅፈዋል። ባንኪ ላይ አጠገቡ ካለ ሰው ጋር ሰበብ ፈጥሮ የመደባደብ ልማድ እንደነበረው ይገልፃሉ። በአንፃሩ ጄኔራል ታሪኩ የቤተሰብ ሰው ነበር። ሁለቱ መኮንኖች በእውቀታቸውም ሆነ በጠባያቸው ወዲህና ወዲያ ነበሩ።

በሙያቸው መንግስቱ ግምጃቤት አካባቢ ይሰራ የነበረ ሲሆን፤ታሪኩ ከእግረኛው ሰራዊት ጋር ዘመቻ መኮንን ነበር።

ብርጋድየር ጄኔራል ታሪኩ ሲገደል፤ የናደው እዝ አዛዥ ነበረ።የጄኔራሉ የመገደል ወሬ እንደተሰማ፣ "ድምፂ ሃፋሽ" ተብሎ የሚታወቀው የሻእቢያ ሬድዮ፣ "ደርግ ቀኝ እጁን በግራ እጁ ቀርጥፎ ጣለው!"የሚል ዜና ማወጁ ይነገራል።

አረፈአይኔ ሃጎስ እፎይታ መፅሄት ላይ ባቀረበው መጣጥፉ፣"እኒህን ስመጥር ጄኔራል ደርግ ስለምን ገደላቸው?" ለሚለው ጥያቄ ያስቀመጠው ምላሽ አጥጋቢ አልነበረም። ርግጥ ነው፤ አረፈአይኔ ወደ ጄኔራሉ መኖሪያ ቤት ሄዶ ሰነዶችን መርምሮ ነበር። የጦር ሜዳ አጀንዳ ቸውን ጭምር ማግኘቱን ፅፎአል። በጄኔራሉ አጀንዳ ላይ ከሰፈረው መካከልም ቆንጥሮ አስነብቦአል።

ጥር 16፣ 1980 በጄኔራሉ አጀንዳ ላይ እንዲህ ሰፍሮ ነበር፣

"...በአሁኑ ጊዜ ሻእቢያ ሁለት እግረኛ ብርጌድ እና ሜካናይዝድ ብርጌድ በማዘጋጀት የትኛውንም አግጣጫ ለመምታትእየተዘጋጀ ነው። በደጋው እና ከአፍአበት ጀርባ ሁለት ብርጌድ አስቀምጧል። በከረን መንገድ አቆርዳት ላይ ሁለት ብርጌድ አሰልፎአል። በቀይ ባህር ዳርቻ አንድ የጠላት ብርጌድ፣ በምፅዋ መንገድ፣ በደቀምሃሬ ከተማ፣ አስመራ ደቀምሃሬ መንገድ፣ ፆረና፣ኳቲት፣ ማይናይ አንድ የጠላት ብርጌድ ለማጥቃት ተዘጋጅተዋል..." የጄኔራሉ ማስታወሻ የሻእቢያ ሃይል የማጥቃት የበላይነት መያዙን የሚጠቁም ነበር።

እንደ አረፈአይኔ ዘገባ ከሆነ ጄኔራሉ የተገደለው ከላይ ያለውን ስጋት አዘል ማስታወሻ ባሰፈረ ልክ በሃያ ቀኑ ነው። ጄኔራል ታሪኩ ከመገደሉ ጥቂት ወራት ቀደም ብሎ ከመንግስቱ ሃይለማርያም ጋር ዝግ





ውይይት አድርጎ ነበር። የተወያዩትንም ጄኔራል ታሪኩ ከመሞቱ በፊት ከበደ ጋሼ ለተባለው ጄኔራል አጫውቶት ነበር።

ጄኔራል ታሪኩ ለመንግስቱ ሃይለማርያም አንድ ግልፅ እውነት ነግሮት ነበር። ቃል በቃል እንዲህ አለው፣"የኤርትራን ችግር በጦርነት መፍታት የሚያስችል አጥጋቢ ሁኔታ የለም። ሰላማዊ መፍትሄ ቢፈለግ ይሻላል።"

አረፋይኔ እንደገመተው በዚህ አባባሉ ብቻ ኮሎኔሉ ጄኔራሉን ገድሎታል ለማለት አይቻልም። ጄኔራል ታሪኩ ያመነበትን ብቻ እንደሚናገር መንግስቱ ያውቃል። በ1973 ቤተመንግስት ውስጥ በተደረገ፣ "የኤርትራን ጉዳይ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መፍታት" በተባለ ርእስ ጉዳይ ላይ ሲወያዩ ጄኔራል ታሪኩ ልዩነት ፈጥሮ ነበር።

"ዘመቻው ኤርትራ ላይ ያተኩር" በሚለው አሳብ መንግስቱና ሌሎች መኮንኖች ሲስማሙ ታሪኩ አይኔ፣ "በቅድሚያ ህወሃትን ከትግራይ እናፅዳ" የሚል አቋም ይዞ ብቻውን ተነጥሎ መቅረቱን፣ ኮሎኔል አምሳሉ በመፅሃፉ ጠቅሶታል። "ጄኔራል ታሪኩ ከሻእቢያ ጋር ግንኙነት ነበረው።"የሚለውን መረጃ እራሱ መንግስቱም የሚያምንበት አይደለም። ኮሎኔል መንግስቱ ለገነት አየለ የነገራት፣ "ሰራዊቱ ጥርጣሬ ነበረው።" የሚል ነው።"የደህንነት ክፍሉ" ቢል እንኳ ክብደት ልንሰጠው በቻልን። "ሰራዊት ጠረጠረው"ማለት ምን ማለት ነው? በዚህ ያልተጨበጠ መረጃ ብቻ የአንድ ሃገር ጄኔራል ይረሸናል? በደፈናው፣ "በውስጣቸው በነበረ ሽኩቻ" ማለትም አይቻልም።

ርግጥ ነው የደርግ አለቆች በጦርነቱ ወቅት ሽንፈትበገጠማቸው ቁጥር አንዱን መኮንን በክህደት ወንጅለው በመረሸን ሰራዊቱን ለማረጋጋት ይሞክሩ ነበር። ለአብነት የቀይ ኮከብ ዘመቻን ሽንፈት

ምክንያት ውብሸት ማሞ የተባለ ኮሎኔል ጫንቃ ላይ ጭነው ረሽነውታል:: የሽንፈቱ መንስኤ ውብሸት እንዳልሆነ ግን ልቦናቸው ያውቀው ነበር:: እንዲህ ያለ ማምለጫ ቀዳዳ መፈለግ የተለመደ ነው:: በርግጥ የኤርትራ የጦር አዛዦች የጄኔራል ታሪኩን ግድያ ከዚህ አንፃር እንደሚያዩት ከአንዳንድ ቃለመጠይቆቻቸው ተረድቻለሁ:: አጥጋቢ ሆኖ ግን አልተሰማኝም::

ጀኔራል ታሪኩ አይኔ ጥር 10፣ 1928 በጨቦና ጉራጌ አውራጃ፣ጉሮ ወረዳ የተወለደ የገበሬ ልጅ ነበር:: በ1949 ከገነት መኮንኖች ትምህርት ቤት በምክትል መቶአለቅነት ተመርቆአል:: በ52 አመት እድሜው የተረሸነው ጄኔራል የአራት ልጆች አባት ነበር:: ይህ ስመጥር ጀኔራል ስለተገደለበት ምክንያት መፃህፍት ብዙ ብለዋል:: ሆኖም ሲባሉ ከኖሩት በተለየ፤ መንግስቱ ሃይለማርያም ያልተናገረው አንድ ግላዊ ምክንያት መኖሩ ይሰማኝ ነበር...

ገነት አየለ መንግስቱ ሃይለማርያምን ቃለ መጠይቅ አድርጋ ያሳተመችው መፅሃፍ ላይ የጄኔራል ታሪኩ አይኔ ጉዳይ የስምንት ገፆች ሽፋን አግኝቶ ነበር:: ኮሎኔል መንግስቱ ስለ ጄኔራል ታሪኩ ሲገልፅ ጥላቻውን መሸሸግ እንኳ አልቻለም:: ተራ አሉባልታ ነበር የሚናገር::

በአንድ በኩል ጄኔራል ታሪኩ ብዙ ጠላቶች እንዳሉት ይገልፃል:: መልሶ ደ'ሞ ጠላቶቹ የሚነዙትን አሉባልታ እንደ መረጃ ያቀርባል:: ለአብነት ህወሃት በሃየሎም አርአያ መሪነት የፖለቲካ እስረኞችን ከመቀሌ እስርቤት ሲያስለቅቅ፣ በወቅቱ ጄኔራል ታሪኩ ትግራይ ላይ የሰራዊት አዛዥ ነበር:: የመቀሌ ወህኒ ቤት በህወሃት አማፅያን ሲወረር፣ የወህኒ ቤቱ አዛዥ፣





"ወንበዴው ወሮኛል፣ እርዳታ ይደረግልኝ?" ብሎ ሲጠይቅ፤ ጄኔራል ታሪኩ እርዳታ በመላክ ፈንታ አልጋው ላይ ተኝቶ፣"እኔ የወህኒ ቤት ዘበኛ አይደለሁም"አለ::"ይለናል::

ይህን መረጃ ማመን ይቻላል? ምናልባት ድርጊቱ ከተፈፀመ በሁዋላ በነበሩ የመወነጃጀል ንግግሮች መካከል፣ ታሪኩ በአባባል ደረጃ ቃሉን ተጠቅሞበት ሊሆን ይችላል:: የሃየሎም ኦፕሬሽን በመፈፀም ላይ ሳለ ግን፣ ታሪኩ አልጋው ላይ ተኝቶ ያን የመሰለ ምላሽ ይሰጣል ተብሎ እንዴት ማመን ይቻላል? በርግጥ ያንን ብሎ ከነበረ፣ ለፍርድ መቅረብ የነበረበት ያን ጊዜ ነበር:: መንግስቱ ግን እንዲህ ያለ ድርጊት የፈፀመን ጄኔራል፣ ያለምንም ቅጣት፣ "የናደው እዝ አዛዥ አድርጌ ሾምኩት::" ብሎ ይነግረናል:: ለቅጣት ወደ ናደው እዝ መላኩን የፃፉም አሉ::

በርግጥ የናደው እዝ ሹመት ቅጣት ከነበረ፤ ጄኔራል ታሪኩን ወጥመድ ውስጥ አስገብቶ ለማጥፋት ፕሬዚዳንቱ ቀደም ብሎ ወስኖ ነበር ማለትነው::

መንግስቱ ከደርዘን ገፆች ንግግሩ መካከል ጄኔራል ታሪኩን ለመግደል ያበቃውን ምክንያት ማቅረብ አልቻለም:: ለአብነት ታሪኩን፣"የነጋዴነት ዝንባሌ ነበረው"በማለት ያጣጥለዋል:: ይህንንም ከጉራጌነቱ ጋር እንድናያይዝለት ፈለገ:: አስረጅ ሲያቀርብ ታሪኩን ልክ እንደ አንድሱቅ በደረቴ፣"ስላሳ ሳንቲም የሚሸጠውን ለስላሳ መጠጥ ለሰራዊቱ በአንድ ብር እየሸጠ፤ ከአንድ ለስላሳ ሰባ ሳንቲም አትርፎ ወደ ኪሱ ይከት ነበር::"ይለናል::

መንግስቱ ይህን የመሰሉ አሉባልታዎችን• በሰፊው ዘርዝሮ ሲያበቃ፣ ጄኔራል ታሪኩ ከሻእቢያ ጋር ስላደረገው ምስጢራዊ ግንኙነት በጨረፍታ ብቻ ነክቶት አለፈ:: አሉባልታውን ትቶ የጄኔራል ታሪኩንና

የሻእቢያን ግንኙነት ቢያብራራልን በተሻለ ነበር። በጥቂት ቃላት እንዲህ ሲል ነበር የገለፀው፣

"ታሪኩ ደህንነቱንና የፖለቲካ ድርጅቱን በማፈራረስ፣የሰራዊቱን ሞራል በማንኮታኮት ከጠላት ጋር በሚያደርገው ስውር ግንኙነት ብዙ ጥፋት አደረሰ።" አያይዞም፣ "ሰራዊቱ 'ይሄ ሰውዬ ከጠላት ጋር ግንኙነት ሊኖረው ይችላል' የሚል ጥርጣሬ አሳድሮአል።"ይላል። የግድያውን ፍትሃዊነት ለማሳመን፣ "ታሪኩ በመረሸኑ ስራዊቱ ደስታውን ገልፆአል።" ይለናል። የግድያውን ውሳኔ ከራሱ ለማላቀቅ ደ'ሞ፣ "ተስፋዬ ወልደስላሴ፣ መስፍን ገብረቃል፣ እና ስዩም መኮንን 'ታሪኩ መመታት አለበት'ብለውኛል።"ይላል።

(በርግጥ ኮሎኔል መንግስቱ በግላጭ የፈፀመውን ወንጀል እንደሚክድና ሌሎች ላይ እንደሚለጥፍ በተደጋጋሚ ታይቷል። ለአብነት የበአሉ ግርማን መገደል ለተስፋዬ ወልደስላሴ ሸልሞታል። የ60ዎቹን የአቤ ሃይለስላሴ ሹማምንት መረሸን ደ'ሞ ወደ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም እና ወደ ዶክተር በረከት ሃብተስላሴ ገፍቶታል። የአጥናፉ አባተን ግድያ የሚያስጠጋበት ቢያጣ "አብዮቱ በላው!"ብሎ ኮመከ። መቸም አገር ሲመራ የቆየ ሰው እንዲህ እንደ ሸውሽዌ ሲወዛወዝ መስማትና ማየት የሚያሳቅቅ ነው።)

ኮሎኔል መንግስቱ ሊነግረን እንደፈለገው፣ "ጀኔራል ታሪኩ ከሻእቢያ ጋር ግንኙነት ነበረው።" ለማለት የሚያበቃ መረጃ የለም።ግድያው የተፈፀመውም መንግስቱ እንደሚለው በወታደራዊ ፍርድ ቤትውሳኔ አልነበረም። በርግጥ ኮሚቴ ተቋቁሞ ነበር። የኮሚቴው ውሳኔ፣ "ጀኔራል ታሪኩ ሙሉ መብቱ ተጠብቆለት በጡረታ እንዲገለል።"የሚል ነበር። መንግስቱ የኮሚቴውን ውሳኔ በመተው የራሱን ርምጃ ወሰደ።





መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ጀኔራል ታሪኩ ላይ የተለጠፈበትን የከሃዲነት ክስ የተቀበለና ያመነ የሰራዊት አባል አልነበረም። የጀኔራል ታሪኩን ሰብእና ስንመዝነውም መንግስቱ ስሙን ሊያጠፋው እንደፈለገው አልነበረም። ጀኔራሉን በቅርብ የሚያውቁ እንደሚገልፁት ጀኔራሉ በሰራዊቱ በጣም ተወዳጅ መሪ ነበር። ከነበረው ዝና አንፃር፤ታሪኩ በመገደሉ የሰራዊቱ ሞራል በከፍተኛ ሁኔታ ተጎድቶ ነበር።

ጀኔራል ታሪኩ ከአስመራ ወጣ ብሎ በሚገኝ፣ አዲጓእዳድ ከተባለ ቦታ ከተረሸነ በሁዋላ፣ ሻእቢያ ናደው እዝ ላይ መብረቁን አወረደበት። ከአርባ በላይ ታንኮችና ከስድሳ በላይ መድፎችን የታጠቀው፣ በተሻለ ሁኔታ የሰለጠነው የናደው እዝ ሰራዊት በሶስት ቀናት ውጊያ ሙሉ በሙሉ ተናደ። በጀኔራል ታሪኩ እግር የተተካው ኮሎኔል ጌታነህ ሃይሌየሚወርድ በትን ቁምቡላ እሳት ተቋቁሞ፣ ሰራዊቱን አስተባብሮ መምራት አልቻለም። ታንኮቹና መድፎቹ ተማረኩ። አዲሽሩም ሸለቆ ውስጥ የነበሩ ከባድ መሳሪያዎችን ደርግ ራሱ አጋያቸው።........››

‹‹......ፕሮፌሰር ገብሩ ታረቀ በመፅሃፉ እንደገለፀው ከጀኔራል ታሪኩ መገደል በሁዋላ በተደረገው የአፍአበት ጦርነት 18 ሺህ ሙትና ቁስለኛ ተመዝግቦአል። ናደው እዝ በጥቅሉ የነበረው የሰራዊት ብዛት 22 ሺህ ነበር።

ናደው እዝ በሶቪየት ወታደራዊ ጠበብት የሚታገዝ፣"ጓድ" መንግስቱ የሚመካበት የታጠቀና የሰለጠነ ዘመናዊ ጦር ነበር።በውጊያው ሶስት የሶቪየት ወታደራዊ አማካሪዎች ሲማረኩ፣ አንድ ሩስያዊ መኮንን ሞቶ ተገኝቶአል። መጋቢት 17፣ 1988 ማለዳ ህዳይ ሸለቆ አካባቢ በሶስት አግጣጫ ማጥቃቱን የከፈተው የሻእቢያ እግረኛ ጦር፣ በሶስተኛው ቀን አፍአበትን ሙሉ በሙሉ ተቆጣጠራት። ታሪክ ፀሃፊው ባሲል ዴቪድሰን፣ ቬትናማውያን በዲያን ቢያን ፉ ፈረንሳይ ላይ ካስገኙት ድል

ጋር አነፃፅሮታል። ገብሩ ታረቀ በባሲል ዴቪድሰን በዚህ አባባል አይስማማም።.....››

‹‹......ኮሎኔል አምሳሉ በመፅሃፉ፣ "የኢትዮጵያ ሰራዊት ያንን መራራ ሽንፈት የተቀበለው በጄኔራል ታሪኩ በግፍ መገደል የተሰማውን ጥልቅ ቅሬታ በልቡ ይዞ በሞራል መዋጋት ባለመቻሉ ነው።"ይላል።

‹‹ሻእቢያ ናደው እዝ ላይ ማጥቃት መሰንዘሩ እንደተሰማ፣ተስፋዬ ወልደስላሴና ተስፋዬ ገብረኪዳን አስመራ መጥተው ጦሩን ለመምራት ሞክረው ነበር። መርእድ ንጉሴ፣ ደምሴ ቡልቶ፣ አምሃ ደስታ እና ሃይሉ ገብረሚካኤል የተባሉት ጄኔራል መኮንኖች በሶቪየት የውጊያ ጠበብት ምክር እየታገዙ ሻእቢያን ለማስቆም ቢሞክሩም፣ሰራዊቱ እየተገለበጠ መፈራረሱ ቀጠለ። ሶስት የኢትዮጵያ ኮሎኔሎች ውጊያው ላይ ተገደሉ። በርካታ ሻለቆችና መስመራዊ መኮንኖች ተማረኩ። አንድ ታንክና አራት ወታደራዊ መኪኖችን ይዞ ከረን ድረስ መሸሽ የቻለው ኮሎኔል ጌታነህ በህይወት በመትረፉ የአፍአበትን የጦርነት መረጃ ለታሪክ ፀሃፊዎች በመስጠት ታሪካዊ አስተዋፅኦ አድርጎአል...

‹‹ከአፍአበት ውጊያ መጠናቀቅ በሁዋላ በኢትዮጵያ መከላከያ መስሪያ ቤት በተደረገ ግምገማ፣ ለናደው እዝ ሽንፈትና መደምሰስ ምክንያት ተብለው ከተዘረዘሩት አምስት ነጥቦች፣ በሶስተኛው ተራ ቁጥር ላይ የተቀመጠው፣ "የናደው እዝ ሰራዊት 'ታሪኩ አይኔ በግፍ ተገድሎአል'ብሎ ማመኑ።"የሚል ነበር። በርግጥ የኤርትራ ወታደራዊ አዛዦች በዚህ ግምገማ አይስማሙም። ከሻእቢያ የዘመቻ መኮንኖች አንዱ እንደገለፀልኝ፣ "ታሪኩ ባይገደልም ናደው ዕዝ መደምሰሱ የማይቀር ነበር። ጄኔራል ታሪኩ ሊደነቅ የሚገባው ይህ ውጤት ሊመጣ እንደሚችል ተረድቶ፣'ወታደራዊ አማራጭ አያዋጣንም፣ ሰላማዊ መንገድ ብንመርጥ ይሻላል'ብሎ በማለቱ ነው።"





‹‹ጄኔራል ታሪኩ አይኔ በወቅቱ ከነበሩ ወታደራዊ መሪዎች የተሻሉ ከሚባሉት መካከል እንደነበረ ጠቁመውኛል። ከወታደራዊ ሳይንስ እውቀቱና ብቃቱ ባሻገር ጄኔራል ታሪኩ በሚመራው ሰራዊት ተወዳጅ መሆኑ የተለየ ያደርገው ነበር'ብለው ይላሉ። በርግጥ በጦርነት ወቅት አንድ ጄኔራል ቀርቶ አንድ ተራ ወታደርም ቢሆን ልዩነት ማስከተል ይችላል። ዞሮ ዞሮ ግን የጦርነት ውጤት የብዙ ግብአቶች ጥርቅም እንደመሆኑ አንድ ምክንያት ብቻ መስጠት ልክ አይሆንም።

‹‹በመጨረሻ "ኮሎኔሉ ጄኔራሉን ስለምን ገደለው?" ለሚለው ጥያቄ የራሴ ግምት አለኝ። ስለ ጄኔራል ታሪኩ የተፃፉትን ሰነዶች ሰብስቤ ሳነብ ትኩረቴን የሳበ መረጃ አግኝቻለሁ። መንግስቱ ስለ ጄኔራል ታሪኩ ሲገልፅ፣"ከአብዮቱ በፊት ወጣት መኮንን ሆኜ ኦጋዴን ውስጥ ሳገለግል፣ ጄኔራል ታሪኩ የዘጠነኛ ብርጌድ የዘመቻ መኮንን ከነበረ ጊዜ ጀምሮ አውቀዋለሁ..."ይላል።

‹‹በዚያን ወቅት የጄኔራል ታሪኩ ባለቤት ሐረር ላይ የመጠጥ ግሮሰሪ ቢዝነስ ነበራት። መንግስቱ ሃይለማርያም፣ ታሪኩ አይኔና ሌሎችም መኮንኖች ወደዚያች ግሮሰሪ ይመላለሱ ነበር። ቅዳሜ ምሽት ወጣቶቹ መኮንኖች በዚያች ባር ሲሰባሰቡ፣ መንግስቱ ሃይለማርያም ከጓደኞቹ ገለል ብሎ ብቻውን ጥግ ላይ ቁጭ ማለትን ያዘወትር ነበር። የወደፊቱ አጥፊና ጠፊ፣ በአንድ ጣራ ስር ያመሹ በነበረበት ዘመን በቅጡ ይተዋወቁ ዘንድ አጋጣሚ, ተፈጥሮአል።

‹‹ጄኔራል ታሪኩ "ለጓድ ሊቀመንበር መንግስቱ"ስልጣን ማጎብደድ አለመቻሉን መታዘብ ይቻላል። የጄኔራል ታሪኩ የህይወት ታሪክ ሲፈተሽ የኮሎኔል መንግስቱን የተወላገደ መንገድ እየተቸ ዘልቆአል። "ከጓድ መንግስቱ ሃይለማርያም' አብዮታዊ አመራር ጋር ወደፊት!" የሚለውን መፈክር እንደ ሃገሪቱ የህዝብ መዝሙር ከማለዳ

እስከ ምሽት እያስጨፈረ አሰርት አመታት የገዛው ኮሎኔል መንግስቱ በጄኔራል ታሪኩ ፊት ድመት ለመሆን በመገደዱ ተቸግሮ ኖሮአል።

‹‹በጥቅሉ ጄኔራል ታሪኩ በኤርትራ ጦርነት ጉዳይ የሰጠው አስተያየትለሞት የሚያበቃው አልነበረም። ስለ ኤርትራ ጦርነት ጄኔራሉ የሰጠው አስተያየት በፖለቲካና በወታደራዊ ሙያ ብቁ እንደነበር ነው የሚጠቁመን። በርግጥ ታሪኩ የሰጠው አስተያየት ለመንግስቱ ያስተላለፈለት መልእክት ይኖር ይሆናል። አገሪቱን መምራት እንዳልቻለ አይነት?

« የጄኔራል ታሪኩ አስተያየት የመንግስቱን ከኦጋዴን ጀምሮ የተቀበረ ቁስል ቀስቅሶበትም ይሆናል። ንቀት አይነት? እናም የኤርትራን ጦርነት በተመለከተ ከጄኔራል ታሪኩ የተሰነዘረው አስተያየት፣ የመጨረሻ ስንጥር ሆኖ የአህያውን ወገብ ሰብሮት ይሆናል። ሰዎች በተፈጥሮ የሚንቃቸውን ሰው ገድለውት እንኳ ርካታ አያገኙም።

‹‹ ርግጥ ነው፣ በዚህች አለም ላይ ንቀትን በፀጋ የመቀበል ችሎታ ያለው ሰው ሊኖር አይችልም። የሰው ልጅ የሚኖረው ለክብር ነው። ክብር ከሌለ ህይወት የለም። በመሆኑም ኮሎኔል መንግስቱ ታሪኩ አይኔ የተባለውን የወጣትነት ጊዜ የስራ ባልደረባውን በጥይት አስደብድቦ ለምን እንደገደለ በግልፅ መናገር ሳይቻለው ቀረ...»

*(ከገጽ 216 እስከ 225)*





## ሌ/ጄኔራል ተስፋዬ ገብረ ኪዳን፣ ከጋዜጠኛ ሣሙኤል ፈረንጅ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ በትዝታ ጋዜጣ ላይ፣ስለ ጄኔራል ታሪኩ ማንነትና ስለተፈፀመው አሳዛኝ ውሣኔ የሰጡት ምስክርነት

ሌ/ጄኔራል ተስፋዬ ገብረ ኪዳን፣ስለ ጄኔራል ታሪኩ ማንነትና በመጨረሻው የአፍአበት ውድቀት ወቅት ስለተፈፀመው ሕገ ወጥ ድርጊት የሰጡት ምስክርነት ከሪፖርተር ጋዜጣ ላይ ተወስዶ ከዚህ በታች ቀርቧል።

ጉዳዩ የሚነሳው በአሥመራ ከተማ በኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ሰብሳቢነት፣በተደረገውን ስብሰባ መሠረት አድርጎ ነው። በዚያ ስብሰባ፣

- ሌ/ጄኔራል ተስፋዬ ገብረኪዳን፣
- ሜ/ጄኔራል ኃይለጊዮርጊስ ሀብተማርያም (የመከላከያ ሚኒስትር)
- ሜ/ጄኔራል ሥዩም መኮንን
- ሜ/ጄኔራል መስፍን ገብረቃል፣ (የወታደራዊ የፖለቲካ ጉዳይ ኃላፊ፣ እና
- ሜ/ጄኔራል ረጋሣ ጂማና ሌሎችም ከፍተኛ መኮንኖች ተገኝተዋል።

ስብሰባው፣ ብ/ጄኔራል ታሪኩ ዓይኔ በናደው ዕዝ አዛዥነታቸው በፈፀሙት ስህተት፣(ስህተቱ በጋዜጣው በዝርዝር አልተገለፀም) ከፍተኛ ቅጣት (ሞት) እንዲወሰንባቸው ኮ/መንግሥቱ ሀሳብ ሰጥተው ሌሎቹ ተሰብሳቢዎች እንዲናገሩ የተደረገበት ነው።

በዚህ ጊዜ ሌ/ጄኔራል ተስፋዬ ገብረኪዳን የራሳቸውን አቋምና ሀሳብ መግለጻቸው ተጠቅሷል። ይህን በተመለከተ ከጋዜጠኛ ሣሙኤል ፈረንጅ ጋር በተደረገው ቃለ ምልልስ ጄኔራሉ የስብሰባውን ሂደት የሚያሳይ ምስክርነታቸውን የሰጡት እንደሚከተለው ነበር።

‹‹.........ስለ ጄ/ ታሪኩ ዓይኔ የማውቀውንና የማስታውሰውን፣ኃይሌ የፈቀደውን ሁሉ በዝርዝር ለማስቀመጥ እሞክራለሁ። ዕድሉን ስለሰጠኸኝ በሙሉ ፈቃደኝነትና በደስታ አንኳር አንኳሮቹን ለማስቀመጥ እጥራለሁ። በጉዳዩም አምኜበት ስለምፈጽመው የህሊናና አካላዊ ፍትህና ሥጋት ፍፁም አይሰማኝም። ስለ ጄ/ታሪኩ የምሰጠው ምስክርነት መሠረት ይዤ ከተጨባጭ ጉዳይ ላይ በመነሣት ስለሆነ፣ ከህሊናዬ በስተቀር የሚወቅሰኝና የሚያስፈራኝ ምንም ነገር የለም።

‹‹ስብሳቢው፣የመጀመሪያውን ዕድል የሰጠው ለጄ/ ኃይለጊዮርጊስ ነበር። የኰ/መንግሥቱን ሀሳብ በመደገፍ በእሳት ላይ ነዳጅ እንደመጨመር ዓይነት አጋንነው፣ የበለጠ ክሱን አሳምረው ጄኔራል ታሪኩን ከነኑ። ጥፋተኛ ነው ብለው የምስክርነት ቃላቸውን ሰጡ።››

‹‹ሌላው (ቀጣዩ) ተናጋሪ ጄኔራል ሥዩም መኰንን ነበር። እሱም የኰ/መንግሥቱን አቀራረብና ሀሳብ በማድነቅ፣ ኰ/መንግሥቱን ለማስደሰት፣ መሠረት የሌለውና ተጨባጭነት የጎደለው የሀሰት ምስክርነቱን፣ ‹‹ታሪኩ ጥፋተኛ ነው።›› ብሎ መሰከረ።››





‹‹ቀጥሎ የዕድሉ ተጠቃሚ ጄኔራል መስፍን ገብረቃል፣ *(በስደት እንግሊዝ አገር ይገኛል ይባላል፣)* ነበር። ሲፈራ ሲቸር አቋም ለመውሰድ አንዳንድ ሀሳቦችን ሰነዘረ። ለምሳሌ ያህል፣ ኰሚቴ ተቋቁሞ ክሱ የበለጠ ቢጣራና ውሳኔ ቢሰጥበት የሚል ነበር። ቢሆንም የኰ/ መንግሥቱን ሀሳብ በሚገባ ተቀብሎታል።››

‹‹የመጨረሻው ዕድል የኔ ነበር። በዕድሉም በመጠቀም አመለካከቴንና አቋሜን በግልጽ ለማስቀመጥ ብሞክርም ተቀባይነት አልነበረውም። አቋሜም የነበረው፣ ገለልተኛ አጣሪ ኰሚቴ ተሰብስቦ ጉዳዩ በስፋትና በጥልቀት ጊዜ ወስዶ፣ የደረሰበትን ውጤት ለመርማሪ ችሎት እንዲያቀርቡ፣ መርማሪ ችሎትም የበኩሉን ከአጣራ በኋላ፣ ሀሳቡን ከነማስረጃው ለመከላከያ ሚኒስትሩ እንዲያቀርብ። የመከላከያ ሚኒስትሩም ከመርማሪው ችሎት በቀረበው ሀሳብና መረጃ መሠረት የሕግ ብይን እንዲሰጡ፣ ማለትም ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ለጦር ፍርድ ቤት መላክ፣ ሆኖ ካልተገኘ በማስጠንቀቂያ በነፃ መልቀቅ የሚል ነበር።››

‹‹እኔ ሀሳቡን ያቀረብኩት በወታደራዊ ሕግና ሥነ ሥርዓት ነበር። ቢሆንም ኰ/መንግሥቱ በቅድሚያ ከሦስቱ ጄኔራሎች ጋር ድርጅታዊ ሥራ አጠናቆ ስለመጣ ውሣኔውን በትእዛዝ ጭምር አስተላለፈ። ትእዛዙ አጭርና ግልጽ ነበር። ‹‹ሠራዊቱ በተገኘበት በነገው ቀን ይወገድ፣ጄኔራል ኃይለጊዮርጊስ ትእዛዙን አስፈጽመው እንዲያሳውቁኝ።›› የሚል ነበር። በማግስቱ ትእዛዙ መፈፀሙን አሳወቁ። ስለዚህ ጄኔራል ታሪኩ የተገደለው የኰ/መንግሥቱን ፍላጐት ለማርካት ብቻ ነበር።

‹‹የጄኔራል ታሪኩ ያለ ፍርድ መረሸን፣ በቋፍ ላይ የነበረውን፣ ሞራሉ የላሸቀውንና እንዲሁም ብሶት ያደቀቀውን ሠራዊት ውድቀት አፋጥኖታል።

‹‹ጄኔራል ታሪኩ በግፈ ቢረሸንም፣ ለአገሩና ለወገኑ የከፈለው መስዋዕትነት በቋሚ ታሪክ ምስክርነት ስሙና ገድሉ ለዘለዓለም ሲዘከር ይኖራል።ይህ የታሪክ ህቅ ስለሆነ ማንም ወይም  ምንም ሊሽረውና አፍኖ ሊያስቀረው አይችልም።

‹‹ጠቅለል ባለ መልኩ ስለ ጄኔራል ታሪኩ ዓይኔ የማውቀውንና የማስታውሰውን ያህል ለማስቀመጥ ሞክሬአለሁ። አሁን ደግሞ በጥያቄ መልክ የቀረቡትን እንደ ጥያቄው አቀራረብ በአጭርና በዝርዝር መልሱን አስቀምጣለሁ።

‹‹ጄኔራል ታሪኩ ሞት የተፈረደበት በጥላቻና ምናልባትም በየቆ ቂም በቀል ነው። ለአገሩ ያበረከተው አገልግሎትና በአስገኘው ውጤት ተመዛዝኖ ቢሆን ኖሮ ፈፀመው ለተባለው ስህተት ቢዛ በምክር ይታለፍ ነበር።‹‹እንኳን የጦር ፍርድ ቤት ይቅርና የምርመራ ችሎትም አልተቋቋመም። የመንግሥቱ ኃ/ማርያም አባባል፣ ‹‹ታሪኩ ጦር ፍርድ ቤት ቀርቦ እንደተገደለ የተናገረው ዓይን ያወጣ ግዙፍ ቅጥፈት ነው።

‹‹ጄኔራል ታሪኩ ለቀረበበት ወንጀል መከላከያ፣ በጠበቃ ወይም በገዛ ራሱ ለመከላከል መጀመሪያ ሕግና ሥነ ሥርዓት ሲኖር ነው። ስለዚህ በጄኔራል ታሪኩ ላይ ውሳኔ የተላለፈው፣ እርሱ በሌለበት ስለሆነ፣ ተከላካይ ጠበቃ አግኝቶ ለመነጋገር ሁኔታው አልፈቀደለትም። ዕድሉን አላገኘም። በጽሑፍም ሆነ በቃል መከላከያውን ለማቅረብ የተመቻቸ ሁኔታ





ለጄኔራል ታሪኩ አልነበረም። ወደ እርድ እንደሚነዳ እንስሳ ምንም ነገር ሳያውቅና ሳይናገር ወስደው ሠራዊቱ ፊት እንደ ወንጀለኛ ረሸኑት።

‹‹በእኔ አመለካከት በመጀመሪያ ደረጃ አንድ ርዕሰ ብሔረ ሥራውን የሚመራው በሙያው ብቃትና ዕውቀት ከተቻለ የረዥም ጊዜ ልምድ የአካበተ በሙያው ብስለት ያለው መሆን ይኖርበታል።

ኰ/መንግሥቱ፣ ከእኔ በላይ አዋቂ የለም በሚል እጉል እምነትና በራሱም ስለማይተማመን፣ በዚያም ላይ ሁል ጊዜ ስለሚጠራጠርና ስለሚሰጋ፣ ብዙ ጊዜ ይቅር የማይባል ስህተት ውስጥ ይዘፈቃል። ጄኔራል ታሪኩ ያለፍርድ ሲገደል፣ የመጀመሪያው ሰው አይደለም። ለማስታወስ ያህል አጼ ኃይለ ሥላሴ፣ ጄኔራል ተፈሪ በንቲ፣ ኰ/አጥናፉ አባተና ሻለቃ ሲሳይ ሀብቴ፣ በመፈንቅለ መንግሥት ምክንያት ደግሞ ያለፍርድ የተገደሉ መኰንኖች ወዘተ ይገኙበታል።››

*(ሪፖርተር ሰኔና ሐምሌ 1995 ቅጽ 7 ቁጥር 49)*

## ሚያዝያ 2 ቀን 2002 ዓ.ም
## ከመቶ አለቃ ታደሰ ቴሌ ሰልባኖ ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ፣
## ጥያቄ አቅራቢ  ፀሐይ መልአኩ

•

ሚያዝያ 2 ቀን 2002 ዓ.ም ሻምበል አለቃ ታደሰ ቴሌ ሰልባኖ ከዚህ መጽሐፍ አዘጋጅ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ፣ ጄኔራል

ታሪኩን ከመቼ ጀምሮና ለምን ጊዜ ያህል ያውቋቸው እንደነበረ በሰፊው መግለጫ ሰጥተዋል:: መግለጫቸውን ሲጀምሩም፣

‹‹ስሜ ታደሰ ቴሌ ሰልባኖ ይባላል መቶ አለቃ፣ በአሁኑ ጊዜ መጽሐፍ ደራሲ ነኝ:: የመጽሐፍ ድርሰቴም በወደታደራዊ ሳይንስና ወታደራዊ ታሪክ ላይ ነው ተመራማሪነቴ::

በቀድሞው ሠራዊት ውስጥ አብዛኛው ሥራዬ የርዕዮተ ዓለም ሥራ ወይም አይዲዮሎጂ ወይ በፖለቲካ ዘርፍ ከ1970 ዓ.ም ጀምሮ የቀድሞው መንግሥት ወይም የኅብረሰባዊት ኢትዮጵያ መንግሥት ደርግ እስከ ወደቀበት እስከ 1982 ዓ.ም ድረስ በወታደራዊ ሥራ በፖለቲካ ኃላፊነት በሻለቃ፣ በብርጌድ፣ በክፍለ ጦሮችና በዕዞች ተዘዋውሬ ሠርቻለሁ::›› በማለት ራሳቸውን አስተዋውቀዋል::

በመቀጠልም ብ/ጄኔራል ታሪኩ ዓይኔን በባህሪያቸውና፣ በተግባራቸው እንዲሁም በሙያቸውና ከሙያ ባልደረቦቻቸው ጋር በነበራቸው ቅርበት ምን ያህል ያውቋቸዋል ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ ሲመልሱ፣

‹‹ጄኔራል ታሪኩ ዓይኔን ከሌ/ኰሎኔልነት ማዕረግ ጀምሮ አውቃቸዋለሁ::ሻለቃ ማዕረግ በነበራቸው ጊዜ ደግሞ በምሥራቅ ዕዝ ትንሽ ጊዜ አውቃቸው ነበረ:: ከዚያ ጄኔራል ታሪኩ ከምሥራቅ ዕዝ ወደ ሰሜን ዕዝ ወደ መቀሌ ተዛውረው የ6ኛ እና 7ኛ ነበልባል ክፍለ ጦር እንዲያሰለጥኑ መንግሥት በሰጣቸው ኃላፊነት፣ ሁለት ክፍለ ጦሮችን መቀሌ ላይ በማሰልጠን ላይ ነበሩ::

‹‹በ1970 ዓ.ም ግንቦት ወር ላይ እኛ ከፖለቲካ ት/ቤት የተውጣጣን ቡድን እንደ ታሪክና እንደ አንድ ተምሳሌት





መቀሌ ላይ ተገኝተን፣ ከየካቲት 66 ፖለቲካ ት/ቤት አርባ ተማሪዎች ተመርጠን በመቀሌና በአሥመራ ጉብኝት ባደረግንበት ወቅት፣ ጄኔራል ታሪኩ እንደርታ በሚባል ወታደራዊ ካምፕ አግኝተናቸዋል::

‹‹የ6ኛ እና የ7ኛ ክፍለ ጦርን ሠራዊት አሰልጥነው 7ኛ ክፍለ ጦርን ወደ ጎንደር አስማርተው፣ 6ኛ ክፍለ ጦርን ደግሞ በትግራይ በተለያዩ ቦታዎችና በኤርትራ ደቡባዊ ክፍሎች በብርጌድ ደረጃ በማሰማራት ወታደራዊ ግዳጃቸውን እየተወጡ ተገናኝተናል:: በመቀሌ ራስ ሆቴል የራት ግብዣ አድርገውልን ከቡድኑ ጋር አብረን ፎቶ ተነስተናል:: ብዙ የልምድ ልውውጥም አድርገናል:: ለእያንዳንዳችንም ነበልባል አርማ ያለበትን የ6ኛ ክፍለ ጦርን አርማ፣ ትከሻ ላይ የሚደረገውን የሠራዊቱን አርማ ለሁላችንም አድርገውልን ስለነበረ ከመነሻ በዚህ ነው የማውቃቸው::

‹‹ከዚያም ከመቀሌ በኋላ እኔ ወደ ፖለቲካ ትምህርት ቤት ተመልሼ ትምህርቴን እንዳጠናቀቅሁ ወደ አሥመራ ስመደብ እሳቸው ‹በምሥራቅ የተገኘው ድል በሰሜን ይደገማል..› ተብሎ መንግሥት አዋጅ በወጣበት ወቅት ጎንደር በመሄድ የ7ኛ ክፍለ ጦር፣ ገስጥ የሚባል ሠራዊት አዛዥ ነበሩ::

‹‹በጎንደር ቀጠናቸው ጎጃምን ደቡብና ሰሜን ምሥራቅና ምዕራብ ጎንደርን እንደገና ምዕራብ ኤርትራን በስለላና በወታደራዊ ግዳጆች እንዲቆጣጠሩ፣ምዕራብ ትግራይን ተከዜ ወንዝን ይዞ ያለውን ሽሬን ጨምረው እንዲቆጣጠሩ ወታደራዊ ቀጠና ተሰጥቷቸው ይህን ግዳጃቸውን በመወጣት ላይ እያሉም አውቃቸዋለሁ::

‹በምሥራቅ የተገኘ ድል በሰሜን ይደገማል› በተባለበት ወቅት፣ 3ኛ ክፍለ ጦር ከምሥራቅ ተነስቶ ጎንደር በገባበት

ወቅት እኛም አሥመራ ሄደን፣ ከአሥመራ እንደገና ወደ ጦር ክፍሎች ከመመደባችን በፊት የዚያን ጊዜ ሻምበል ማዕረግ ነበራቸው።

ኮሎኔል ሽዋረጋ ቢሆን የሚባሉ ወታደራዊ የፖለቲካ መምሪያ ኃላፊ አማካይነት ከብርጌዶችና ከተለያዩ ክፍሎች የተውጣጣን በግምት ምናልባት ሪስቼው ካልሆነ ወደ አርባ የምንሆነው፣ መኰንኖችና የበታች ሹማምንቶች ጎንደር በሁለት ዙር ሄደን ጎንደር ላይ ተገኛኘተል።

በተገናኘንበት ወቅት ተቀብለውን፣ በሬ በማረድ የአርማ ልውውጥ በማድረግ ከሠራዊቱ ዱሮም በኦጋዴን ይተዋወቁ ስለነበረ በከፍተኛ ልቅሶ፣ በከፍተኛ ስሜት፣ በከፍተኛ ጭፈራ ሠራዊቱ ሞራል እንዲያገኝ በተደረገው ትልቅ ባዛር እነ ጥላሁን ገሠሠ፣ እነ ብዙነሽ፣ እነ ተፈራ ካሣ፣ እሳቱ ተሰማ የሚባሉት ዘፋኞች ሌሎችም ነባር የሙዚቃ ሰዎች በተገኙበት ከፍተኛ ድግስና ከፍተኛ ግብዣ ጎንደር ላይ ተደርጎ በነበረበት ጊዜ የመክፈቻ ንግግሩን ያደረጉት፣ በዚያን ጊዜ ማዕረጋቸው ሌ/ኰሎኔል ነበረ፣ ሌ/ኰሎኔል ታሪኩ ዓይኔ ናቸው።

‹‹እዚያ የነበረው ሠራዊት በተለይ ታሪኩን ‹ታላቅ ወንድሜ› እያሉ የ3ኛ ክፍለ ጦር አባላት ‹የኔ ጋሻ.....የኔ አንበሳ...› እያሉ ሲያሞከሹአቸው ነበር። አይቻለሁ ሰምቻለሁ፣ እኔም እዚያው ነበርኩ ይህን አውቃለሁ። 7ኛ ክፍለ ጦር አባላት ደግሞ፣ ‹ታሪኩ ዓይኔ አባታችን....ለዘላለም ይኑር....› በማለት መፈክር ሲያሰሙ ባወቅቱ ተጨብጭቦላቸው ነበር።





‹‹በወቅቱ ብ/ጀኔራል ማዕረግ ነበራቸው፣ ሌ/ጀኔራል ተስፋዬ ገብረ ኪዳን በወቅቱ በበዓሉ ላይ ተገኝተዋል። በበታች ሹም ማዕረግ በዚያን ጊዜ በመቶ አለቃ ማዕረግ የነበረ በዚያን ጊዜ ሻምበል ለገሠ አስፋው ሌሎችም የፖለቲካ ኃላፊዎች በቦታው ተገኝተው የአርማ ልውውጥ ለሠራዊቱና ከዘመቻ መምሪያው ወይም ከወታደራዊ መንግሥት መሪ ከኰ/መንግሥቱ ኃ/ማርያም የተላከውን አርማ ለሠራዊቱ በመስጠት ጀኔራል ተስፋዬ ለታሪኩ፣ ታሪኩ ለሠራዊቱ በሰጡበት ወቅት በቦታው ላይ በሙሉ ኰሎኔል ማዕረግ ረጋሣ ጂማ ነበሩ።

ይህን ሠራዊት ከጎንደር ይዘው በሁመራ በኩል በተሰነይ አድርገው ወደ ኤርትራ እንዲገቡ ግዳጅ የተሰጣቸው ሲሆን፣ 7ኛ ክፍለ ጦር ደግሞ ማገኛውንም እንቅስቃሴ. አድርጎ በትግራይ ሽሬን ተራምዶ ሽሬን እንዲቆጣጠር፣ ሽራሮንና እስከ ተከዜ ወንዝ ያለውን እንዲቆጣጠር ሌላ ሚሊሺያ ብርጌድ ተጨምሮላቸው እንደሚወጡና ሌሎችም ከመቀሌ ተነስተው በደቡባዊ ኤርትራ በአዲ ቀይህ በኩል በፆረና በኩል በአቆርዳት በኩል በመስበር የኤርትራን ወንበዴ የኤርትራን ተገንጣይ ቡድን ሻዕቢያንና ጀብሀን ለመደምሰስ መንግሥት ከፍተኛ እቅድ ነበረው።

ከፍተኛ ተዋናይ ከነበሩና ለሠራዊቱ ከፍተኛ ቅስቀሳ ሲያደርጉ ከነበሩት በወቅቱ ማዕረጋቸው ሌ/ኰሎኔል በመጨረሻ ብ/ጀኔራል ታሪኩ ዓይኔ አንዱ ናቸው። ከዚያም ጦርነቱ እንዳበቃ በቀይ ኮከብ ዘመቻ ለአጭር ሴሚናር አሥመራ መጥተው ነበር።

ኰሎኔል ታሪኩ፣ሻለቃ መላኩ ተፈራ፣ የጎጃሙ አስተዳዳሪ ሻለቃ ካሣዬ አራጋው፣ አሥመራ መጥተውና ታሪኩ ኒያላ ሆቴል አርፈው በነበረ ጊዜ በአካል ተገናኝተን ነበር። አብረንም ፎቶ ተነስተናል።

የአሥመራን የተለያዩ ክፍሎች፣ የአሥመራ ዙሪያ ጥበቃ በኛ ሥር ስለነበረ እኔ በወቅቱ የ262 ሜካናይዝድ ፖለቲካ ኃላፊ ስለነበርኩ የአሥመራ ጥበቃ በኔ ሥር ነበር። በዚህ ጊዜ ተገናኝተን ዱሮ ቀደም ሲል ለአጭር ጊዜ የሚያውቁትን ቦታ አሳዩን። እኛም አሳየናቸው። በተመደበላቸው ላዳ መኪና እየተዘዋወርን ከምሽቱ አንድ ሰዓት፣ ሰዓት እላፊ ስለነበረ እርሳቸውን ኒያላ ሆቴል አድርሰን በማግስቱም ተገናኝተን በሄሊኮፕተር ወደ ጎንደር ሄዱ።

‹‹እንግዲህ የቀይ ኮከብ ዘመቻ ካከተመ በኋላ እሳቸው በአጋጣሚ ሞስኮ ላይ በ1975 ዓ.ም ሚያዝያ የፋሲካ ፍቺ ሰሞን ይመስለኛል፣አብረን ሞስኮ ነበርን። እሳቸው ለክፍለ ጦር አዛዥነት እኛ ደግሞ ለወታደራዊ ፖለቲካ ሥራ በሚባል የሌኒንዝም ሥራዎች ለመማር ሌኒኒግራድ ሄደን ነበር። እሳቸውም በሌኒንግራድ ዩኒቨርሲቲ በክፍለ ጦር አመራር ከሌሎች ጄኔራሎች ጋር እነ ካሣዬ ጨመዳ ነበሩ፣ ሌሎችም ኮሎኔሎች ነበሩ፣ እዚያ ለተወሰነ ጊዜ አብረን ቆይተን፣ እኛ ቀድመን መጣን። እነሱ በኋላ ሁለት ዓመት ቆይተው ነው የመጡት።

‹‹ከዚያ ከመጡ በኋላ ጎንደር ሄደው ጎንደር ሲሠሩ ከቆዩ በኋላ በነበረው የፖለቲካ አለመጣጣም ከሻለቃ መላኩ ተፈራ ጋር ግጭት ነበራቸው።

‹‹ቀጥሎም ሆለታ አዛዥ ከነበሩት አለቆች ይሰጥ ወደነበረው የርዕዮተ ዓለም ኮርስ ገብተው፣ ራሽያ ይሰጥ የነበረው ትምህርትና እዚያ/ሆለታ የሚሰጠው ትምህርት አልተጣጣመም በማለት፣ ከአዳዲስ የሆለታ ሠልጣኞች ጋር ምክትል የመቶ አለቃ





በነበርኩበት ጊዜ የተማርኩትን እንደገና አልማርም በማለት ወደ ጎንደር ተመለሱ።

‹‹በዚህ ጊዜ ሌኒኒዝምንና ማርክሲዝምን ረግጠው ወጥተዋል በማለት ተከሰው፣ሻለቃ መላኩ ተፈራ ያደርጉባቸው የነበረው የፖለቲካ ሪፖርቶች ሁሉ ተደምረው፣

‹‹ኮሎኔል ታሪኩ ከነጋዴዎች ጋር ተመሳጥረዋል፣ ከሕዝቡ ጋር ፀጉርና ቅቤ ሆነዋል፣ እንዲያውም ከፀረ ሕዝቦች ጋር ግንኙነት ሳይኖራቸው አይቀርም በማለት በአስቸኳይ ከጎንደር ይነሱ ተብሎ፣ እሳቸው በሌሉበት ተሰብስበው በመወሰን ለኘሬዚዳንት መንግሥቱ አቀረቡ።

‹‹ኘሬዚደንት መንግሥቱ ታሪኩን በቀረቤታ ያውቁ ስለነበረ፣‹‹አይመስለኝም፣ ይኼ የምታቀርቡት ሁሉ ስም ማጥፋት ይመስለኛል፣ ስለ ትምህርቱ እምቢታም ቢሆን፣ ትምህርቱ ከኔ ዕውቀት ጋራ አይሄድም ያለው፣ ምናልባት የበለጠ ዕውቀት ኖሮት ይሆናል፣ወይም የሚያስተምሩት ሰዎች ብቃታቸው ዝቅ ብሎ አግኝቶት ይሆናል።

‹‹ታሪኩ ፊት ለፊት መናገርን ይወዳል። በዚህ ምክንያት አልተግባባችሁ ይሆናል እንጂ ይህንን ያህል አብዮቱን ለመጉዳት ሰሜን ኢትዮጵያን ለድል ያበቃ ሰው፣ ከድል በኋላ ከጠላት ያብራል ብዬ ግምት የለኝም።

‹‹ሆኖም ጎንደር በመቆየቱ ባለው ሁኔታ ከሱም ጋራ ልትጣጣሙ ስላልቻላችሁ የደቡብ ዕዝ እዛዥ ይሆናል ብለው ከጎንደር አነሱዋቸውና የደቡብ ዕዝ አዛዥ ሆኑ።

‹‹ደቡብ አዛዥ ሆነው ሲመሩ በነበሩበት ጊዜ መንግሥቱ ብዙ ሴኩሪቲዎችን መድበው ብዙ የፖለቲካ ሰዎችን መድበው ታሪኩን እንዲገመገሙ አድርገዋል።

‹‹ይሁንና ታሪኩ የዋህና አገር ወዳድ፣ሆነው በመገኘታቸው ጎንደር ይወራባቸው የነበረው ሁሉ ውሸት ሆኖ በመታየቱና እስከ ብሔር ብሔረሰቦች ዘልቆ የአካባቢ ሚሊሺያ በመመልመል በማስታጠቅ አካባቢያቸውን እንዲያለሙ፣በቋንቋቸው እንዲ ጠቀሙ፣ከመንግሥት ጋር እምነት እንዲያደርጉ ከፍተኛ ሥራ ሠርተዋል።

‹‹ፈጽሞ ለመንግሥት ግብር ከፍለው የማያውቁት ኋላ ቀር ብሔረ ሰቦች፣ የመንግሥት ግብር እየከፈሉ እንዲያርሱ፣ መንግሥትም ሕክምና እንዲሰጣቸው፣ ራሽን እንዲሰጣቸው፣ ማንኛውንም ድጋፍ እንዲያደረግላቸው በማድረጋቸው፣ ይህ ራሱ የፖለቲካ አመራር ነው በሚል ተመስግነውበታል።

‹‹ከወታደራዊ ግዳጅ ባሻገር ሲቪላዊ አመራር በመስጠታቸው ለስንት ጊዜ በኢሠፖአኮ አመራር አባልነት ደቡብን ከመሩ ሰዎች ተሸለው ተገኝተዋል።

‹‹በሌላም በኩል ሱማሌ ሊወረን በነጌሌ ቦረና በኩል በመጣበት ጊዜ፣ ወደ ኬንያ ድንበር ሁለት ክፍለ ጦር ሠራዊት እንዳቀረቡ በማስመሰል ነገር ግን ሁለት ሻለቃ ጦር በማቅረብ ግራና ቀኝ አልፈው በሱማሌዎች ሽብር በመፍጠር የሶማሌ ሜካናይዝድ ክፍለ ጦር በፍርሀት ከአካባቢው ያለ ምንም ውጊያ እንዲሸሽ አድርገዋል።





‹‹ያ የሱማሌ ጦር ትጥቆቹንና ስንቁን ጥሎ እስከመሸሽ ደርሶ ነበርና ይህም ቀላል ወታደራዊ አመራር አይደለም በሚል፣ (በዚያ ወቅት መንግሥቱ ትንሽ አስተዋይነት ነበራቸው በመጨረሻ እንደወሰዱት እርምጃ አልነበረም፣ ሰውን በጥልቀት የመመርመር ብቃት ነበራቸው።)እና ታሪኩን ለማሳደግ አሰቡ።

‹‹ለወታደራዊ ጄኔራልነት ታሪኩ አያንስም ደካማ ጉንም ካለው ሹመነው እንገመግማለን ብለው፣ ከደቡብ ዕዝ አምጥተው ብ/ጄኔራል በማድረግ የተወሰነ ጊዜ አዋሳ ላይ እንደሠሩ ካደረጉ በኋላ፣ ይኼ ለትግራይ ዕዝና ለደቡብ ኤርትራ ወሳኝ ሰው ነው፣ ጎንደርን፣ ጎጃምን፣ ትግራይንና ደቡብ ኤርትራን፣ ምሥራቅ ትግራይን፣ ወይም ምዕራብ ቀይ ባህርን ጠረፍ፣ በወሳኝ ደረጃ መጠበቅ የሚችል ብቃት ያለው ሰው ነው፣› ብለው ለአራት ክፍለ ጦሮች የበላይ ኃላፊ ሆነው በመንግሥቱ የተሾሙ የትግራይ ዕዝ አዛዥ ነበሩ።›› ሲሉ የማወቃቸውን አድማስ ስፋትና የጊዜ ርዝመት አብራርተው ገልጸዋል።

ከጄኔራል ታሪኩ በኋላ ስለሆነው ሁኔታ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣

‹‹......መንግሥቱን ለመገልበጥና ሥልጣን ለመያዝ፣ ኤርትራን ያለምንም ውጊያ ለመገንጠል፣ ለትግራይ የራስ ገዝ ሥልጣን ለመስጠት እና የተቀሩትን የኢትዮጵያ ግዛቶች ለማስተዳደር የክቡር ዘበኛ ሠራዊት ጄኔራሎች ፍላጎት ነበራቸው።ለዚህም ወታደራዊ መፈንቅለ መንግሥት ዝግጅት ሲያደርጉ ሠራዊቱ ከታሪኩ ሞት ጀምሮ ሲያደርጉት የነበረውን አሻጥር ያውቅ ስለነበረና፣ በጄኔራሎቹ መካከል የነበረውን ፍጥጫም ያውቅ ስለነበረ፣ አንድም ጄኔራል ሳይተርፍ ሠራዊቱ አሥመራ ላይ 27 ጄኔራሎችን ጨፍጭፏል።

‹‹ለጄኔራል ታሪኩ ያልሆናችሁ ለኢትዮጵያ እንዴት ትሆናላችሁ በማለት ሠራዊቱ ጨፈጨፋቸው፡፡ የጄኔራል ደምሴ ቡልቶን አንገት ሠራዊቱ ቆርጦ በቀረው አካላቸው ላይ የኢትዮጵያን ባንዲራ አስገብቶ አሥመራ ውስጥ አዙሯል፡፡ በወቅቱ አሥመራ ስለነበርኩ ካየሁትና የማስታውሰው ነው፡፡

‹እዩት.....ይኼ የጄኔራል ታሪኩ ዓይኔ ጠላት ነው፣ ለዚህ ያበቃው የጄኔራል ታሪኩ ዓይኔ በግፍ መገደል ነው፡፡ የማትወድቀው የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማችን ዛሬ በግፈኞች ሬሳ ላይ ከፍ ብላ ትውለበለብ፣ እየተባለ፣ በድምጽ ማጉሊያ እየተነገረ አሥመራ ላይ ሕዝብ እንዲያይ ተደርጓል፡፡ ሲሉ ከጄኔራል ታሪኩ ሞት በኋላ በሌሎችም መኰንኖች ላይ የደረሰውን አደጋና የታሪክ ውድመት አስረድተዋል፡፡

በመቀጠልም፣ ‹‹እንግዲህ ጄኔራል ታሪኩ ክፉ ሰው ቢሆኑ ኖሮ፣ ከሞቱ በኋላ የሠራዊቱን ምስክርነት አያገኙም ነበር፡፡

‹‹ጄኔራል ታሪኩ የሞት ቅጣት ውሳኔ የተላለፈባቸው የካቲት 6 ቀን ከቀኑ አስር ሰዓት አካባቢ ነው፡፡ በዚያው ቀን ማታ ለጄኔራል ታሪኩና ለጄኔራል ከበደ ጋሼ የራት ግብዣ ፕሬዚደንት መንግሥቱ አድርገዋል የሚል የፕሮቶኮል ወረቀት ተሰጧቸዋል፡፡

‹‹በዚያው ዕለት ደግሞ ለጄኔራል ታሪኩ ከገጀረት ሆስፒታል ለጦር ኃይሎች ሆስፒታል የሪፈራል ወረቀት ወጥቶላቸው በማግስቱ ወደ አዲስ አበባ የሚበሩበት ሁኔታ ተዘጋጅቶ ነበር፡፡ ‹ታሪኩ አዲስ አበባ ከሄደ ከጀሌዎቹ ጋር ተመሳጥሮ ከአገር ይወጣልና ተይዞ ይታሠር፣...› በሚል ውንጀላ ጠላቶቻቸው ኰ/መንግሥቱን ስሜት የሚገዛ ነገር መወትወት ቀጠሉ፣ ከምድረ ገጽ የሚያጠፉ ሴራቸውን ተበተቡባቸው፡፡





‹‹የካቲት ስድስት ቀን ማታ ተደግሶላቸው የነበረውን መከራ ያላወቁት ጄኔራል ታሪኩና ጄኔራል ከበደ በተጠሩት የራት ግብዣ ላይ ተገኝተው ከመንግሥቱ ጋር ራት በሉ፡፡ ከዚያም አልጋ ከያዙበት ሀማሴን ሆቴል በር ላይ ሲደርሱ ታፍነው፣ አሥመራ ሚሊተሪ ፖሊስ ቃኘው ታስረዋል፡፡

‹‹አንድ ስሙን የማውቀውና ስሜ እንዳይገለጽ ያለኝ፣ በወቅቱ ጥበቃ ላይ የነበረና በርሸና ላይም የተሳተፈ፣ በአሁኑ ጊዜ ሱሉልታ ከተማ የሚገኝ፣ በዚያን ጊዜ ማዕረጉ የሃምሳ አለቃ፣በመፈንቅለ መንግሥቱ የመቶ አለቃ የሆነ ወታደር እንደነገረኝ፣ልክ እጃቸውን በሰንሰለት ታስረው እስር ቤት ገብተው በመሬት ላይ በተነጠፈ ፍራሽ ላይ እንዲተኙ ጄ/ታሪኩ በታዘዙበት ወቅት፣

‹‹.....ወይኔ ታሪኩ፣ በጠላቴ ተበላሁ.... ረጋሣ ጂማ ተሳካለት፣ መንግሥቱ ኃይለ ማርያምስ ጦር ሠራዊት መሆኑን እንዴት ዘነጋው፣...... ስለ እኔ ማንነት፣ ስለእኔ ታሪክ የጎንደር ሕዝብ፣ የትግራይ ሕዝብ፣ የኤርትራ ሕዝብ፣ የሐረር ሕዝብ የሲዳሞ ሕዝብ ይመስክር፣ እኔ አብዮተኛ አይደለሁም ወይ......

ለዚች አገር ብዬ ከልጆቼ ጋራ አንድም ቀን ዓመት በዓል ውዬ አላውቅም፡፡ ለልጆቼ እንኳን ደህና ልብስ ገዝቼ አልብሼ አብሬ ታይቼ አልታወቅም፣....በማታ ገብቼ በማግስቱ ጠዋት ልጆቼን በጨረፍታ አይቼ ወደ ግንባር የምመለስ ሰው ነበርኩ፣ እኔ የሠራዊቱ አባት አይደለሁም ወይ......ኤርትራንና ትግራይን ነፃ ካወጡት አንዱ አይደለሁም ወይ...... ውለታዬ እንዴት ተረስቶ የሞት ድግስ ውስጥ እንዴት ገባሁ፣.....

የረጋሣ ጂማን ታሪክ መንግሥቱ ኃይለማርያም እንዴት ረሳው..... ሕይወቴ ይፋረድ......ታሪኬ ይፋረድ.... እኔ ብሞትም ታሪክ አይሞትምና ሀቁን ያወጣልኝ ይሆናል፣.....እስካሁን ስለፋሁት ልፋቴም የኢትዮጵያ ሕዝብና እግዚአብሔር ውለታዬን ይከፍሉ ኛል፡፡......ከዚህ በኋላ ሠራዊቴንና ልጆቼን መሰናበት እንኳን አልቻልኩም፣ በፈረዱብኝ ላይ እግዚአብሔር ይፍረድ ሌላ ምን እላለሁ...›› እያሉ ሲያለቅሱ እንዳደሩ ነግሮኛል፡፡

‹‹በማግስቱም እጃቸውን ታስረው እኔና ሌሎችም ባለንበት አዲ ጉአዲድ በተባለ ቦታ ላይ ሠራዊቱ ተሰብስቦ አንድ ገጽ ወረቀት ብቻ ከተነበበ በኋላ ዘጠኝ ሆነው በተሰለፉ የሠራዊቱ ሰዎች የእሩምታ ጥይት ተኩሰው ገለዋቸዋል፡፡

‹‹ከዚያም አስከሬናቸው ተነስቶ ፀፀረት በተባለ ቃኘው ጆርባ በነበረው ቤተ ክርስቲያን ኦርቶዶክስና ካቶሊክ ሚቾች በሚቀበሩበት አስራ አራት ቁጥር ከሚባለው መቃብር ጐን ነው የተቀበሩት፡፡ መቃብራቸው አሁንም አሥመራ ይገኛል፡፡ እንግዲህ ጀኔራል ታሪኩን የማውቃቸው እስከዚህ ነው፡፡





# ምዕራፍ ፱

## እንደ ታሪክ ፀሐፊዎቹ ማስረጃና ምስክርነት ታላቁ የናደው ዕዝ የተናደበት ሁኔታ፣

በታላቁ የናደው ዕዝ መናድና በኢትዮጵያ ሠራዊት አወዳደቅ ሁኔታ ላይ አሳማኝ እውነተኛ ታሪኮች ተጽፈው ቀርበዋል፡፡ ወደፊትም ይጻፋል፡፡

በከፍተኛ የዕዝ ደረጃ ባለሥልጣናት ሆነው ሠራዊት የመሩና የትግል ሂደቱ ተካፋዮች የነበሩ ሕያው ምስክሮች ከጻፏቸው መጻሕፍት በተጨማሪ እንደ ዕድል ከእልቂቱ ተርፈው በሕይወት የሚገኙ የሠራዊቱ አባላት የነበረውን የጦርነቱን እውነተኛ ገጽታ በመግለጽ ሕዝቡን ከአሉባልታ ታሪክና ከውዥንብር አላቀውታል፡፡

በዚህም መሠረት ሕግን በረገጠ የበላይነትና በግፍ የተፈፀሙ የመንግሥት ድርጊቶች በወቅቱ ሀሰተኛ ምክንያታዊ መግለጫዎች ተሰጥተዋቸው እንደነበርና አሁን ግን እውነት ስታንሠራራ ራቁታቸውን እንደቀሩ መገንዘብ ተችሏል፡፡

የደርግ መንግሥት ከሥልጣን ኮርቻ ላይ የተፈናጠጠው ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ በአምባ ገነንነት መሆኑን ስለሚያውቅ፣ የነቁና የተደራጁ ኃይሎች ይገለብጡኛል የሚል ከባድ ሥጋትና ጥርጣሬ ነበረው፡፡ በዚህም ምክንያት በየክፍለ ጦሩ አዛዦችን በማጣላትና በማናከስ ከፋፍሎ የመግዛት ስልት ይጠቀም ነበር፡፡